# ምዕራፍ ስድስት

# አፍሪካ በጣሊያን

የአፄ ዮሐንስ ልጅ የሆነው መንገሻ ከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ ባይኖረውም መልከመልካም እና የተለየ መስህብ የታደለ ነበር። እጅግ ውብ ከሆነው ገጹ በተጨማሪ ያማረ አለባበሱ የማንንም እይታ ሊማርክ ይችላል። በበርካታ ፎቶዎች ላይ እንደሚታየው ፀጉሩን ሹሩባ ይሠራ የነበረ ሲሆን ጆሮውም ላይ ሎቲ ያንጠለጥል ነበር። ከአልባሳቱ በተጨማሪም እጅግ ማራኪ መዓዛ የነበራቸውን ሽቶዎችን ይቀባም ነበር። በዘመኑ ሽቶ ያመጡ የነበሩት ሙስሊም ነጋዴዎች በመሆናቸው የአገሬው ሰው ሽቶ መቀባትን ከኃይማኖት አልባነት ጋር ያገናኙ ነበር።

ልውል አልጋ ወራሽ መንገሻ ከሕዝቡ የሚነሳበትን የሴታሴትነት እና ለስላሳነት ሽሙጥ መቋቋም ቢችልም የአባቱን ዘውድ ለመውረስ የማይችል መኾኑን ሲጠቋቆሙበት ግን መፍረክረክ ጀመረ። የመንገሻ እናት በታሪክ ስሟ ያልተጠቀሰች አንዲት የዮሐንስ ዕቁባት እንደሆነች እና መንገሻም የዮሐንስ ሕጋዊ ልጅ እንዳልሆነ ሕዝቡ ውስጥ ለውስጥ ማውራት ቀጥሎ ነበር።

በ1889 ከመሃዲስቶች ጋር በመዋጋት ላይ ሳሉ ቆስለው የነበሩት አፄ ዮሐንስ ቃሪዛ ላይ ሳሉ የዘውዳቸው ወራሽ ወንድ ልጃቸው መንገሻ እንደሆነ መናዘዛቸውን መንገሻ እንደ ሕጋዊ መረጃ ያቀርብ ነበር። የዮሐንስን ሞት ተከትሎ በተደረገው የዘውድ ሹሚያ መንገሻ ሙሉ በሙሉ ከውድድር ውጪ ተደረገ። የአባቱን ዘውድ ከምኒልክ ላይ ለመንጠቅም የግድ ብዙ መልፋት ያስፈልገው ነበር።

የመንገሻ ዋና መተማመኛ የነበረው አሉላ ሲሆን ይህ የአፄ ዮሐንስ ታላቅ የጦር መሪ ለንጉሡ የነበረውን ታማኝነት እርሳቸው መተማ ላይ ከሞቱ በኋላ በልጃቸው ደግሞታል። አሉላ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ከውጪ ወራሪ ኃይሎች





ጥቃት የጠበቀ እና ለወራሪዎች በተለያዩ የጦር አውዳሚዎች ታላቅ ትምህርትን የሰጠ ታላቅ የጦር መሪ ነው። በ1870ዎቹ ተደጋጋሚ የወረራ ሙከራ ያደረገውን የግብፅ ጦር ጉራ እና ሰአቲ ላይ ድል ነስቶ መልሷል። በ1880ዎቹ በግብፅ እግር የተተካውን የጣሊያን ወራሪ ኃይል ዶጋሊ ላይ ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ የውርደት ካባ አከናንቧቸዋል። ከዶጋሊው ሽንፈት በኋላ በርካታ ጣሊያናውያን አሉላን «ኢትዮጵያዊው ጋሪባልዲ» በማለት ከዘመናዊት ጣሊያን መሥራቹ ጋሪባልዲ ጋር ሲያመሳስሉት ተደምጠዋል።

የአሉላ ድጋፍ እያለው እንኳን መንገሻ የሥልጣን የወራሽነት ሚናውን በአግባቡ ማሳየት አልቻለም ነበር። በአሉላ እና መንገሻ መካከል የነበረው ልዩነት የመወሰድ እና የጀግንነት ንፅፅር ነበር። መንገሻ የዘር ሐረጉን መሠረት በማድረግ ዘውዱን ለመውረስ ሲንቀሳቀስ ሕዝቡ ግን አድናቆትን ይሰጥ የነበረው በጀግንነቱ ለሚያውቀው አሉላ ነበር። ታሪክ አሉላን የሚያወሳው «በዘመናዊ ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው አፍሪካዊ ጀነራል» በማለት ነው። በዚህ የተነሣም የዘውድ ወራሹ መንገሻ ምስል ከአሉላ አንፃር ሲታይ ፈዛዛ ነበር።

የአፄ ዮሐንስን ሞት ከምኒልክ የተሻለ ሊጠቀምበት የተዘጋጀ አልነበረም። የሸዋው ንጉሥ የራሱን ጦር ከማደራጀት ጎን ለጎን ከጣሊያን ጋር ምስጢራዊ ጓደኝነቱን አጠናክሮ የዮሐንስን ሞት ወይም ከሥልጣን የመወገድ አጋጣሚ ሲጠባበቅ ነበር። ወጣቱ ጣሊያናዊ መልዕክተኛ ፒየትሮ አንቶኔሊ ኢትዮጵያ ከደረሰበት ከ1879 ጀምሮ ከምኒልክ ጋር ወዳጅነቱን ሲያጠናክር ከርሟል። የምኒልክ እና የጣሊያን ወዳጅነት ጣሊያን በ1885 ምፅዋን ስትይዝ ከአፄ ዮሐንስ ጋር ግልጽ ቅራኔ ውስጥ በመግባት ከምኒልክ ጋር ቁርኝቷ ጠነከረ። ዮሐንስን የጋራ ጠላት በማድረግ የጣሊያን እና የምኒልክ ወዳጅነት ጠነከረ። የአንቶኔሊ ዋና ተልዕኮ የነበረው እንግሊዝ ዮሐንስን በአፄ ቴዎድሮስ ላይ እንዳሥነሳችው ኹሉ ጣሊያንም ምኒልክን አፄ ዮሐንስን ለማዳከም እንድትጠቀምበት ማስቻል ነበር።

ምኒልክ ከጣሊያን የሚያገኙትን ድጋፍ ላለማጣት ሲል የጣሊያን መጠቀሚያ ለመሆን ተስማማ። ከጣሊያን በሚቀርብለት የጦር መሣሪያ ኃይሉን አጠናክሮ ዮሐንስን መገዳደር እና ግዛቱን ማስፋት ችሎ ነበር። የዶጋሊን ውርደት ተከትሎ ጣሊያን አሉላን እና ዮሐንስን ለመበቀል ስትዘጋጅ የምኒልክን ድጋፍ እንደምታገኝ ተስፋ አድርጋ ነበር። ለዚህም ስትል ዐሥር ሺህ የሬሚንግተን ጠመንጃ ከአራት መቶ ሺህ ጥይት ጋር ለምኒልክ ለማቅረብ ቃል ገባች።

ምኒልክ የአንቶኔሊ ዋና ተልዕኮ ኢትዮጵያን መከፋፈል እንደሆነ የተረዳው በፍጥነት ነበር። በተጨማሪ የጎጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖት እና የወሎው ራስ ሚካኤል ከአፄ ዮሐንስ ተፅዕኖ ነፃ በመሆን የየራሳቸውን ግዛት ለመገንጠል መዘጋጀታቸውንም ምኒልክ ተረድቷል። በርካታ የግዛት አስተዳዳሪዎች የአፄ ዮሐንስን ብቸኛ የስልጣን ባለቤትነት ከልባቸው አልተቀበሉትም ነበርና እንደ ዘመነ መሳፍንቱ ጊዜ የየራሳቸውን ግዛት የሚያስተዳድሩበትን አጋጣሚ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

የአንቶኔሊ ስሌት የነበረው አገሩ ጣሊያን የቀይ ባሕር ወደብ የነበሩትን ምፅዋ እና ዘይላን በመያዝ የምኒልክን የባሕር በር አማራጭ በእጇ ለማስገባት ነበር። አንቶኔሊ በግሉ አፄ ዮሐንስ አገሪቷን አንድ አድረገው መግዛታቸውን ያደንቃል። ነገር ግን እርሳቸው በሆነ መንገድ ቢወገዱ በርካታ የሥልጣን ተቀናቃኞች ስለሚኖሩ አገሪቷ በእርስ በእርስ ግጭት እንደምትበታተንም ገምቶ ነበር። ግምቱ ከተሳካም አገሩ ጣሊያን ምኒልክን በመጠቀም የተበታተነችውን አገር በቀላሉ መበዝበዝ እንደምትችል ተስፋ አድርጓል።

በ1880ዎቹ አንቶኔሊ ከሮም አዲስ አበባ በመመላለስ አገሩ ምኒልክ ጋር ወዳጃዊ ስምምነት የምታደርግበትን መንገድ ለማመቻቸት ሲጣጣር ከርሟል። የስምምነቱ ዓላማ የነበረው አፄ ዮሐንስ በምኒልክ ላይ ቢዘምቱ ጣሊያን በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ከቀይ ባሕር ዳርቻ እስከ አስመራ ያለውን ግዛት ትወርራለች። የጣሊያን ወረራ የዮሐንስን ኃይል በማዳከም ምኒልክን ይደግፋል። በዚህ ስምምነት





መሠረት ምኒልክ የጣሊያንን ወዳጅነት ለማግኘት በማለም በአፄ ዮሐንስ ሥር የነበረውን የአገሪቱን ግዛት ለጣሊያን አሳልፎ መስጠቱ አልቀረም። አፄ ዮሐንስም የምኒልክ እና የጣሊያንን ሽፍጥ እንዳወቁ ምኒልክን ከጎናቸው ለማድረግ ተንቀሳቀሱ። ለምኒልክ በጻፉትም ደብዳቤ «ኹለታችን በጋራ ከቆምን በእግዚአብሔር እገዛ እናሸንፋለን» በማለት ጥያቄ አቅርበውለት ነበር።

ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ያደረጉት ስምምነት አደገኛ የፖለቲካ ጥልፍልፍ ውስጥ ጨምሯቸው ነበር። አካሄዳቸውን በተደጋጋሚ ሲቃወሙ የነበሩት ባለቤታቸው ጣይቱ ሲኾኑ በዘውድ ም/ቤቱ የሚገኙ የትግራይ አካባቢ ተወላጆችም በምኒልክ አካሄድ ደስተኛ አልነበሩም። ጣይቱ አንቶኔሊን በተደጋጋሚ ፊት በመንሳት ለባለቤታቸው ተቃውሞአቸውን ቢያሳዩም ምኒልክ ግን አፄ ዮሐንስ በሕይወት እስካሉ ድረስ ከአንቶሊም ሆነ ከጣሊያን ጋር መራራቅ አይፈልጉም ነበር። ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ወዳጅነታቸውን በአንድ በኩል በማጥበቅ በሌላ ወገን ደግሞ ከፈረንሳይ ጋር መቀራረብ ጀምረው ነበር። በአልፍሬድ ኢልግ አበረታችነት ለፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ጁሌስ ግሬቪ በጻፉት ደብዳቤም ራሳቸውን የጣሊያን እና የዮሐንስ ግጭት ለመፍታት የሚጥር ገለልተኛ አድርገው ነበር ያስቀመጡት።

ምኒልክ በአፄ ዮሐንስ ላይ በምስጢር ቢያሴርም አገር ወዳድነቱን አሳጣም ነበር። ራሱን ለጣሊያን የጦር መሣሪያ አቅርቦት በሽያጭ እንዳሳቀረበ ኹሉ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ አልሰጠም። ዐፄ ዮሐንስ የምኒልክና የጣሊያንን ሽፍጥ ዮሐንስ ቢያውቁም ለእርምጃ አልቸኮሉም ነበር። ሥልጣናቸውን ላለመቀበል ያንገራገሩትን በመቅጣት የሚታወቁት አፄ ዮሐንስ የጎጃሙን ንጉሥ ተ/ኃይማኖት ዳተኝነት ተገንዝበው የጦሩ መሪያቸው አሉላን ልከውበት ነበር። አሉላም ንጉሡን ለማሳደድ በተራሮች መካከል እንዲሸሽግ አድርጎ አዋርዶታል። በምኒልክ ላይ በ1888 ተመሳሳይ የቅጣት እርምጃ ከመውሰድ ያገዳቸው አንድም የሸዋ ርቀት ሲሆን ሌላው ደግሞ የመሃዲስት ወራሪ ኃይል መቃረብ ነበር።

ዮሐንስ ከመሃዲስት ወራሪ ጋር ለመዋጋት በዝግጅት ላይ ሳሉ አንቶኔሊ ደብዳቤዎችን፣ ስጦታዎችን፣ 4,700 የሬሚንግተን ጠመንጃዎችን እና 220,000 ጥይቶችን ይዞ አዲስ አበባ ደረሰ። በዚያ ወቅት ምኒልክ ከመቶ ሺ አባላት በላይ ያሉት ሠራዊት በመገንባት ኃይሉን ከአፄ ዮሐንስ ጋር አስተካክሉ ነበር። ጣሊያንም ለምኒልክ ልዩ ድጋፍ በማድረግ በቀጠናው ታላቅ ጦር እንዲገነባ አስችላው ነበር።

ምኒልክ የባለቤታቸው ጣይቱ ብጡልን ርስት ለመጎብኘት ውጫሌ ሳሉ ነበር የአፄ ዮሐንስን መሞት የሰሙት። በጉጉት ሲጠብቁት የነበረውን ዜና ተከትሎ ራሳቸውን «ንጉሠ ነገሥት» አድርገው ሾሙ። የምኒልክ እርምጃ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ በዝግጅት ላይ ለነበረው መንገሻ ከፍተኛ ጫና ፈጠረበት። በረጅም ዘመን ታሪኳ ኢትዮጵያ በሰሜን ነገሥታት በተለይም በትግራይ ስትመራ ኖራለች። ምኒልክ ይህንን የረጅም ዘመን ታሪክ በመቀልበስ የአገሪቷን በትረ ሥልጣን ወደ ደቡብ ሲያዞሩ ሰሜናውያኑ በደቡባውያኑ በተለይም በሸዋ ላይ አቄሙ፤ ውስጣቸውም በከፍተኛ ጥላቻ ተሞላ።

ምኒልክ ዘውዱን ወደ ደቡብ ማዞራቸውን ተከትሎ ከተቆረቆረች ዐሥር ዓመት ያልሞላት አዲስ አበባ የአገሪቷ አዲስ ርዕሰ መስተዳድር (መዲና) ሆነች። አፄ ዮሐንስን ለመፎካከር የተገነባው የምኒልክ ጦርም እጅግ ኃያል የነበረ በመኾኑ በአገሪቱ የተለያዩ ግዛቶች የነበሩትን ተቀናቃኞች አደብ ማስገዛት እንደሚችል አረጋገጠ።

የምኒልክ ለዘውድ መቃረብ ያስደሰተው ሌላ ሰው ፔትሮ ኢንቶኔል ነበር። ከመጀመሪያ ጀምሮ በድጋፍ እና ክትትል ያጎለበተው ንጉሥ የአገሪቷ ርዕሰ ብሔር ለመሆን መዘጋጀቱን በመረዳትም ግንኙነቱን በፊርማ ለማረጋገጥ መሯሯጥ ጀመረ።

የአንቶኔሊ የልፋት ውጤት ደግሞ ግንቦት 2 ቀን 1889 ዓ.ም ውጫሌ ላይ የተፈረመው የኹለትዮሽ ስምምነት ነው። ስምምነቱ (አንቀጽ 14) የባሪያ ንግድን





ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት እንዲሁም (አንቀጽ 18) ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር የንግድ ልውውጥ እንድታደርግ ቅድመ ሁኔታን ለመፍጠር ያለመ ነበር።

የስምምነቱ አወዛጋቢ አካል የነበረው በአንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው ቅድመ ሁኔታ ነበር። በአንቀጹ ድንጋጌ መሠረት ኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነቷን በጣሊያን ተወካይነት አማካይነት ለማድረግ የምትገደድ ሲሆን ይህም ማለት ኢትዮጵያ በጣሊያን ሞግዚትነት የምትተዳደር ትሆናለች። በስምምነቱ አንቀጽ 19 ላይ እንደሰፈረው የሰነዱ አማርኛ እና ጣሊያንኛ ቅጂ እኩል ተቀባይነት እንዳላቸው ቢገልጽም በስምምነቱ አማርኛ ቅጂ ላይ አለመግባባት ተፈጠረ። ይህ አለመግባባት ወደ ከፍተኛ ጡዘት ደረጃ ደርሶ በመጨረሻ አድዋ ላይ በጦርነት ተጠናቀቀ።

የጣሊያኑን ንጉሥ ኡምቤርቶ በመወከል ፒየትሮ አንቶኔሊ ከአፄ ምኒልክ ጋር የተፈራረመው የውጫሌ ውል በኹለት ሉዐላዊ አገራት መካከል የተደረገ እኩልነት መገለጫ ነው። ኢትዮጵያ ቀድሞ በአውሮፓ ባገኘችው ዕውቅና የተነሣ ነበር የኹለትዮሽ ስምምነቱን ለመፈረም የበቃችው። የኹለትዮሽ ስምምነቱ በ19ኛው ክፍለዘመን አንድ አውሮፓዊ አገር ከአፍሪካ አገር ጋር ያደረገው የመጀመሪያ ሕጋዊ ስምምነት እና ቀድሞ ያልነበረ ኹነት ነው።

ስምምነቱ በርካታ ነገሮችን አስከትሏል። ስምምነቱ ለምኒልክ ንጉሠ ነገሥትነት ዋስትና መሆን ቻለ። በተጨማሪም ምኒልክ ሥልጣንን በግዛት የለወጡበትም ጭምር ነበር ስምምነቱ። በመኾኑም ከፊርማው በኋላ ጣሊያን ነሐሴ 1889 ላይ ከምፅዋ በመንቀሳቀስ ደጋማውን የኤርትራ ክፍል በመያዝ መቀመጫዋን አስመራ አደረገች። የጣሊያን ወረራ ለመንገሻ የይስሙላ ሥልጣን ፍጻሜን ሲሰጥ ራስ አሉላን ደግሞ በጣም አስቆጥቷል። ጣሊያን በአፄ ዮሐንስ ላይ እንዳደረገችው ኹሉ የመንገሻንም ለሜናዊ ሥልጣን ጥያቄ ውስጥ አስገባችው።

ምኒልክ በበኩላቸው በትረ ሥልጣናቸውን የማረጋገጥ ሥራ ጀመሩ። የተለያዩ የግዛት አስተዳደሮች ላይ የሥጋ ዘመዶቻቸውን በመሾም ተጠሪነታቸውን በቀጥታ ለራሳቸው አደረጉ። የጣይቱ ወንድም ለሆነው ወሌ የራሥነት ማዕረግ በመስጠት ቀድሞ ከነበረው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ግዛት እንዲያስተዳድር ሾሙት። የምኒልክ የአክስት ልጅ የኾኑት መኮንን ደግሞ የሐረር ገዢነታቸው ጸና። በመጨረሻም ከሰሜኖቹ መንገሻ እና ራስ አሉላ በቀር መላው የአገሪቷ ግዛቶች በምኒልክ ታማኞች አስተዳደር ሥር ኾኑ።

በመቀጠል ለውጫሌ ስምምነት ማረጋገጫ ለመስጠት ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ልዑካን ቡድኗን ወደ ሮም ለመላክ ተዘጋጀች። በኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ተልዕኮ እንዲመሩ በምኒልክ የተመረጡት መኮንን ነበሩ።

### የሐረር አስተዳዳሪው መኮንን

ምኒልክ በአርባ አምስት ዓመት ዕድሜያቸው የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዳቸውን ሲጭኑ አብዛኛውን ኃላፊነት በወጣቱ የአጎታቸው ልጅ ራስ መኮንን ጫንቃ ላይ ነበር የጣሉት። የግብፅን መዳከም እና የአፄ ዮሐንስን እና አውሮፓውያን የዶጋሊ ውዝግብ እንደ አጋጣሚ በመጠቀም ነበር 1887 ምኒልክ ጦራቸውን በማዝመት ሐረርን በቁጥጥራቸው ሥር ያዋሉት። ሰር ሪቻርድ በርተን ስለ ሐረር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ሲናገር *«በርባራ ላይ ይዞታ ያለው ኃይል የሐረርን ቁም በእጁ መያዝ ይችላል»* ብሎ ነበር። ምኒልክም የከተማዋን የንግድ ጠቀሜታ እና የባሕር በር መስመርነት ቀድመው በመረዳት ነበር የያዝዋት። ወታደሮቻቸው ከተማዋን በተቆጣጠሩ ማግስት የግዛት አስተዳዳሪነት ሥልጣኑን ለ35 ዓመቱ ራስ መኮንንም ሰጡ።

የሐረር ከተማ ቁመቱ እስከ ዐሥራ አምስት ጫማ በሚደርስ የግንብ አጥር የተከበበች ናት። በዙሪያዋ አምስት በሮች ሲኖሩ ዐሥራ አምስት የጥበቃ ማማዎች አሉ። በወቅቱ የነበረው የከተማዋ የጥበቃ ሥርዓት ከሶማሊያ ጠረፍ በአፋር በርሃ





አቋርጠው ይመጡ የነበሩ ነጋዴዎችን ያስገርም ነበር። አንድ ተጓዥ ነጋዴ ሐረርን «በቸኮሌት የተገነባች» ትመስላለች ብሎ ነበር።

ሐረር በበርካታ ነጋዴዎች ምልልስ የምትደምቅ ከተማ ናት። አብዛኛው ነዋሪ ኦሮሞ ሲሆን ብዙ ቁጥር ያላቸው የአደሬ ተወላጆችም በሐረር ይኖራሉ። ከኹሉቱ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ በተጨማሪ አረብኛ፣ ግሪክ፣ ሂንዲ፣ ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛ እና እንግሊዝኛ በሐረር ይነገሩ ነበር። በዐሥር ሺህ የሚቆጠሩ የከተማይቱ ነዋሪዎች በከተማዋ እምብርት አካባቢ ሰብሰብ ብለው ይኖሩ ነበር። በሐረር የገበያ ማዕከል የማይሸጥ ነገር የለም። የተለያዩ የእዝዕርት ዓይነቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ አትክልት፣ አልባሳት፣ ቡና፣ የቁም ከብት እንደሁም ሥጋ ሳይቀር ለሽያጭ ይቀርቡ ነበር።



Ras Makonnen. From Guèbrè Sellassié, *Chronique du règne de Ménélik II, roi des rois d'Éthiopie*. Paris: Maisonneuve Frères, 1930

***ምስል፦ ራስ መኮንን***



Ras Makonnen. From Guèbrè Sellassié, *Chronique du règne de Ménélik II, roi des rois d'Éthiopie*. Paris: Maisonneuve Frères, 1930.

[redacted]፡- ራስ መኮንን

በርካታ አውሮፓውያን ጎብኚዎች ሐረር ከሰሜን አፍሪካ ከተሞች ጋር እንደምትመሳሰል በተለያዩ ጊዜያት ገልጸዋል። ግብፅ እና ሸዋ ሐረርን ለመያዝ በተለያዩ ጊዜያት ሲፎካከሩ ቆይተዋል። በመጨረሻም ምኒልክ ከተማዋን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው «ይህ የእስላም አገር አይደለም። ኹሉም ይሄንን ይወቅ» በማለት ዐወጁ። በመቀጠልም ራስ መኮንን የከተማዋን ትልቅ መስጊድ አስፈርሰው በጣሊያን የሕንፃ ባለሙያዎች አገዛ ትልቅ ቤተ-ክርስቲያን አስገነቡ፡

ሐረር የጠረፍ ነጋዴዎች መዳረሻ ብቻ ሳትሆን ከፍተኛ ዋጋ ያለው የቡና ገበያም ጭምር ነበረች። ምኒልክ ወደ ደቡብ፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ባደረጉት የመስፋፋት ዘመቻ በግዛታቸው ሥር ካደረጉዋቸው ይዞታዎች መካከል ሐረር እና ወላይታ ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝተውላቸዋል። የኹለቱ ግዛቶች የሐብት መጠን የአድዋውን ዘመቻ ስኬታማ ማድረግ አስችለዋል። ከአዳዲሶቹ ግዛቶች ምኒልክ ከፍተኛ ገቢ መሰብሰብ ችለዋል። በሐረር ልዩ የቀረጥ ሥርዓት በመጣል ከጀመሩት የግብር መሰብሰብ እርምጃ ቀጥሎ በከተማዋ የነበሩ የአውሮፓዊ ነጋዴዎች ብድር እንዲያቀርቡ እስከማስገደድ ደርሰው ነበር። ምኒልክ የተፈለገውን ያህል ገቢ ከሐረር መሰብሰብ ቢችሉም የከተማዋ የንግድ እንቅስቃሴ ለማገገም በርካታ ዓመታት አስፈልጓታል።

የሐረር ገገር በመሆን በምኒልክ የተሾሙት ራስ መኮንን ከተማዋን ከማስተዳደር እና ግብር ከመሰብሰብ የዘለለ ኃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር። ሐረር በመቀመጥ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡትን እንግዶች በመቀበል ወደ ምኒልክ ያስተላልፉ ነበር። በርካታ አገር ጎብኚዎችን እና ዲፕሎማቶችን ይቀበሉ የነበረው ሐረር ከመድረሳቸው በፊት የአንድ ቀን መንገድ ሲቀራቸው ነበር። መኮንን በአግባቡ የታጠቁ ፈረሰኞቻቸውን በመላክ እንግዶችን አሳጅበው እስከ ሐረር ያስመጧቸውም ነበር።





በሐረር ጎላ ብሎ ከሚታየው ባለ ኹለት ፎቅ ሕንፃው ቤተ-መንግሥታቸው ነበር ራስ መኮንን እንግዶችን የሚቀበሉት። እንደ እንግዶቹ ደረጃ የተለያየ የአቀባበል ሥርዓት ቢያደርጉም ራስ መኮንን በመልካም እንግዳ ተቀባይነታቸው ይታወቃሉ። ብዙውን ጊዜ እንግዳ በሚቀበሉበት ወቅት ይለብሱ የነበረው ጥቁር የሐር ሸሚዝ ሲሆን የሸሚዙ ቁልፎች ከወርቅ የተሰሩ ነበሩ።

መልክ መልካሙ ራስ መኮንን እርሞ ሚስታቸውን በሞት ከተነጠቁ በኋላ ድጋሚ አላገቡም። ለሟች ሚስታቸው ያሳዩትን ታማኝነት ለሐረር ከተማ እና ለሕዝቦቿ ያላቸው ታማኝነት ማሳያ እንደነበር ይነገርላቸዋል። በዚያም ነበር በሐረር ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ያገኙት። ብዙ ጊዜ ከቤተ መንግሥታቸው በመውጣት ሕዝቡ መካከል ይዘዋወሩ ነበር። ያለምንም አጃቢ አንድ አስጎብኚያቸውን ብቻ አስከትለው መንቀሳቀሳቸው በሕዝቡ ዘንድ የነበራቸውን ከበሬታ እና ተወዳጅነት ያሳያል።

በርካቶች በራስ መኮንን ምሁራዊ አስተዳዳሪነት እና ጥበበኛነት ይስማማሉ። በርካታ ባላንጣዎቻቸው ሳይቀሩ ይህንኑ ይመሰክራሉ። ሰር ጀምስ ሬኔል ሮድ «የተዋጣለት ዐዋቂ» በማለት ነበር መኮንን ያሞገሳቸው።

ራስ መኮንን በብዙዎቹ ዘንድ የምኒልክ ዘውድ ወራሽ እንደሚኾኑ ቢገመትም በ1906 ነበር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት። በርካታ ባሕርያትና ስብዕናቸውን ለልጃቸው ራስ ተፈሪ አውርሰው ነበር የሞቱት። ወራሽ ልጃቸውም ከአገራቸው አልፈው በበርካታ የአፍሪካ ስደተኞች ዘንድ የራስተፈሪያን ዕምነት እና ፍልስፍና ማዕከል በመሆን ይታወቃሉ። ራስ መኮንን ምኒልክን ተክተው መምራት ባይችሉም ልጃቸው በ1930 ዓ.ም ኃይለሥላሴ በሚል የንግሥና ስም ዘውድ ጭነዋል።

የራስ መኮንን መቀመጫ የሆነችው ሐረር የዲፕሎማቶች መግቢያ በር ብቻ ሳትሆን የባሕል እና ኃይማኖት ማዕከልም ጭምር ነበረች። ከቀይ ባሕር ዳርቻ በተነሳ የእስልምና እና የኢትዮጵያ ደገኞች ዕምነት በሆነው ክርስትና ዕምነት ሥርዓት

የተቀረጸ የአኗኗር ዘይቤዋ፣ የቤት አሠራር እና የአለባበስ ሥርዓቶቿ ሐረርን ከመካከለኛው ምሥራቅ ከተሞች ጋር እንጂ ከየትኛውም የጥቁር አፍሪካ መንደር ጋር አያመሳስላትም።

የንግድ እንቅስቃሴዋ ጫፍ በነካባቸው በ1880ዎቹ ሐረር የበርካታ ፈረንሳዊ፣ ጣሊያናዊ፣ ሕንድ፣ አርመን እና ግሪኮችን ቀልብ ስባ ነበር። በርካቶቹ ከአውሮፓ የተለያዩ አልባሳትን እና የጦር መሣሪያዎችን ለአፍሪካ ገበያ የሚያቀርቡት ሐረርን ማዕከል አድርገውም ነበር። እንደ ፈረንሳዊው ገጣሚ አርተር ራምቦ ያሉ የትልልቅ ኩባንያ ተወካዮችም ሐረርን መቀመጫቸው አድርገው የወጪ እና ገቢ ንግዳቸውን ያከናውኑ ነበር።

ራምቦ በ1880 ለመጀመሪያ ጊዜ ሐረር የመጣው መቀመጫው በኤደን የነበረውን ባርዴ ኩባንያ ወክሎ ነበር። በ1885 ግን ውክልናውን በመተው ለምኒልክ የጦር መሣሪያ ለማቅረብ ወሰነ። ከአውሮፓ ያስመጣቸውን ያገለገሉ የጦር መሣሪያዎች ለምኒልክ አቀረበ። ምኒልክም የመሣሪያውን ዐሥር ከመቶ በአገር ውስጥ ገቢ መልክ ከቆረጡበት በኋላ የቀረውን ለመግዛት ዋጋ ቆረጡለት። ክፍያውን ሐረር ሲደርስ ራስ መኮንን እንደሚፈጽሙለት በመናገር ምኒልክ ሲያሰናብቱት አልተቃወመም ነበር።

ሐረር ደርሶ ክፍያውን ከተቀበለ በኋላ የተረዳው ነገር ቢኖር ለአፍሪካ ነገሥታት እና የጎሳ መሪዎች መሣሪያ ማቅረብ የዋጋ ድርድር ለማድረግ እንደማያስችል ነበር። በመኾኑም በበርካታ ግሪኮች ቁጥጥር ሥር በነበረው የአገር ውስጥ ገበያ በመግባት ለግለሰቦች መሣሪያ ለመቸርቸር ወሰነ።

በወቅቱ አዋጭ የነበረው የባሪያ ንግድ ቢሆን ሐረርም በሸዋ እና በጠረፍ አካባቢ ማዕከል ላይ በመገኘቷ ለባሪያ ንግዱም ማዕከል ነበረች። ከጠረፍ እስከ ሐረር በተዘረጋው የንግድ መስመር ላይ አምስት የንግድ ማዕከላት የነበሩ ቢሆንም ሦስቱ





ብቻ ነበሩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው። እነርሱም በእንግሊዝ ሥር የነበረው ዘይላ እና በፈረንሳይ ቁጥጥር ሥር የነበሩት አቦክ እና ታጁራ ናቸው።

የታጁራ ሰርጥ እና እስከ ሐረር የተዘረጋው የ182 ማይል የንግድ መሥመር በኢብራሒም አቡበከር እና ዐሥራ ኹለት ልጆቹ ቁጥጥር ሥር ነበር። በርካታ አውሮፓዊ የንግድ አጋሮቹን ቡና በመጋበዝ የሚታወቀው አቡበከር የንግድ ቀጠናውን በመቆጣጠሩ ለዕቃ ዋጋ የሚያቀርበው እርሱ ብቻ ነበር። በርካቶች ነጋዴዎች ‹‹ሕጋዊ ዘራፊ›› በሚል ጥቅል ስሙ ይለዩት ነበር። በንግድ መስመሩ ይካሄድ የነበረውን የባሪያ ንግድም ይቆጣጠር የነበረው አቡበከር ነበር። በርካታ አውሮፓውያን እንግዶች ከአቡበከር ጋር በተገናኙበት ወቅት የማይረሷቸው ኹለት መለያዎችን ሲሆን ከእጁ የማይለየውን የመቁጠሪያ ዶቃ(ሙስበሐ) እና በተደጋጋሚ በፊት ጥርሱ ፍንጪት በኩል ምራቁን ‹ጢቅ› ማድረጉን ነበር።

የአቡበከር ጎሳ አባላት ከጠረፍ አካባቢ ስለማይንቀሳቀሱ የሐረሩ ገዢ ራስ መኮንን ከአቡበከር ጋር መልዕክት ይለዋወጡ የነበረው በነጋዴዎች አማካይነት ነበር። በኹለቱም ወገን የነበረው ፍላጎት የንግድ መስመሩ እክል ሳይገጥመው ንግዱ እንዲከናወን ነበር። የአቡበከር ከፍተኛ ገቢ የነበረው ቀይ ባሕርን አሻግሮ በሚልካቸው ባሮች ሲሆን የባሪያ አቅርቦቱም የኢትዮጵያ ደጋማ አካባቢ ነበር። ምኒልክ በሌላ ወገን የንግድ መስመሩ ብቸኛ የመሣሪያ ማስገቢያ እና ወጪ ንግድ ማከናወኛቸው በመኾኑ የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን በማስቆም አቡበከርን ማስከፋት አልፈለጉም ነበር። በመኾኑም ምኒልክ ከአቡበከር ጋር ከመስማማት ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም።

እንግሊዝ በዘይላ እና ሌሎች የቀይ ባሕር ወደቦች ሲካሄድ የነበረውን የመሣሪያ እና የባሪያ ንግድ ስታስቆም የምኒልክ እና የአቡበከር ህልውና በጋራ ትብብር ላይ የተመሠረተ በመኾኑ ኹለቱ ተስማሙ። አቡበከር ከበርካታ ዘረፋ እና ግድያ ጋር ስሙ ቢያያዝም ምኒልክ ወዳጅነታቸውን አላቆሙም ነበር። በ1886 ባራል ሳቮሬ በተባሉ የፈረንሳይ ነጋዴዎች ላይ ግድያ የተፈጸመ ሲሆን ብዙኃን የድርጊቱ

ባለቤት አቡበክር እንደሆነ እና የፈረንሳይ ባሕር ኃይል የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን በመረበሹ የወሰደው የበቀል እርምጃ እንደሆነ ገምተዋል።

አቡበክር ነጋዴ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የግንኙነት መስመርም ነበር። በጠረፍ ካሉ ሶማሊዎች ጋር ብዙ ጊዜውን ቢያሳልፍም የዘር ሐረጉ ከአፋር ጋር በመገናኘቱ ከአፋር የጎሳ መሪዎች ጋርም ጥሩ ግንኙነት ነበረው። በመኾኑም ከታጁራ የሚነሳ ጭነቱን ወደ ሐረር ለማሳለፍ የአፋርን የንግድ መስመር በነጻነት መጠቀም ችሎ ነበር። አቡበክር በ1885 ሲሞት ልጆቹ የንግድ እንቅስቃሴውን ወረሱ። ወደ ሸዋ በርካታ ዕቃ በማስገባት በመልስ ጉዟቸው ደግሞ ወደ አረብ ባሕረሰላጤ የሚያሻግራቸውን ባሪያ ወጣቶች ይዘው ይመለሱ ነበር።

ሐረር ላይ የተቀመጡት ራስ መኮንን ከምኒልክ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት የአገሪቷን ወጪ እና ገቢ ንግድ ይቆጣጠሩ ነበር። ምኒልክም ኾኑ ራስ መኮንን የባሪያ ንግድ እንቅስቃሴውን ለማቆም ፍላጎት ነበራቸው። ይህንን እንዲያደርጉ ያስገደዳቸው የአገሪቱ ዋና የወጪ ንግድ በባሪያ አቅርቦት ላይ የተመሠረተ በመኾኑ ነበር። ከኹሉም በላይ ግን የባሪያ ንግዱን ማቋረጥ የንግድ መስመሩን ባለቤቶች ስለሚያስቀይም ብቸኛውን የባሕር በር እንዳያሳጣቸውም ሰግተው ነበር።

ሪቻርድ ፓንክረስት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚያዊ ታሪክ በዳሰሰበት ሥራው የባሪያ ነጋዴዎች በ1880ዎቹ በየሦስት ወሩ ከሸዋ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ባሪያ ያግዙ እንደነበር ጽፏል። በ1890ዎቹ አጋማሽ ላይ ግን ምኒልክ የባሪያ ንግዱን ለማስቆም ቁርጥ ውሳኔ ላይ በመድረስ በርካታ የባሪያ ገበያዎችን ያፈረሱ ሲሆን የታወቁ የባሪያ ፈንጋዮችን እጅ በማስቆረጥ ቀጥተዋል። በዚያ ሁኔታ የባሪያ ወጪ ንግዱ ቢቆምም በአገር ውስጥ ግን ባሮች በሠርግ፣ በለቅሶ፣ እና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች በስጦታ መልክ ይቀርቡ ነበር። ይህ የስጦታ ሥርዓት እስከ 1903 ድረስ ዘልቋል።





እንደ ነጋዴዎች ኹሉ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ወደ ሐረር እና ሸዋ መግባት የጀመሩት ራስ መኮንን ሐረር ሳሉ ነበር። ሉዊስ ታውሪን የተባሉ የካቶሊክ ቄስ በ1881 ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የሮም ካቶሊካዊ ሚሲዮን የማቋቋም እንቅስቃሴ ጀመሩ። ቄስ ታውሪን የባሪያ ንግዱን በመቃወም ዕድሜያቸው ከ15-30 የነበሩ ወጣት ባሮችን ለመታደግ ከነጋዴዎች ላይ ይገዙ ነበር። የገዟቸውን ወጣቶች ወደ ካቶሊክ በመቀየር ያስተምሩም ነበር። ወጣቶቹም በመቀጠል በተለያዩ የግል ሥራዎች እና የወንጌል ሥርጭት ተግባር ተሰማሩ። ቄስ ታውሪንን የተኳቸው መጋቢ አንድሬ ጃሮሱ በ1884 ወደ ሐረር ያቀኑ ሲሆን ከአምሳ ዓመታት በኋላ በ1930ዎቹም መጋቢው እዛው ነበሩ።

በሐረር ቆይታቸው ራስ መኮንን በርካታ የዲፕሎማሲ ልምድ አካብተዋል። በከተማዋ ይገቡ እና ይወጡ ከነበሩ በርካታ የአውሮፓና አረብ ነጋዴዎች ጋር ያደርጉ የነበረው ውይይት ለዲፕሎማሲያዊ ዕውቀታቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የመኮንንን የላቀ የዲፕሎማሲ ችሎታ የተረዱት አፄ ምኒልክ ወደ ሮም፣ ሴንት ፒተርስበርግ፣ ፓሪስ እና ለንደን ልዑካንን ሲልኩ በመሪነት የመረጡት ራስ መኮንንን ነበር። የፈረንሳዩ ሌ ፒምፕስ ጋዜጣ ራስ መኮንንን በተደጋጋሚ አሞግሶ የጻፈ ሲሆን በኢትዮጵያ መንግሥት ከምኒልክ ቀጥሎ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ እንደኾኑም መስክሮላቸዋል። በአዲስ አበባ እና በመላው አገሪቱ ክፍል የነበሩ ጎበዛዝት የምኒልክ መኮንንን መመረጥ ተከትሎ ቢያጉረመርሙም ቅሉ ምኒልክ የውጫሌን ስምምነት ለማጠቃለል ወደ ሮም መኮንን ለመላክ የወሰኑት ያለምንም ማቅማማት ነበር።

### የራስ መኮንን ተልዕኮ በጣሊያን

በራስ መኮንን የተመራው የኢትዮጵያ የዲፕሎማቶች የልዑካን ቡድን ነሐሴ 27 ቀን 1889 ሮም ሲደርስ ክስተቱ ለአፍሪካ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ድል ነበር። የኢትዮጵያ ልዑካንን የሮም ጉብኝት ልዩ እና አንፀባራቂ የሚያደርገው በጥቁር አፍሪካ

እና በዘመናዊ አውሮፓ መካከል የተደረገ የመጀመሪያው ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት መኾኑ ነው።

የልዑካኑ ጉብኝት የጀርመኑ ኦቶ ቮን ቢስማርክ ከአምስት ዓመታት በፊት በርሊን ላይ በጠራው ስብሰባ የአፍሪካ ቀጣይ ዕጣ ፈንታ በአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች ፍላጎት እንደሚወሰን ለተናገረው ምላሽ የሰጠም ነበር። በ1884 የበርሊን ኮንፈረንስ አንድም የአፍሪካ መንግሥት አልተጋበዘም ነበር። የመኮንን ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮ ለአሳፋሪው የቢስማርክ ንቀት የመጀመሪያውን አፍሪካዊ ምላሽ የሰጠ ሲሆን ቀጣዩ እና ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ምላሽ የተሰጠው ግን በ1896 የአድዋ ጦርነት ነበር።

በመኮንን የተመራው የልዑካን ቡድን በሐምሌ ወር 1889 ከሐረር ሲነሳ ፒየትሮ ኢንቶኔሊ እና ሉዊ ካፑቺም ጉዞውን ተቀላቀሉ። ዘይላ ደርሰው ኮሉምቦ መርከብ ላይ የተሳፈረው የልዑካን ቡድን አስተርጓሚ የነበረውን ዮሴፍ ንጉሴ፣ የኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን ቄስ የኾኑትን ወደልሚካኤልን ጨምሮ አምስት ከፍተኛ ልዑካንን ከዐሥራ ሦስት አጃቢዎቻቸው እና ሐያ አንድ አገልጋዮቻቸው ጋር የያዘ ነበር።

መርከቧ የጣሊያን ንብረት ብትሆንም የተሰቀለባት ሰንደቅ ዓላማ የኢትዮጵያ ነበር። አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ያለው ሰንደቅ መካከሉ ላይ መስቀል የያዘ ባለ ዘውድ የይሁዳ አንበሳ ምስል ነበረው። በመርከቧ ላይ በክብር የተሰቀለው ሰንደቅ የኢትዮጵያን ሉዐላዊነት ለዘመናዊው ዓለም ያሳወቀ የመጀመሪያው ታሪካዊ ኹነት ነበር።

የውጫሌ ስምምነት ጣሊያን የኢትዮጵያ ጠባቂ ወይም ሞግዚታዊ አስተዳደር እንደሆነች አስቀምጧል። በመኾኑም ጣሊያን ያላትን የማስተዳደር ኃይል ለኢትዮጵያ ልዑካን ለማሳየት ተዘጋጅታ ነበር። ልዑካኑን የያዘችው ኮሉምቦ የጣሊያኗ ኔፕልስ ከተማ ከመድረሷ በፊት አቀባበል ያደረገላት የጣሊያን ባሕር ኃይል ነበር። ልዑካኑ





ከስትሮም ቦሊ እስከ ኔፕልስ በባሕር ኃይል ታጅበው በመጓዝ ነሐሴ 21 ቀን የኔፕልስን መሬት ረገጡ። ግማሽ ሚሊዮን ነዋሪዎች ያሏት ኔፕልስ የሚላንን ያህል ትልቅ ባትሆንም የጣሊያንን የቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ የሚያቀነቅነው የItalian Geographical Society መቀመጫ በመሆኗ ነበር የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እንዲጎበኟት የተደረገው።

ልዑካኑን በርካታ ዲፕሎማቶች፣ ባለሥልጣናት እና የጦር ሠራዊት አባላት የተቀበሏቸው ሲሆን ለክብራቸውም መድፍ ተተኩሶላቸዋል። እንግዶቹ በተዘጋጀላቸው ልዩ ባቡር ሆነው ቡቶሌዶ በኩል አድርገው ወደ ካፓዲሞንቴ ቤተ-መንግሥት አመሩ። ቤተ-መንግሥቱ የኢትዮጵያውያኑን ቀልብ ለመሳብ ሲባል ልዩ እድሳት ተደርጎለታል። በቤተ-መንግሥቱ ለእንግዶቹ ቡቲ የኾኑ መኝታ ክፍሎች የተዘጋጁ ቢሆንም አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ከቤት ውጪ ማደርን ነበር የመረጡት። ውስጥ ያደሩትም ቢኾኑ ጠመንጃ እና ጎራዴያቸውን ከጎናቸው አድርገው ነበር።



The Ethiopian diplomatic mission to Italy, 1889. From SAI Archive at the University of Naples "L'Orientale". Silvana Palma, *Archivio storico della Società africana d'Italia.* [illegible] Napoli, Istituto Universitario Orientale, 1997.

***ምስል፡- የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ልዑካን በጣሊያን (1889)***



The Ethiopian diplomatic mission to Italy, 1889. From SAI Archive at the University of Naples "L'Orientale"; Silvana Palma, *Archivio storico della Società africana d'Italia; fondo fotografico e cartografico.* Naples: Istituto Universitario Orientale, 1997.

ምስል፡- የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ልዑካን በጣሊያን (1889)

በኔፕልስ ቆይታቸው ወቅት መኮንን እና ልዑካኑ በሳንካርሎ ቲያትር ኦፔራ ተጋብዘዋል። ወደ ካሴርታ በመሄድም የባርበን መዝናኛ የነበረውን ያማረ ቤተ-መንግሥት ጎበኙ። የአንድ ሳምንት የኔፕልስ እና ካምፓንያ ቆይታቸውን ጨርሰው ነሐሴ 27 ቀን 1889 በባቡር ወደ ሮም አመሩ።

የኢትዮጵያ ልዑካን ጣሊያን በደረሱበት ተመሳሳይ ወቅት ምፅዋ የነበረው የጣሊያን ጦር ወደ አስመራ ተንቀሳቀሰ። ለአፄ ምኒልክ ስለ እንቅስቃሴው በተጻፈ ደብዳቤ ሠራዊቱ የምፅዋን ሞቃት አየር መላመድ ባለመቻሉ ወደ ቀዝቃዛዋ አስመራ እንደተንቀሳቀሰ ነበር የተገለጸላቸው። የወታደሩ እንቅስቃሴ ከራስ መኮንን ጉብኝት ጋር እንዲገጣጠም የተደረገው የኢትዮጵያ እና ጣሊያን ወዳጅነት መጠናከሩን ለማሳየት ነበር።

የጣሊያን ሠራዊት ወደ አስመራ መንቀሳቀስ በአገረ ጣሊያን ሕዝብ ዘንድ ተቃውሞ አሥነስቶ ነበር። የቫቲካንን ጋዜጣ ጨምሮ በርካታ የኅትመት ውጤቶች የጣሊያንን መንግሥት ወረራ በመቃወም ላይ ነበሩ። የመንግሥት ልሳን እንደሆነ የሚታወቀው ትሪቡና ጋዜጣ «የቅኝ ግዛት ወረራ ድርጊት» በማለት ጽፎ የአስመራን መወረር ተቃውሟል።

የልዑካን ቡድኑ ሮም የደረሰው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ነበር። በርካታ ጣሊያናውያን በአገራቸው መንግሥት የቅኝ ግዛት አካሄድ ለመቃወም የኢትዮጵያ ልዑካንን መምጣት በመጠባበቅ ላይ ነበሩ። በርካታ ቁጥር ያላቸው ጣሊያናውያን ደግሞ የዶጋሊውን ጭፍጨፋ በማስታወስ ለተቃውሞ ወጥተዋል።

ራስ መኮንን ከባቡር ሲወርዱ የተቀበሏቸው ጀነራል ኤሚሊዮ ፓላቪቺኒ እና ሌሎች የመንግሥት ተወካዮች ነበሩ። ከባቡር ጣቢያው ዙሪያ በርካታ ተቃዋሚዎች የተሰበሰቡ ሲሆን እነርሱን ለመበተን የመጣ በርካታ የፖሊስ ሠራዊትም ተሰልፎ





ነበረ። የተቃውሞ ግርግሩ እስኪበተን ድረስ የኢትዮጵያ ልዑካን በአንድ ፋርጎ ውስጥ እንዲቀመጡ ተደረገ። የወቅቱን ተቃውሞ በርካታ የጣሊያን ጋዜጦች «ኃላፊነት የጎደለው» እንዲሁም «ያልተገባ» በማለት ገልጸውታል።

ተቃዋሚዎች ከተበተኑ በኋላ ኢትዮጵያውያኑ በልዩ ጥበቃ ሥር ሆነው ወደ ቪላ ሚራፊዮሪ ተወሰዱ። በቪላው የነበረው መስተንግዶ እጅግ የተሟላ ነበር። በኢትዮጵያ ባህል መሰረት ለእርድ የተዘጋጁ በግ እና በሬ ነበሩ። የምግብ አልፍኙ በኢትዮጵያ ወግ መሠረት እንስተኛ በጠረጴዛ እና ከፍ ባሉ ወንበሮች ተዘጋጅቷል።

በኹለተኛው ቀን አመሻሽ ላይ ልዑካኑ ከተማዋን ጎበኙ። ራስ መኮንን የቪክቶር ኢማኑኤል ዳግማዊን መቃብር በመጎብኘት ፊርማቸውን አስቀመጡ። በባቡር ጣቢያው የተፈጠረው ግርግር እንዳይደገም በማሰብ በጉብኝቱ ወቅት ጠንካራ የደኅንነት ጥበቃ ተደርጎ ነበር።

### «የግርማዊነትዎ ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ»

የራስ መኮንን ዋና ተልዕኮ የጀመረው ነሐሴ 29 ነበር። በዕለቱ በከፍተኛ ወታደራዊ ሰልፍ የታጀበው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ ወደነበሩበት ኲሪናል ቤተ-መንግሥት አመራ።

የንጉሡ ማረፊያ ክፍል ሲደርሱ የተቀበሏቸው ንጉሡ ብቻ አልነበሩም። ጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንሴስኮ ክሪስፒን ጨምሮ ኹሉም ሚኒስትሮች፣ የጦር ሠራዊት ጀነራሎች እና የግዛት አስተዳዳሪዎች ተገኝተዋል። ለበርካታ ዓመታት የጣሊያንን እና የምኒልክን ግንኙነት ሲያጠናክሩ የነበሩ የጣሊያን ልዑካን - ፒየትሮ አንቶኔሊ፣ አጉስታ ሳሊምቤኒ፣ ሴዛር ኔራዚኒ፣ ሉዒ ካፑቺ እና ሊዮፓልዶ ትራቬርሲ - ከንጉሥ ኡምቤርቶ አጠገብ ቆመዋል።

በኢትዮጵያ ንጉሣውያን ሥርዓት እና ወግ መሠረት ራስ መኮንን ከንጉሥ ኡምቤርቶ ፊት በማጎንበስ ሰላምታ አቀረቡ። ሰላምታው ተጠናቅቆ በታቸውን እንደያዙ ንጉሡ በጨዋ ደንብ ስለ ጉዟቸው እና ስላጋጠማቸው ነገሮች ጠየቋቸው።



Umberto receives the Ethiopian diplomatic mission. From L'Illustrazione italiana, 1889. Widener Library, Harvard College Library, [illegible]

*ምስል፦ የጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችን በቤተ-መንግሥታቸው ሲቀበሉ*

ዋናው ውይይት የተጀመረው በከፍተኛ ጥንቃቄ የተመረጡ ቃላትን በመጠቀም ነበር። የመጀመሪያው ተናጋሪ የነበሩት ራስ መኮንን ሲኾኑ በአስተርጓሚያቸው ዮሴፍ ንጉሤ አማካይነት የአፄ ምኒልክን መልዕክት አስተላለፉ። *«የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ ለኹለቱ አገራት የጋራ ጥቅም ሲባል ከአገርዎ የገባድ ስምምነት ማድረጋን ይገልጻሉ»* በማለት ነበር ራስ መኮንን መልዕክቱን ማስተላለፍ የጀመሩት። በመቀጠልም፦ *«ለኢትዮጵያ እና በዙሪያዋ ለሚገኙ የጣሊያን ይዞታዎች ሰላም እና ደኅንነት ሲባል የግርማዊነትዎ ጥበቃ እንዲደረግልኝ እጠይቃለሁ»* የሚለውን የአፄ ምኒልክ መልዕክት ቃል በቃል አቀረቡ። በወቅቱ በቦታው ተገኝተው የመኮንንን ንግግር ያዳመጡ ሰዎች ሊረዱ የሚችሉት ነገር ግልጽ ሲሆን ይኸውም ራስ መኮንን በምኒልክ ስም የጣሊያንን ጥበቃ መጠየቃቸው ነው።






ንጉሥ ኡምቤርቶም በምላሻቸው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል። *«መልዕክትህን ተቀብያለሁ። ለኹለቱ አገራት የጋራ ጥቅም ሲባል የተገባውን ስምምነት ለማክበር ቃል እገባለሁ። በጠየቃችሁኝ መሠረትም እኔና መንግስቴ ለአገራችሁ ጥበቃ ለማድረግ ቃል እንገባለን።»*

ራስ መኮንን በሕጋዊነት ሊያጸድቁት ወደ ጣሊያን የተጓዙበት የውጫሌ ስምምነት ኢትዮጵያን በጣሊያን ጥበቃ ሥር ለማድረግ ያስማማ እንደሆነ ጣሊያኖች ያቀርባሉ። በስምምነቱ ሰነዱ ውስጥ «ጥበቃ» ወይም «የሞግዚት አስተዳደር» የሚሉ ቃላት ባይጠቀሱም የራስ መኮንን ተማፅኖ እና የንጉሥ ኡምቤርቶ ምላሽ ብቻውን የጣሊያንን «የጥበቃ» መብት ያረጋገጠ ነበር። የመኮንን እና የንጉሡ ውይይት ቃል በቃል በጋዜጦች የወጣ ሲሆን በዚያ ወቅት ጣሊያን የነበሩት የኢትዮጵያ ልዑካን ማስተባበል ይችሉ ነበር። በውይይቱ የተፈጠሩ አለመግባባቶች ከነበሩም ራስ መኮንን ምላሽ ለመስጠት እና ለማስተባበል በቂ ዕድል ነበራቸው።

ይህ የማጭበርበሩ አንድ አካል ነበር? ታሪኩ ገና መጀመሩ ነበር።

የኡምቤርቶ እና የመኮንንን የጋራ መግለጫ በመስማት ውይይቱ ተጠናቀቀ። በመቀጠል ከአፄ ምኒልክ የተላኩ ስጦታዎችን ልዑካኑ ለንጉሡ አቀረቡ። ስጦታዎቹም በወርቅ ያጌጠ ጦር እና ጋሻ፣ አምስት የአርሞ የፈረስ ኮርቻ፣ ነጋሪት፣ ኹለት ገንቦ ጠጅ፣ ሠላሳ ትልልቅ የዝሆን ጥርስ እና አንዲት የዝሆን ግልገል ከነሕይወቷ ነበሩ።

ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮው ሲጠናቀቅ ልዑካኑ ጉብኝት ማድረግ ቀጠሉ። ላ ስፔዚያ፣ ሞንዛ፣ ቱሪን፣ ቦሎኛ፣ ሚላን፣ ሞዴና እና ቬኒስን በማስጎብኘት የጣሊያን መንግሥት በኢትዮጵያ ጥበቃ ማድረግ እንደሚችል ለልዑካኑ አሳየ። ንጉሥ ኡምቤርቶ እና ባለቤታቸው ንግሥት ማርጋሪታ ልዑካኑን ሞንዛ በሚገኘው ቤተ-



Umberto receives the Ethiopian diplomatic mission. From *L'Illustrazione Italiana*, 1889. Widener Library, Harvard College Library, ICAFoig.

ምስል፡- የጣሊያን ንጉሥ ኡምቤርቶ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶችን በቤተ መንግሥታቸው ሲቀበሉ

መንግስታቸው ጋበዙ። በጉብኝቱ እጅግ የተደሰቱት ራስ መኮንን የቱሪን ከተማን «መንግሥተ-ሰማያት» በማለት ሲያሞግሱ የኮሞን ሐይቅ ደግሞ «ማንም ከዚህ መሄድ አይፈልግም» በማለት አድንቀው ተናግረዋል።

የራስ መኮንን ልዑካን መስከረም 19 ቀን ወደ ሮም በመመለስ የውጫሌ ስምምነት ላይ ስለሚገቡ ተጨማሪ ነጥቦች ከጣሊያን መንግሥት ጋር ተወያዩ። ጥቅምት 1 ቀን ኔፕልስ ላይ በተደረገ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት ተጨማሪ ነጥቦቹ ሕጋዊ ኾኑ። በአዲሱ ማስተካከያ መሠረት ጣሊያን የያዘቻቸው የኢትዮጵያ ግዛቶች በጊዜያዊነት የራሷ እንዲኾኑ ተደነገገ። ስምምነቱ በክረምቱ ወራት ጣሊያን የያዘችው መሬት ማለትም አስመራን ጨምሮ ከመረብ ወንዝ ባሻገር ያለውን የኢትዮጵያ ግዛት ለጣሊያን አሳልፎ የሰጠ፣ ያፈጠጠ የመሬት ወረራ ነበር።

በተጨማሪ ነጥቦቹ ማስተካከያ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያ ከጣሊያን ላይ የ4 ሚሊዮን ሊሬ ብድር የምታገኝ ሲሆን ግማሹ በፊርማው ወቅት ለኢትዮጵያ የሚሰጥ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ኢትዮጵያ ከጣሊያን ለምትገዛቸው ቁሳቁሶች የሚከፈል ይሆናል። የብድር ስምምነቱ የጣሊያንን ምርቶች ለኢትዮጵያ ለመሸጥ ያመቻቸ ሲሆን ለኢትዮጵያ ግን ሌላ አጣብቂኝ ፈጥሮባታል። ይኸውም ብድሩን ለመክፈል ራስ መኮንን ያቀረቡት አማራጭ የሐረር ከተማን የቀረጥ ገቢ ነበር። በመኾኑም በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ኢትዮጵያ ብድሩን ባትከፍል ጣሊያን ሐረርን በመያዝ ብድሯን እስክታስመልስ ድረስ የሐረርን የንግድ ገቢ ትቆጣጠራለች።

በስምምነቱ የተጨመሩት ማስተካከያዎች ለጣሊያን ተስማሚ ቢኾኑም ለኢትዮጵያ ግን አደገኛ ነበሩ። በወቅቱ ኢትዮጵያ ስምምነቱን ለመፈረም አስገዳጅ አጣብቂኝ ውስጥ ነበረች። አገሪቷ በዙሪያዋ ከሚያንዣብቡ አውሮፓውያን ሉዓላዊነቷን ለመጠበቅ በመታገል ላይ ነበረች። ከዚያም በላይ ደግሞ ባጋጠማት ድርቅ የተነሣ የእርሻ ምርቷ የተጎዳ ሲሆን የገንዘብ እጥረትም አጋጥሟት ነበር። በዚያ የተነሣም





ኢትዮጵያ ከጣሊያን ብድሩን በመውሰድ በምላሹ ጣሊያን ኤርትራን እንድታስተዳድር ዕውቅና ሰጠች።

ስምምነቱ ከጊዜ በኋላ ጣሊያን እና ኢትዮጵያን ያወዛገበ ቢሆንም ምኒልክም ኾኑ ራስ መኮንን ለጣሊያን ዕውቅና በመስጠት አስመራን እንድታስተዳድር ሲፈቅዱ ቦጎስ፣ ሃማሴን፣ እና አካለ ጉዛይንም ጭምር አሳልፈው ሰጥተዋል። በብድር ስምምነቱ መሠረት ጣሊያን ሐረርን ለመያዝ የሚያስችላትን መብትም አግኝታለች።

# ምዕራፍ ሰባት

## ‹‹ለአገሬ ውርደት››

የጣሊያን አካሄድ የተለሳለሰ ቢመስልም ችግር ማስከተሉ አልቀረም ነበር። ‹‹ለአገሬ ውርደት የሆነ ተግባር እንደሆነ ደርሼበታለሁ›› አፄ ምኒልክ ለጣሊያኑ ንጉሥ ኡምቤርቶ መስከረም 27 ቀን 1890 በጻፉት ደብዳቤ የጠቀሱት ነበር። ይህ ደብዳቤ የተጻፈው ከራስ መኮንን የዲፕሎማቶች ቡድን የጣሊያን ጉዞ አንድ ዓመት በኋላ ነበር።

ከደብዳቤው አንድ ዓመት በፊት በወርኃ ጥቅምት ምኒልክ ‹ንጉሠ ነገሥት›› ሆነው በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን በአቡነ ማቴዎስ ተቀቡ። በመቀጠልም ንግሥናቸውን ለማሳወቅ ለበርካታ የአውሮፓ መንግሥታት ደብዳቤ ፃፉ። እንግሊዝና ጀርመን በጥቅምት 1890 ለምኒልክ በጻፉት ምላሽ ኢትዮጵያ በሞግዚት አስተዳዳሪዋ ጣሊያን በኩል ከኹለቱ አገራት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቷን ማድረግ እንደሚኖርባት አቋማቸውን አሳወቁ።

የኹለቱ አገራት ምላሽ በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጣን አሥነሣ። ለመኾኑ ኢትዮጵያ በሞግዚት አስተዳደሩ ተስማምታለች? ይህ ጥያቄ የውጫሌ ስምምነትን ትርጓሜ ለመከለስ መንገድ ከፍቷል። ስምምነቱ በአማርኛ እና ጣሊያንኛ የተረቀቀ ሲሆን የስምምነቱ 17ኛው አንቀጽ በኹለቱ ቋንቋዎች የተለያየ ትርጉም ነበረው። አፄ ምኒልክ ለንጉሥ ኡምቤርቶ በጻፉት የተቃውሞ ደብዳቤ እንደገለጹት የጣሊያንኛው ቅጂ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት ጋር ግንኙነት ማድረግ የምትችለው በጣሊያን መንግሥት አማካይነት እንደሆነ የሚደነግግ ሲሆን፤ የአማርኛው ቅጂ ግን ኢትዮጵያ ‹ከፈለገች› በጣሊያን በኩል ግንኙነት የማድረግ አማራጭ እንዳላት መጥቀሱን አስታውሰው ነበር። የእንግሊዝና ጀርመን ምላሽ በጣሊያን በኩል ለኢትዮጵያ ሲላክ ኹሉም ነገር ግልጽ ሆነ።





ብዥታው የታሰበበት ነበር? ለአድዋ ጦርነት መነሻ የሆነው የአንቀጽ 17 የትርጉም ስሕተት ወይም ‹‹የትርጉም መለወጥ›› ሴራ እንደሆነ ግልጽ ነው። በእርግጥ ስምምነቱ በግልጽ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን ‹‹የሞግዚት አስተዳደር›› የሚል ቃል በየትኛውም አንቀጽ ውስጥ አልተጠቀሰም። ቃሉን የፈጠረው በአንቀጽ 17 የሰፈረው የቋንቋ አጠቃቀም ነበር።

የአንቀጽ 17ቱን የትርጉም ብዥታ አፄ ምኒልክ ቀድመው አልተረዱትም ለማለት ያስቸግራል። ምኒልክ የጀርመን እና እንግሊዝ ምላሽ በጣሊያን በኩል የደረሳቸው ስምምነቱን ከፈረሙ ከአንድ ዓመት በኋላ ነበር። የተቃውሞ ድምጽ ማሰማት የጀመሩትም ዘግይተው በመኾኑ ስለ አንቀጹ የትርጉም ስሕተት ሳያውቁ ያን ያህል መቆየታቸውን መቀበል ያስቸግራል።

ራስ መኮንን ስምምነቱን ሕጋዊ ለማድረግ በ1889 ክረምት ወደ ጣሊያን ባመሩበት ወቅት ‹‹የሞግዚት አስተዳደር (Protettorato)›› የሚለው ቃል በበርካታ የጣሊያን ጋዜጦች የፊት ገጽ ላይ ሰፍሮ ነበር። የራስ መኮንን የልዑካን ቡድን በጣሊያን ለበርካታ ሳምንታት በቆዩበት ወቅት የተፈጠረውን ግርታ ማጥራት ይችሉ ነበር። ራስ መኮንን እና ንጉሥ ኡምቤርቶ ተገናኝተው ሲነጋገሩም ‹‹የሞግዚት›› ግንኙነት ላይ አተኩረው ነበር። ራስ መኮንን ‹‹በንጉሠ ነገሥቴ ስም የእርስዎን ጥበቃ እጠይቃለሁ›› በማለት ሳቀረቡት የጥበቃ - ‹‹ሞግዚትነት›› - ጥያቄ ንጉሡ ኡምቤርቶ ሲመልሱ ፦ ‹‹ለአገርዎ ጥበቃ ለማድረግ በራሴ እና በመንግሥቴ ስም ቃል እገባለሁ።›› ብለው ነበር።

ራስ መኮንን በቀላሉ የሚታለሉ ዓይነት ሰው አይደሉም። በምኒልክ ቤተ-መንግሥት አካባቢ ራስ መኮንን ታማኝ እንዳልኾኑ የሚጠቅሱ መሳፍንት እና ኀበዛዝት ነበሩ። በምኒልክ እና ‹‹ወንድሜ›› በሚሏቸው ራስ መኮንን መካከል የነበረውን ወዳጅነት ስንመለከት ራስ መኮንን በምኒልክ ላይ ክሕደት ይፈጽማሉ ማለት

አስቸጋሪ ነው። ራስ መኮንን በአዲስ አበባ እና ሮም ኹለት የተለያዩ ቃላት ተናግረው ይሆን? በዘመናዊው የጋዜጦች ታሪክ አንድ ዘገባ በኹለቱም አገራት ሊገኝ እና ሊነበብ መቻሉን ስናስብ ራስ መኮንን ምኒልክን ለመክዳት ሮም ሳሉ «ሞግዚት» የሚለውን ቃል ለመጠቀም የሚያሳስታቸው አይመስልም።

በሌላ በኩል የአንቀጽ 17ቱን የትርጉም ስሕተት ምኒልክ ሊጠቀሙበት አስበው በስሌት ተንቀሳቅሰውም ሊሆን ይችላል። በመኾኑም ራስ መኮንንን ወደ ሮም በመላክ ስምምነቱን ሕጋዊ በማድረግ እና የአራት ሚሊዮን ሊሬ ብድር ተቀብለው እንዲመጡ በማድረግ ከጣሊያን ጋር ወዳጅነታቸውን ወደ ላቀ ደረጃ አሸጋገሩ። ከአንድ ዓመት በኋላ ሥልጣናቸውን አማክለው ኢትዮጵያን መግዛት ሲችሉ አፄ ምኒልክ ለዘውድ ካበቃቻቸው ወዳጃቸው ጣሊያን ተፅዕኖ ነፃ ለመሆን መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ምኒልክ ተቃውሞአቸውን እንደተበደለ ወዳጅ በለስላሳ ቃላት ነበር ለጣሊያን ማሰማት የጀመሩት። በወቅቱ የዘውድ ተቀናቃኛቸው የነበረውን ራስ መንገሻ ሙሉ በሙሉ እስኪያስወግዱ ድረስ ጣሊያንን ማስቀየም አልፈለጉም ነበር። ለዚህ ደግሞ ዋናው ምክንያታቸው የነበረው ጣሊያን በምፅዋ በኩል ለመንገሻ የጦር መሣሪያ እንዳታቀብል ማድረግ ነበር። ኃይላቸውን አጠናክረው መጪውን ለመቀበል ዝግጁ እስኪኾኑ ለአንድ ዓመት ያህል የውጫሌን ስምምነት ከመቃወም ታቀቡ።

በአፍሪካ የጣሊያን የጦር መሪ የነበረው አንቶኒዮ ባልዲሴራ የምኒልክን ስሌት ቀድሞ ነበር የተረዳው። አገሩ ጣሊያን አፄ ዮሐንስን ለማዳከም የምኒልክን ጉልበት ማፈርጠሟ ትክክል መኾኑን ነገር ግን የጣሊያንን ፍላጎት በኢትዮጵያ በዘላቂ ለማስፈጸም ሚዛን የሚያስጠብቅላት እና የምኒልክ ተፎካካሪ የሆነ ኃይል ማዘጋጀት እንዳለባት ነበር ሲናገር የቆየው።

የምኒልክ የረጅም ጊዜ ወዳጅ የነበረው ፒየትሮ አንቶኔሊ በበኩሉ የምኒልክ ሥልጣን መያዝ ለጣሊያን ጠቀሜታ እንደነበረው ያምን ነበር። ጣሊያን ስትደግፈው የነበረው ምኒልክ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ በቀላሉ የምትፈልገውን ነገር ለማስፈጸም እንደምትችል ፒየትሮ ያምናል።





ባልዲሴራ የተለየ አመለካከት ነበረው። ምኒልክ ጣሊያንን በፒየትሮ አንቶኔሊ በኩል እንዳታለሏት በመግለጽ አንዴ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ ጣሊያንን ወደጎን እንደሚገፉት ተናገረ። በመኾኑም ጣሊያን በአንቀጽ 17 ላይ ስለተፈጠረው የትርጉም ስሕተት በማስረዳት ጊዜዎን ከምታጠፋ ይልቅ ምኒልክን የሚያዳክምላት የውስጥ ወዳጅ ማዘጋጀት ይበጃታል። ለዚህም የዮሐንስ ልጅ መንገሻ ጥሩ የጣሊያን ምርጫ ይሆናል። የባልዲሴራ ዕምነት የሮማውያን ዘመን መስፋፋት መርህ «ከፋፍለህ ውረር» Divide et impera ዓይነት ነበር።

የባልዲሴራ አማራጭ ተቀባይነት አላገኘም ነበር። ጣሊያን ለበርካታ ዓመታት የሸዋውን ምኒልክ ስትረዳ ቆይታለች። ከራስ መንገሻ ጋር በመመሳጠር ምኒልክን ለማዳከም መሞከር በጣሊያን ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም። ምክንያቱም ከመንገሻ ጋር ለመመሳጠር ጣሊያን ከጦር መሪው ራስ አሉላ ጋር በጋራ መሥራት ይኖርበታል። የዶጋሊውን ጭፍጨፋ በመመልከትም ከአሉላ ጋር መሥራት ጣሊያንን ከፍተኛ የፖለቲካ አጣብቂኝ ውስጥ ይከታታል። ባጋጠመው ከፍተኛ ውጥረት የተነሣ በመጨረሻም ባልዲሴራ በገዛ ፍቃዱ ሥራውን ለቀቀ።

## የኤርትራ አፈጣጠር

በባልዴሴራ የተመራው የጣሊያን ሠራዊት በነሐሴ 1889 ያለምንም የተኩስ ድምፅ አስመራን በቁጥጥር ሥር አዋለ። በምሥራቅ አፍሪካ ታሪክ የተለየ ክስተት ከመፈጠሩ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ በወርኃ ታኅሳስ ጣሊያን ኤርትራን በቅኝ ግዛቷ ሥር ማድረጓን አስታወቀች። «ኤሪትሮስ» የሚለው የግሪክ ቃል በመጠቀምም ለግዛቱ «ኤርትራ» የሚል ስያሜ ሰጠች። የቃሉ ትርጉም «ቀይ» ማለት ሲሆን ቀይ ባሕርን የሚወክል ነበር። ቃሉ የመካከለኛው ዘመን የሮማውያን ኃያልነት የሚያስታውስ ሲሆን አዲሲቷ ቅኝ ግዛት ኤርትራም የሮማውያን መነሣት እና ሕዳሴ ማሳያ ሆነች።

ባልዲሴራን በመተካት አስመራ የተቀመጠው ጀነራል ባልዴሴራ ኦሬሮ ለአፄ ምኒልክ እና ለኢትዮጵያ ወዳጅነቱን ለማሳየት መጣጣር የጀመረው ገና ከጅምሩ ነበር። ጥያቄው ግን «ምኒልክ የኦሬሮን ወዳጅነት ይፈልጉ ነበር?» የሚለው ነው። የምኒልክን ልብ ለማግኘት ይጣጣር የነበረው ኦሬሮ ወዳልተረጋጋው የትግራይ ግዛት በመዝመት ቀጠናውን አረጋግቶ ምኒልክን ለማስደሰት ዐቀደ። ለሮም በጻፈው

ደብዳቤም ወደ ትግራይ በመዝመት የዮሐንስ መቀመጫ የነበረችውን አድዋ ተቆጣጥሮ ምኒልክን ሊጠብቃቸው ማሰቡን ገለጸ። ዕቅዱ የጣሊያንን ዐቅም እና ወዳጅነት ለምኒልክ ለማሳየት እንደሚያስችል ገምቶ ነበር። እንደታቀደው ከተሳካም ምኒልክ ቢታሪካዊቷ ቅድስት ከተማ አክሱም ዘውዳቸውን የሚጭኑ ይሆናል።

ሮም ለጀነራሉ በጻፈችው ምላሽ ኤርትራ ላይ ምሽጉን እንዲያጠናክር ብትገልጽም ጀነራሉ ኤርትራን ለመከላከል የተሻለው አማራጭ ትግራይን መያዝ እንደሆነ ለሮም በጻፈው ምላሽ አሳወቀ። በዚያ ጊዜ ነበር አንቶኔሊ ለበርካታ ዓመታት ምኒልክን በማለሳለስ የገነባው ወዳጅነት አደጋ ላይ ሊወድቅ መኾኑን የተረዳው። በዚያው ፍጥነት ጀነራሉ እንዳቀደው ወደ ትግራይ የሚዘምት ከሆነ ሥራውን በፍቃዱ ሊለቅ እንደሚችልም አንቶኔሊ ተናገረ። ነገር ግን ጀነራል አሬሮን ያስቆመው አልነበረም። የሚቀጥለው የአሬሮ ደብዳቤ ለሮም የተጻፈው ጥር 26 ቀን 1890 ከአድዋ ከተማ ነበር።

ጣሊያን የኤርትራ ቅኝ ግዛት መፈጠሯን ባወጀች በአንደኛው ወር የአሬሮ ወደ አድዋ መዝመት አደገኛ ውጥረት ፈጠረ። መሳው ኢትዮጵያዊ ዜጋ የጣሊያንን የመስፋፋት እንቅስቃሴ አውቋል። አፄ ምኒልክ ለጣሊያን ያሳዩትን መለሳለስም መቃወም ጀምሯል። አፄ ምኒልክ በጣሊያን ኹለንተናዊ ድጋፍ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ ቢችሉም በመጨረሻ የጣሊያን ጉዳይ አስፈጻሚ መሆናቸውን አልተቀበሉም። አሬሮ እንዳቀደው ወደ አክሱም በማምራት የንግሥና ሥርዓታቸውን በጀነራሉ ድጋፍ ቢፈጽሙ ኖሮ ከሕዝባቸው ሊነሳባቸው የሚችለውን ተቃውሞ ገምተዋል። በመኾኑም ወደ ትግራይ በመሄድ ከጣሊያን ሠራዊት ጋር የመገናኘት ዕቅዱን አነሱ።





አፄ ምኒልክ የጣሊያንን ስሌት በሌላ መንገድ ለመጠቀም ወሰኑ። የአሬሮ ሠራዊት ትግራይን በማረጋጋት እና ራስ መንገሻን በማስፈራራት ቢረዳቸው መልካም መኾኑን በማስላት ከጣሊያን ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሰሱ ለመያዝ መጠንቀቅን መረጡ። በመኾኑም የጀነራል አሬሮን ሠራዊት ለመገናኘት በሚመስል መንገድ ወደ ትግራይ ጉዞ ጀመሩ። በዝግታ ያደረጉት የትግራይ ጉዞ በእንዳርታ በኩል ነበር ያለፈው። በአንዳንድ የትግራይ አካባቢዎች ወታደሮቻቸውን ሳለመቀለብ ከተቃወሙ የትግራይ ገበሬዎች መጠነኛ ተቃውሞ ያጋጠማቸው ምኒልክ በተደጋጋሚ የወሰዱት እርምጃ የማያዳግም ነበር። በተቃዋሚ ገበሬዎች ላይ የወሰዱት እርምጃም ለመንገሻ የሚፈልጉትን መልዕክት አስተላልፎላቸዋል።



ምስል፦ ኦሬስቴ ባራቴሪ

ራስ መንገሻ ከደቡብ አቅጣጫ በመገስገስ ላይ ባለው የምኒልክ ሠራዊት እና ከሰሜን እየተጠጋው በነበረው የጣሊያን ጦር መካከል መኾኑን ዐወቀ። ለመዋጋት ቢሞክር የሚያጋጥመውን አደጋ በመገመትም እጁን ለመስጠት ወሰነ። በ300 ወታደሮቹ ታጅቦ ወደ ትግራይ በመገስገስ ላይ ወደነበሩት አፄ ምኒልክ በመሄድም ድንጋይ ተሸክሞ እጁን ሰጠ። የመንገሻ መንዘርከክ የዮሐንስን ዘውድ ለመውረስ የነበረው ሽኩቻ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በምኒልክ አሸናፊነት መጠናቀቁን አመላከተ።

ጀነራል አሬሮ በአንባሩ አደጋ ላይ ወደቀ። ከአንቶኔሊ ጋር ከፈጠረው አለመግባባት በተጨማሪ አለታዘዝ ባይነቱ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ አደረገው። በወርኃ ሰኔ አሬሮን በመተካት ኦሬስቴ ባራቴሪ ወደ ኤርትራ መጣ። ተተኪው ባራቴሪ የጣሊያን ቅኝ ግዛት የወታደራዊ እና የሲቪል አስተዳዳሪ በመሆን ነበር የተሾመው።



ምስል፦ ኦሬስቴ ባራቴሪ

ኦምቤርቶ ባራቴሪ በኦስትሪያ እጅ በነበረችው የሰሜን ጣሊያኗ ግዛት ትሬንቲኖ በ1841 ተወለደ። የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጅ ሳለ የጁሴፔ ጋሪባልዲን «ቀይ ለባሽ» ሠራዊት ተቀላቅሎ የሲሲሊን ግዛት ከጣሊያን ጋር ለመቀላቀል በተደረገው ውጊያ ተሳተፈ። በወታደራዊ ሥራው ስኬታማ መሆን የቻለው ኦምቤርቶ ቬኒሺያን ከኦስትሪያ ነፃ ለማውጣት በተደረገው ውጊያም ተሳትፏል። በ1876 የጀነራልነት ማዕረግ ካገኘ በኋላ የጣሊያን ብሔራዊ ምክር ቤት አባል መሆን ቻለ። ወደ ኤርትራ ተሹሞ ሲመጣ ዕድሜው 35 ዓመት ገደማ ይሆን ነበር።

ባራቴሪ በሰሜን አፍሪካ በነበረው የጣሊያን ሠራዊት ውስጥ በማገልገል ላይ ሳለ ነበር የጣሊያን የተስፋፊ ወጣቶች መፈልፈያ የነበረውን «የጂኦግራፊ ማህበር» የተቀላቀለው። በግሉ የቤልጂየሙ ንጉሥ ሊዮፖልድ አድናቂ የነበረ ሲሆን ንጉሡ በ1880ዎቹ ኮንጎን በመውረር እንዲት ትንሽ አውሮፓዊ አገር ሰፊ ግዛተ-አጼ መገንባት እንደምትችል ያሳዩበትን አጋጣሚ ያደንቃል።

ባራቴሪ ጥልቅ አንባቢ ነበር። ምፅዋ በደረሰበት ወቅት በአስተዳዳራዊ ሥራው ከኢትዮጵያ የሚገጥመውን ብርቱ ተቃውሞ እና ግፊት ለመቋቋም የሚችልበትን መንገድ አጥንቶ ጨርሶ ነበር። ሥልጣኑን እንደተረከበም በኤርትራ የነበሩ የጎሳ መሪዎችን ሰብስቦ አገሩ ጣሊያን ከራስ መንገሻም ሆነ ከአጼ ምኒልክ ብዝበዛ በተለየ መልኩ የተሻለ አስተዳደር እንደሆነች ለማሳመን ጥሯል።

ባራቴሪ ለሥልታዊ መግቢያነት የተጠቀመው መንገድ በሽፍታነቱ ይታወቅ ከነበረው ባኅታ ሓጎስ ጋር ወዳጅነትን መፍጠር ነበር። ባኅታ ከምጽዋ ወደ መሐል አገር ይደረግ በነበረው ንግድ እንቅስቃሴ ላይ የዘረፋ ተግባር ይፈጽም ነበር። በአፄ ቴዎድሮስ እና አጼ ዮሐንስ ዘመን የዘረፋ ሥራው ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። የጣሊያን መምጣት ከኢትዮጵያ ነገሥታት ይጋጥመው የነበረውን ተቃውሞ በተወሰነ ደረጃ ቀንሶለት ነበር። ባራቴሪም ሽፍታውን ባህታ በማግባባት ወዳጁ በማድረግ የሰገነይቲ አካባቢ አስተዳዳሪ እንዲሆንም ሾመው።





ሹመቱ ለባህታ የኢኮኖሚ እና ወታደራዊ ኃይል ጨመረለት። ለአገልግሎቱ ክፍያ ይሆን ዘንድም ከሚያስተዳድረው ግዛት ከሚሰበሰበው ግብር ዐሥር በመቶውን እንዲወስድ ባራቴሪ ፈቀደለት። ባህታ የካቶሊክ ዕምነት ተቀብሎ እንደነበርም ይነገራል። ጣሊያን ይዞታዋን ካጠናከረችባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የነበረው የተለያዩ የጎሳ መሪዎችን እና የግዛት አስተዳዳሪዎችን ወደ ካቶሊክ ኃይማኖት ተከታይነት መቀየር ነበር።

### የሰፈራ ቅኝ ግዛት በኤርትራ

ኅዳር 10 ቀን 1893 በድምሩ አምሳ አባላት ያሏቸው ዘጠኝ የጣሊያን ቤተሰቦች ኤርትራ ደረሱ። የሰፋሪ ጣልያናውያን ኤርትራ መድረስ ጣሊያን በማደግ ላይ የነበረው ሕዝቧን የምታሰፍርበት የውጪ ግዛት ማግኘቷን አመላካች ነበር። ጣሊያን ኤርትራ የቅኝ ግዛቷ መሆኗን ካወጀች ከአንድ ዓመት በኋላ በ1891 የጣሊያን የፓርላማ አባላት ምፅዋን በመጎብኘት ኤርትራ ጣሊያናውያንን ለማስፈር አመቺ መሆኗን አረጋግጠው ተመለሱ። ዘመኑ በየዓመቱ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አውሮፓውያን ወደ ብራዚል፣ አርጀንቲና እና አሜሪካ በመሄድ አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ የአውሮፓ መንግሥታት የሚያበረታቱበት ነበር። ጣሊያንም ዜጎቿን በአዲሲቷ ቅኝ ግዛት ኤርትራ ለማስፈር ተዘጋጀች። የሰፈራ ፕሮግራሙ ዋና አቀንቃኝ የነበረው የፓርላማ አባል ሊዎፖልዶ ፍራንቼቲም ይህንኑ አቋም ማራመድ ጀመረ።

የጣሊያን መንግሥት መሬት የሌላቸውን ገበሬዎች በመደጎም በኤርትራ እንዲያሰፍር ፍራንቼቲ ሃሳብ አቀረበ። ሰፋሪዎቹ በኤርትራ ሰፋፊ የእርሻ ሥራ በማከናወንም ለጣሊያን የምግብ እና የፋብሪካ ግብዓት አቅራቢ መሆን እንደሚችሉም ጨምሮ አቀረበ። ከተወሰኑ ባለሥልጣናት ጥቂት ተቃውሞ ቢገጥመውም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የፍራንቼቲ ሃሳብ በጣሊያን መንግሥት ተቀባይነት አገኘ።

የጣሊያን መንግሥት በፍጥነት የሰፈራ ፕሮግራሙን ጀመረ። አንድ የጣሊያን ገበሬ ቤተሰብ ለአምስት ዓመት በተከታታይ የሚያርሰው ሐያ ሄክታር መሬት በኤርትራ እንደሚሰጥ በመጥቀስ ቅስቀሳው ተጀመረ። ሰፋሪዎቹ ወደ ኤርትራ የሚያደርጉትን የጉዞ ወጪ መንግሥት የሚሸፍን ሲሆን የዘር፣ የእርሻ መሣሪያ፣ ቀለብ እና መኖሪያ ቤትም እንዲሁ ተዘጋጅቶላቸው ነበር። የመጀመሪያ ዓመት ምርታቸውን እስኪያገኙ ድረስም በአነስተኛ የወለድ መጠን የጣሊያን መንግሥት ብድር ለማቅረብ ቃል ገባ።

የሰፈራ ፕሮግራሙ አስተባባሪ የነበረው ፍራንቼቲ ከ1893 እስከ 1895 ባሉት ዓመታት ለእርሻ አመቺ የሆነ አራት መቶ ሺህ ሄክታር መሬት በኤርትራ ዝግጁ አደረገ። በመሬት ዝግጅቱ ወቅት የበርካታ ኤትራውያን የመሬት ይዞታ ተቀነሰ። የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ከኹለት የጣሊያን መንደሮች ነበር የተመረጡት። ሰባቱ የሰፋሪ ቤተሰቦች ሉምባርድ ግዛት ከምትገኘው ማጊንታ መንደር የመጡ ሲሆን የቀሩት ኹለት ቤተሰቦች ደግሞ የሲሲሊ ግዛት አካል ከኾኑት ፒዳራ እና ካታንያ መንደሮች ነበር የመጡት።

ከአስመራ በስተደቡብ ሠላሳ ማይል ርቃ የምትገኘው አዲ ኡግሪ የመጀመሪያዋ የሰፈራ መንደር ሆና ተመረጠች። ለመንደሯ «ኡምቤርቶ አንድ» የሚል ስም ተሰጣት። ሰፋሪዎቹ እንደደረሱ ለእያንዳንዳቸው ኹለት የጎጆ ቤቶች፣ ስምንት የቀንድ ከብቶች፣ ዐሥር ዶሮ እና አንድ የአሳማ ግልገል ተሰጣቸው። ዘጠኙ ሰፋሪ ቤተሰቦች በቤታቸው አቅራቢያ የተዘጋጀላቸውን መሬትም ተረከቡ። ኡምቤርቶ የሰፋሪዎች መንደር በወርኃ ግንቦት 1893 ሲመረቅ የመሬት ጠረጋ እና የመስኖ ቦይ ሥራ ተጠናቆ የነበረ ሲሆን የወይን እና ቡና ችግኝ ተከላ ተጀምሮ ነበር።

በምርቃት ሥነ-ሥርዓቱ ዕለት ትልቅ ድንኳን ተጥሎ ነበር። ከጣሊያን ወታደሮች ጋር ወደ ኤርትራ የመጡት የካቶሊክ ቄስ አባ ቦኖሚ ሰፋሪዎች የሚገጥማቸውን ችግር በፈጣሪ ጸጋ እንዲቋቋሙ በማበረታታት የእርሻ መሬት እና





መኖሪያ ቤታቸውን ባረከላቸው። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በሰኔ ወር የመጀመሪያዋ የኤርትራ የሰፋሪዎች ልጅ ሮሚሊያ አልዳኒ ተወለደች።

የሰፈራው ፕሮግራም ተቃውሞ የገጠመው ወዲያውኑ ነበር። በደቡብ ጣሊያን የነበሩ ገበሬዎች መንግሥታቸው በቅኝ ግዛት ለሰፈሩ ገበሬዎች የሚያደርገው ድጎማ ፍትሐዊ አለመኾኑን በመናገር ተቃወሙ። ኹለተኛው ተቃውሞ የተነሣው ደግሞ ከመሬታቸው በተፈናቀሉ የኤርትራ ደጋማ አካባቢ ነዋሪዎች ነበር።

በወቅቱ በከብት በሽታ ምክንያት የተነሣው ረኃብ የበርካታ ኢትዮጵያውያን ገበሬዎችን ሕይወት አመሰቃቅሎ ነበር። በምዕዋ በኩል ከሕንድ ከገቡ ከብቶች የተነሣው ወረርሽኝ ከ1888 እስከ 1892 የበርካታ ገበሬዎችን እና ከብቶቻቸውን ሕይወት ቀጥፏል። በበርካቶች ግምት ከአንድ አስረኛ እስከ አንድ ሦስተኛ የሚደርስ መጠን ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበሽታው እና በሽታው ባስከተለው ርሃብ አልቋል። ከወቅቱ መጠነ ሰፊ ቀውስ ለማገገም በመታገል ላይ የነበረው ደገኛ ገበሬ ለም መሬቱ ተነጥቆ ለነጭ ሰፋሪዎች መሰጠቱን ተቃወመ።

ፍራንሲስኮ ክሪስፒ ለወታደራዊ አጋሩ ከርም ባስተላለፈው መልዕክት ሠራዊቱ መሬቱን በመተው ሰፋሪዎችን ከጥቃት እንዲከላከል አዘዘ። ቀድሞ የነበረው የክሪስፒ ዕቅድ ሰፋሪዎችን በማስታጠቅ የጣሊያን ገበሬ ሠራዊትን በኤርትራ ማደራጀት ነበር። በዕቅዱም ገበሬ ሠራዊቱ መሬቱን እና ኤርትራን እንደሚጠብቅ ተስፋ አድርጎ ነበር። ዕቅዱን የተረዱ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለማመፅ ጊዜ አልወሰዱም ነበር።

የኤርትራው ተቃውሞ በሸዋ ከተደረገ አንድ ሥነ-ሥርዓት ጋር ታሪካዊ መገጣጠም ነበረው። ምርኮኛው ልዑል መንገሻ እና አዝማቹ ራስ አሉላ አዲስ አበባ የሚገኘው የምኒልክ ቤተ-መንግሥት የደረሱት ሰኔ 2 ቀን 1894 ዓ.ም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ ነበር። እጃቸውን በሰጡበት ወቅት እንዳደረጉት ኹሉ ወደ ምኒልክ ቤተ-

መንግሥት ግቢ ሲቃረቡ ድንጋይ በትከሻቸው ተሸክመው ነበር። መንገሻ ወደ ምኒልክ መንበር ሲቃረብ በግንባሩ ተደፍቶ ሰላምታ ሲሰጥ በግቢው የነበሩ የምኒልክ ወታደሮች ወደ ሰማይ በመተኮስ የንጉሣቸውን ድል አደመቁ።

የዕለቱ ንጉሣዊ ሥነ-ሥርዓት የዘመናዊት ኢትዮጵያን መፈጠር የመጨረሻ ምዕራፍ የዘጋ ነበር። ምክንያቱም በመንገሻ ሥር የነበረው የትግራይ ግዛት ከሸዋ ጋር የተጠቃለለበት አጋጣሚ ነበር። በጣሊያን እና በምኒልክ ተከብቦ የነበረው መንገሻ ምንም አማራጭ ስላልነበረው ግዛቱን ለንጉሠ ነገሥቱ አስረከበ። በዚያው ዓመት መጨረሻ ነበር በኤርትራ ጣሊያን ላይ ተቃውሞ መነሣት የጀመረው።



Francesco Crispi. From John Grand-Carteret, *Crispi, Bismarck et la Triple-alliance en caricatures*. Paris: C. Delagrave, 1891.

***ምስል፦ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ (ፓሪስ 1891)***





**ባሕታ ሐጎስ እና ልዑል መንገሻ፦ ከነጭ እባብ ጋር የተደረገ ግብግብ**

በነሐሴ 1894 በአንዱ ምሽት ባህታ ሐጎስ ሰገነይቲ በነበረው የጣሊያን አስተዳዳሪ መኖሪያ ቤት ራት ተጋብዞ ተቀምጧል። ገበታው ከፍ እንዳለ ባህታ እና ግብረአበሮቹ ቤቱን ለቀው መውጣት እንደጀመሩ ወደኋላ በመመለስ ጋባዥን ጣሊያናዊ በማነት ከወንበር ጋር አሠሩት። «ገደል ግባ! ጣሊያን አሁንም ታላቅ ናት!» በማለት ጣሊያኑ ባህታ ላይ ጮኸበት። ባህታም «ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ታላቅ ናት!» በማለት ታጋቹ ላይ ጮኸበትና ወዲያውኑ ተኩሶ ገደለው። እገሩን በመክዳት፣ ሃይማኖቱን በመቀየር እና የጣሊያን አሽከር በመሆን ይታወቅ የነበረው ሽፍታው ባህታ በመጨረሻም አገሩን መረጠ።

የባህታ ወታደሮች ኹለት የጣሊያን ቴሌግራፍ ባለሙያዎችን አግተው ወሰዱ። ለታጋቾቹ «ከእናንተ ጋር የግል ፀብ የለኝም» በማለት ባህታ ተናግሮ ነበር። ጣሊያን ለሰፋሪ ዜጎቿ ለም የእርሻ መሬት ለማቅረብ ስትል የአገሬውን ሰው ማፈናቀሏ ነበር ታማኟ ባህታን እንዲያምፅ ያደረገው። ከመሬቱ በተጨማሪም በርካታ የኤርትራ ሴቶችንም በማስገደድ እና በማማለል የወታደሮች ቅምጥ «ማዳማ» ማድረጓ ነበር ያስቆጣው። በኢትዮጵያ ማህበራዊ ሥርዓት ለዘመናት የቆየ ዕምነት አለ። ይኸውም የአገሬው ሰው በአገሩ፣ በሴቶቹ እና በመሬቱ ከመጡበት አለመመለሱ ነበር።

የነጭ የዘር መድልዎ በግልጽ የታየበት የጣሊያን አካሄድ በርካታ የባህታ ወገኖችን አስቆጣ። ባህታ ለዘረኝነቱ ምላሽ ሲሰጥም «ነጭ እባብ ከነደፈህ መድኃኒቱንም ማግኘት ቀላል አይደለም» በማለት ተናግሯ ነበር ሕዝቡን ለአመፅ ያነሳሳው።

በአመፁ ሦስተኛ ቀን በጀነራል ፒየትሮ ቶሴሊ የሚመራ አንድ ሺህ አምስት መቶ የጣሊያን ወታደር ወደ ሰገነይቲ ተንቀሳቀሰ። ባህታ ለመከላከል ያሰለፈው ሠራዊት ከሰባት መቶ በታች ነበር። ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመቱ ቀላል



ncesco Crispi. From John Grand-Carteret, *Crispi, Bismarck et la Tripl-*
*iance en caricatures.* Paris: C. Delagrave, 1891.

ምስል፡- ፍራንሲስኮ ክሪስፒ (ፓሪስ 1891)

ነበር። ታጋቾችን በነፃ በመልቀቅ ዘወትር ይመሰገን የነበረው ባህታ ከጣሊያን ጋር ባደረገው የአመፅ ውጊያ ሃላይ በተባለ ቦታ በበርካታ ጥይት ተደብድቦ ሞተ። ከባህታ ሞት በኋላ የአገሬው ሕዝብ ትግሉን ሊያስቀጥለው የሚችል መሪ በማጣቱ ቂሙን በልቡ በመያዝ አመፁን ለጊዜው አቆመ።

የባህታ ሞት በተሰማ በማግስቱ መንገሻ ጦሩን ከአድዋ በስተምሥራቅ ወደምትገኘው ኢንጢቾ አዘመተ። በወቅቱ ቁጥሩ ወደ ዘጠኝ ሺህ የሚጠጋውን ጦር ሲያዘምት መንገሻ ለሽፋን የተጠቀመው «ሙስሊም ደርቪሽ» እየመጣ በመኾኑ ኢንጢቾ ላይ ሊመሽግ እንደሆነ ነበር። ነገር ግን መንገሻ በቀጥታ ያመራው በአቅራቢው ወደ ነበረው የጣሊያን ምሽግ ነበር።

አሬስቴ ባራቴሪ የመንገሻን መምጣት እንደሰማ ነበር ፀ ሺህ አባት ያሉት ሠራዊቱን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ያዘመተው። መንገሻ ያለ ምንም በቂ መከላከያ የተዋትን የአድዋ ከተማ ታኅሣሥ 28 ቀን በቁጥጥሩ ሥር አዋለ። የከተማው ነዋሪ መንገሻ ያለ ምንም ጠባቂ ስለተወው በማኩረፉ የኤሬስቴን ሠራዊት ያለምንም መከላከል ነበር ያስገባው። በተለይ ቀሳውስት እና ካህናት ለአሬስቴ ያሳዩት የወዳጅነት አቀባበል ያልተጠበቀ ነበር።

የአድዋን መያዝ የሰማው የመንገሻ ጦር ከነበረበት ቦታ ለመንቀሳቀስ አልሞከረም ነበር። ባራቴሪ እንዳደረገው ኹሉ መንገሻም አድዋን በመተው በቀጥታ ወደ ኤርትራ በመግባት ምፅዋን ጨምሮ አጠቃላይ ኤርትራን መያዝ ይችሉ ነበር። መንገሻ ያንን ማድረግ ቢችል ኖሮ አገር ወዳድነቱን በማስመስከር የአባቱን ዘውድ ለመውረስ ቢጣጣር የሕዝብ ድጋፍ ማግኘት ይችልም ነበር።

አፄ ምኒልክ ዘንድ የደረሰው ጭምጭምታ መንገሻ የባራቴሪን ጦር ደምስሶ ወደ ምፅዋ እየገሰገሰ መኾኑ ነበር። በእርግጥ ይህ ተራ ወሬ ነበር። ባራቴሪ በአድዋ ለሦስት ቀናት ከቆየ በኋላ መንገሻ ወደ ኤርትራ ለመንቀሳቀስ መዘጋጀቱን ሲሰማ





ጦሩን ወደ መጣበት መለሰ። በመልስ ጉዞው ከመንገሻ ጋር ላለመገናኘት የቻለውን ጥንቃቄ አድርጓል። ምክንያቱም የመንገሻን ጦር ፊት ለፊት ለመግጠም በቂ ኃይል አልነበረውም። በኹለቱ ጦር አሰላለፍ መሠረት ኹለት የመንገሻ ወታደር ለአንድ የባራቴሪ ወታደር ሊደርስ ይችላል።

ጥር 12 ቀን 1895 የባራቴሪ ሰላዮች የመንገሻ ጦር ኮአቲት ላይ መመሸጉን ደረሱበት። የመንገሻ ሠራዊት የጠላት ጦር መጠጋቱን ባላወቀበት ሁኔታ ነበር በማግስቱ ጦርነቱ የተጀመረው። በጦርነቱ አሸናፊ ባይኖርም በመንገሻ በኩል በርካታ ወታደሮች ሞተዋል። ጥር 14 ምሽት ላይ መንገሻ ቀሪውን ሠራዊት አስከትሎ በጭለማ ወደ አድዋ አፈገፈገ። ጥር 15 ባራቴሪ የመንገሻን ምሽግ ሲቆጣጠር አንድም የመንገሻ ሠራዊት አላገጠመውም።

ባራቴሪ በዚያው ቅፅበት መንገሻ ያመለጠበትን መንገድ ይዞ ወደ ኋላ ተመለሰ። የመንገሻን ጦር በማሳደድም በማግስቱ እኩለ ቀን ላይ ሰንአፌ ላይ ደረሰበት። የጣሊያን መድፍ የመንገሻን ካምፕ ሙሉ በሙሉ ደበደበ። የመንገሻ ማረፊያ የነበረውን ድንኳን ሳይቀር አቃጠሉት። መንገሻም የተረፉ ወታደሮቹን አስከትሎ ሸሸ።

በመድፍ ከተቃጠለው የመንገሻ ማረፊያ ድንኳን የተገኘው የግል ማሕደር ለባራቴሪ ቀጣይ እርምጃ መንገድ ጠቋሚ ነበር የሆነለት። ቀጣይ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ግን የካቲት 1 ቀን 1895 ከመንገሻ ደብዳቤ ደረሰው። ደብዳቤው የይቅርታ ይዘት ያለው ሲሆን «ሰይጣን አሳስቶኝ እንጂ ኤርትራን የመውረር ሃሳብ አልነበረኝም» በማለት ነበር መንገሻ ባራቴሪን ይቅርታ የጠየቀው።

መንገሻ ለማስተባበል ቢሞክርም ባራቴሪ ግን የመንገሻን ትክክለኛውን ሴራ በምርኮ ካገኘው የግል ማህደሩ ውስጥ አግኝቷል። በማህደሩ ከነበሩት በርካታ መረጃዎች መካከል ምኒልክ እና መንገሻ የተለዋወጧቸው ደብዳቤዎች ይገኙ ነበር።

በአንዱ ደብዳቤው አፄ ምኒልክ ‹‹ጠላቴ›› ሲሉ የገለጻቸውን ጣሊያኖች እንዲያጠፉ መንገሻን መላካቸው ታወቀ። ከዚህ በተጨማሪም ባህታ ሓጎስ አመፅ ጀርባ ምኒልክ እና መንገሻ እንዳሉበት ባራቴሪ አረጋገጠ። በአጠቃላይ ጣሊያኖች ደጋግፈው ለሥልጣን ያበቃቸው አፄ ምኒልክ ከእጃቸው እንደወጣ አረጋገጠላቸው።

- ጣሊያን የምኒልክ ኃይል ለመጠባበቅ እንዲያስችላት መንገሻ እና አሉላን በምኒልክ ላይ ለማሥነሳት ዐቅዳ ነበር። ነገር ግን መንገሻ ምኒልክን መምረጡን ካረጋገጠች በኋላ ዕቅዷን ሰርዛለች። በባራቴሪ ከተደበደበ በኋላ መንገሻ ጦሩ በመዳከሙ የአንድ ተራ ሽፍታ ያህል እንኳን ጥንካሬ አልነበረውም። የመንገሻ መዳከም ለጣሊያን አንድ ጠላት ቢቀንስላትም በሌላ በኩል ግን ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በምኒልክ ዘውድ ሥር መጠቃለል ቻለች።

ባራቴሪ መንገሻን ለመውጋት ያወጣው የጦር ወጪ በአጠቃላይ ከ10 ሺህ ፓውንድ (ግማሽ ሚሊዮን ሊሬ) በታች ነበር። የጦር ወጪውን አነስተኛ ካደረጉለት ምክንያቶች መካከል አንዱ የነበረው ባራቴሪ በርካታ አፍሪካዊ አስካሪ ወታደሮችን በአነስተኛ ደሞዝ ቀጥሮ በማዋጋቱ ነበር። ከገንዘቡ በተጨማሪ የሟች አውሮፓውያንም ቁጥር አነስተኛ ለማድረግ ችሉ ነበር። ሰሮም በጻፈው ደብዳቤ እንደገለጸው በአጠቃላይ ዐሥራ አንድ ወታደር ሲሞትበት ሠላሳ ደግሞ ቆስለውበታል። ከሟቾቹ መካከል ነጭ ወታደር አለመኖሩንም ጠቅሶ ነበር።

ባራቴሪ በ1894 እና በ1895 በአነስተኛ የገንዘብ ወጪ እና መስዋዕትነት ያገኛቸው ድሎች የኢትዮጵያን ጦር ዝቅ አድርጎ እንዲመለከት አድርጎታል። ባህታን እና መንገሻን ማሸነፉ የምኒልክን ጦር አሳንሶ እንዲመለከት አስቻለው። የተሳሳተ የጣሊያን ግምት በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ለነበሩት አፄ ምኒልክ መልካም ዕድል እንደሆነላቸው የታየው በአድዋው የውጊያ ውሎ ነበር።





## ባራቴሪ የኢትዮጵያን ድንበር ጣሰ

በአነስተኛ ድሉ የተኩራራው ባራቴሪ ትግራይን በመውረር ኤርትራን በዘላቂነት ከኢትዮጵያ ጥቃት ለመከላከል የሚያስችለውን ቦታ ለመያዝ ተዘጋጀ። ከአድዋ እስከ አዲግራት የተዘረጋውን ተራራማ ይዞታ ለመውረርም ዕቅድ አወጣ። ትግራይን መውረሩ ከአፄ ምኒልክ ምን ሊያስከትልበት እንደሚችል ሳያስብ ነበር የካቲት 3 ቀን 1895 አዲግራትን በቁጥጥሩ ሥር ያዋላት።

አዲግራት በአፍሪካ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ከሚገኙ ጥቂት ከተሞች አንዷ ናት። ከከተማዋ በምሥራቅ አቅጣጫ ያሉ ወንዞች ወደ ቀይ ባሕር የሚገቡ ሲሆን በምዕራብ ያሉት ደግሞ የዓባይ ገባር ናቸው። ከተማዋ የአጋሜ ምድር ማዕከል ስትሆን ተስማሚ አየር እና ጥሩ ወታደራዊ ጠቀሜታ አላት። ጣሊያን በ1895 አዲግራትን መያዝ ከፍተኛ ጠቀሜን አስገኝቶላታል።

ከአዲግራት ምዕዋ ያለው ርቀት አነስተኛ መሆን በራሱ ለጣሊያን መልካም ነበር። በአጠቃላይ ከምፅዋ ጀምሮ ጊንዳ፣ አስመራ፣ ጎራ፣ ከአቲት፣ ሰንአፌ፣ ባራኪት እና አዲግራት ላይ ጣሊያን ጠንካራ ምሽግ ገነባች። ከወታደራዊ ጠቀሜታዋ በተጨማሪ አዲግራት ለጣሊያን የሰፈራ ቅኝ ግዛት ተመራጭ ቦታ መሆኗን ባራቴሪ ለሮም በጻፈው ደብዳቤ ገልጿል።

. አዲግራትን ከተቆጣጠረ በኋላ ባራቴሪ ሊያሳካ ያልቻለው ነገር ቢኖር መንገሻን መያዝ ነበር። ጦሩን እስከ መቀሌ በመላክ ቢያስስም መንገሻ ግን አልተገኘም። ባራቴሪ የራሱን ጦር በመምራት ወደ ምዕራብ ዘምቶ ከአድዋ እስከ አክሱም አሰሰ። ወደ ደቡብ እስከ አምባላጌ ድረስም እንዲሁ። እግረ መንገዱንም ለአሰሳ የወጣባቸውን ቦታዎች በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ የጣሊያንን ቅኝ ግዛት አሰፋ። ነገር ግን ተጨማሪ ቦታዎችን በያዘ ቁጥር የአስተዳደር ቁጥጥሩ እየላላ ኤርትራም ያለ ጠንካራ መከላከያ ለኢትዮጵያ ወረራ ቀላል እየሆነች መሆኗን ባራቴሪ የተረዳው ቆይቶ ነበር።

አዲስ የተያዙ የትግራይ አካባቢዎች ለሰፈራ አመቺ እንደኾኑ የተመለከተው ባራቴሪ መሬቱን በኹለት መንገድ ለሰፈራ ማመቻቸት ጀምሮ ነበር። የተሻለ ለምነት ያላቸውን ቦታዎች ለጣሊያን ዜጎች እንዲሁም መለስተኛ የኾኑትን ለቅጥረኛ «አስካሪ» ወታደሮች በማከፋፈል በዚያውም ጠንካራ የመከላከያ ሰፋሪ ጦር መገንባት ነበር ዕቅዱ።

የዕቅዱን ዝርዝር ወደ ሮም በመላክ ለአጠቃላይ ዘመቻው የሚያስፈልገው 13 ሚሊዮን ሊሬ እንዲላክለት ጠየቀ። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ በምላሹ 9 ሚሊዮን ሊሬ አብቃቅቶ እንዲጠቀም በተጨማሪም የጦርነት ወጪውን በወረራው ከሚገኘው የዘረፋ እና የምርኮ ንብረት ላይ እንዲጠቀም አዘዘው።

ባራቴሪ ግራ ተጋብቶ በውጥረት ቆየና በመጨረሻም በቦታው ሰው እንዲተካ ለሮም አሳወቀ። ክሪስፒም የባራቴሪን መልቀቂያ ውድቅ አድርጎ ለምክክር እና ተጨማሪ የዘመቻ ዕቅድ ዝግጅት በግንቦት ወር 1895 ወደ ጣሊያን አስጠራው።

ሮም ሲደርስ የጀግና አቀባበል ተደረገለት። «የክሎቲት እና የሰንአፊ ጀግና» በሚል ማዕረግም ኒሻን ተሸለመ። በሽልማቱ እና አቀባበሉ ተደስቶ ስለነበር ሥራውን እንደ ቀድሞው ባልዲሴራ ላለመልቀቅ ወሰነ።

ክሪስፒ እና ባራቴሪ የዘመቻ ዕቅድ በማውጣት ላይ ሳሉ በማቲዎ ኢምብሪያኒ የተመራ የተቃዋሚዎች ቡድን ጣሊያን የቅኝ ግዛት ወረራዋን እንድታቆም ጠየቀ። ጠቅላይ ሚኒስትር ክሪስፒ ጥያቄያቸውን ሲመልስ ኤርትራ ለጣሊያን ዓይነተኛ የሰፈራ አማራጭ መሆኗን አስረግጦ ነበር የተናገረው።

ባራቴሪ የጠየቀውን የዘመቻ ወጪ ተቀንሶ ዐሥር ሚሊዮን ሊሬ ተፈቀደለት። እረፍቱን ከቤተሰቡ ጋር አሳልፎ በወርኃ መስከረም ወደ ኤርትራ የመልስ ጉዞውን ጀመረ። በስንር ፍቅር እና የተስፋፊነት ፍላጎት የታወረው ባራቴሪ ለአገሩ ጣሊያን ከእርሱ የምትፈልገውን ኹሉ ሊሰጣት ቃል ገብቶ ነበር ወደ ኤርትራ የተመለሰው።





# ክፍል ኹለት
# የአድዋ የጦር ሜዳ ውሎ

# ምዕራፍ ስምንት

## የምኒልክ ዘመቻ

የምኒልክ «ክተት» ዐዋጅ የተነገረው በመስከረም ወር በአንዱ ቅዳሜ ነበር፡፡ ዕለቱ በአዲስ አበባ ደማቅ ገበያ የሚቆምበት ነው፡፡ ኹለት ዐዋጅ ነጋሪዎች ገበያተኛውን በመሰብሰብ የንጉሡን ዐዋጅ አሰሙ፡፡ ኢትዮጵያ ለጦርነት መዘጋጀት ጀመረች፡፡

በጥር 1895 የመንገሻን በጣሊያን መደምሰስ የሰሙት ምኒልክ እርምጃ ለመውሰድ አልቸኮሉም፡፡ በመቀጠልም በወርኃ የካቲት የጣሊያን ወራሪ ኃይል ወደ ትግራይ በመዝለቅ እስከ ደቡባዊው አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ወረራ ሲፈጽምም ለመከላከል አልተንቀሳቀሱም፡፡

የምኒልክን ዝምታ ከፍራቻ ጋር በማያያዝ የተረዱ በርካታ አውሮፓውያን ነበሩ፡፡ ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና የጣሊያኑ ጀነራል ፒየትሮ ቶሲሊ ግን የምኒልክ ዝምታ አደጋ እንዳረገዘ ደጋግመው ተናግረዋል፡፡ በምኒልክ ዝምታ የተበረታታችው ጣሊያን በአጠቃላይ ወደ ሰባት ሺህ ስኩዌር ማይል ስፋት ያለው ቦታ በወረራ ያዘች፡፡ በአጠቃላይ ስፋቱም ከቤልጅየም የሚበልጥ ቦታ ነበር፡፡ የጣሊያን መስፋፋት ቀጥሎ በመጨረሻም የታቦተ ጽዮን መቀመጫ የሆነችውን ቅድስቲቱን አክሱም ወረረች፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ያለፉ ነገሥታት በሙሉ የማይደራደሩበት ነገር ቢኖር አክሱምን ለጠላት አሳልፎ መስጠትን ነው፡፡

የምኒልክ ዝምታ መስበር የተጀመረው ከአክሱም መያዝ በኋላ ነበር፡፡ የንግሥና ዘውዳቸውን ከጫኑ ስድስት ዓመታት ቢያልፍም ምኒልክ ትግራይን አልጎበኙም ነበር፡፡ ክልሉን በተለያዩ የጦር መሪዎቻቸው በኩል ሲያስተዳድሩ ነበር የቆዩት፡፡ በመጨረሻም ጣሊያን መላውን የትግራይ አካባቢ ስትይዝ ምኒልክ ለመጀመሪያ ጊዜ ትግራይን በመጎብኘት የአገራቸውን ግዛት ለማስከበር ተነሱ፡፡





### ሕዝባዊ ቅስቀሳ በኢትዮጵያ

አፄ ምኒልክ ከቤተ መንግሥታቸው አካባቢ በሚነሳ ተቃውሞ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ባለቤታቸው ጣይቱ እና ወንድማቸው ራስ ወሌ ከሰሜናዊ ወዳጆቻቸው መንገሻ እና አሉላ ጋር በመሆን ጣሊያን ላይ ጦር እንዲያዘምቱ ምኒልክን ወተወቷቸው፡፡ ወታደራዊ ዘመቻ የሚደረገው ወቅትን በመጠበቅ በመኾኑ ምኒልክ የክረምቱ ወራት እስኪያልፍ ለመጠበቅ ወሰኑ፡፡

ከመጋረጃ ጀርባ በመሆን ምኒልክ የዘመቻ ዕቅድ መንደፍ ጀመሩ፡፡ በሚያዝያ 1895 አዲስ የጠመንጃ እና ጥይት ግብር ጣሉ፡፡ ከሙስሊም ደርቪሾች ጋር የነበረውን ፍጥጫ ለማርገብ በርካታ ፈረሶችን እና ቡና በስጦታ መልክ ላኩላቸው፡፡ ኃይማኖታዊ ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተውም ጥቁርነታቸው ላይ ተመርኩዘው የጋራ ጠላታቸውን እንዲከላከሉ ለደርቪሾች ጥሪ አቀረቡ፡፡ ለደርቪሽ በጻፉት ደብዳቤም አፄ ምኒልክ እንዲህ ብለዋል፡- *«እኔም እንደ እናንተ ጥቁር ነኝ፡፡ በአንድ ላይ በመሆን የጋራ ጠላታችንን መውጋት ይኖርብናል፡፡»*

ክረምት እንደወጣ በወርኃ መስከረም 1895 አፄ ምኒልክ አገር አቀፍ «ክተት» አወጁ፡፡ ወራሪው የጣሊያን ጦርም ግዛታቸውን ለቅቆ እንዲወጣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ አስተላለፉ፡፡

ከዐዋጁ በፊት ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጦር ሠራዊት አልነበራትም፡፡ አገሪቷን ለዘመናት ከወራሪ የጠበቃት የሕዝቡ ጠንካራ ወታደራዊ ልምድ ነበር፡፡ በአገሩ እና በኃይማኖቱ ስም ለሚደረግለት ጥሪ ሕዝቡ በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ይታወቃል፡፡ ወታደራዊ ትዕዛዝ በቀጥታ ከንጉሡ ወደ ራስ ይወርዳል፡፡ በመቀጠልም ወደ ግዛት አስተዳዳሪዎች እና የቀበሌ/ሰፈር ጭቃ ሹሞች ይደርሳል፡፡

የክተት ዐዋጁ ከቤተ-መንግሥት በተነገረበት ቅጽበት በርካታ መልዕክተኞች በአገሪቱ የተለያዩ አቅጣጫዎች ተበትነው ዐዋጁን አዳረሱ፡፡ ወንዱ ጦር፣ ጎራዴ፣


ጋሻ፣ ጠመንጃ እና ያለውን መሣሪያ ከዐሥር ቀን ስንቅ ጋር ዝግጁ አደረገ። ሴቶች ለስንቅ የሚሆን ዳቦ፣ በርበሬ እና ቅቤ አዘጋጁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ወንዶች በኢትዮጵያ ባሕል መሠረት መሣሪያ እና ጎራዴያቸውን በቀኝ ጎናቸው ታጥቀው በየቀዬአቸው መሸለል ጀመሩ። በየግዛቱ ያሉ ዜጎች ከአጎራባች ግዛቶች ጋር በመገናኘት ጉዞ የሚጀምሩበትን ዕለት እና ቦታ ወሰነው ጉዞ ጀመሩ።

ወታደር የመመልመሉ ተግባር በፍጥነት ቢከናወንም በምልመላው ወቅት የምልምሎቹ ታማኝነት ዋናው የትኩረት ነጥብ ነበር። ከሸዋ ንጉሥነት በመነሳት የመላ አገሪቱ መሪ መሆን የቻሉት አፄ ምኒልክ በአብዛኛው አገሪቱ በነበሯቸው ታማኞቻቸው አማካኝነት በርካታ ሠራዊት ማሰባሰብ ቻሉ። የራስ መኮንን፣ ራስ ወሌ፣ ንጉሥ ተክለሃይማኖት፣ መንገሻ እና አሉላ ድጋፍ አስፈላጊ ነበር። በምልመላ ሥራው ወቅት ጣሊያኖች የገመቱት በጦርነቱ ወቅት የምኒልክ ቅይጥ ሠራዊት በመበታተን ከዳተኛው እንደሚበዛ ነበር። በዚያም የተነሣ የምኒልክ ሠራዊትም ሆነ መላዋ ኢትዮጵያ በእጃቸው እንደሚወድቁ በመጠባበቅ ላይ ነበሩ።

የምኒልክ ሠራዊት ከአዲስ አበባ በመነሳት ጉዞውን የጀመረው ጥቅምት 11 ቀን ነበር። ከደቡብ የተነሣው ጦር ወረኢሉ ላይ የሰሜኑ ደግሞ አሸንጌ ሐይቅ አቅራቢያ እንዲቀላቀላቸው አፄ ምኒልክ ቀድመው አሳውቀዋል። የምኒልክ ወታደር ባለፈባቸው ቦታዎች ኹሉ እርሶ እደሩ ስንቅ በማቀበል እና በማበረታታት ነበር የሸኘው።









Route of the Adwa Campaign, Addis to Adwa

*ካርታ - የአድዋ ዘመቻ የጉዞ መስመር (ከአ.አ እስከ አድዋ)*




Route of the Adwa Campaign, Addis to Adwa

ካርታ - የአድዋ ዘመቻ የጉዞ መስመር (ከአ.አ እስከ አድዋ)

## የዘመቻው አጀማመር

ጣይቱ እና ምኒልክ ከሠራዊቱ ጋር በመሆን ነበር ጉዞውን የጀመሩት። የኹለቱ መኖር ሠራዊቱን ከወዲሁ ከማነቃቃቱ በተጨማሪ መንገድ ላይ የሚቀላቀለውን የሠራዊት ቁጥር ከፍ አድርጓል። ምኒልክና ጣይቱ በጉዞው ወቅት ቃል የገቡ የግዛት አስተዳዳሪዎች በቃላቸው መሠረት ሠራዊት፣ ትጥቅ እና ስንቅ ማቅረባቸውንም መታዘብ ችለዋል።

በዘመቻው ወቅት በምኒልክ የሚመራው ሠራዊት መሃል ጎዳና ይዞ ሲጓዝ የራስ ወሌ እና ንጉሥ ሚካኤል ጦር ደግሞ ግራና ቀኝ ተራራውን በመያዝ አጅቧቸዋል። የጉዞው ሥልት በቂ የጥበቃ ደኅንነት ከመፍጠሩ በተጨማሪ የወታደሩን መዳከም ቀንሷል። የሠራዊቱን ጉዞ የተመለከቱ ሰዎች የሠራዊቱን ነጭ ሸማ እና የሚያብረቀርቅ ጦር እና ጋሻ እንደማይረሱት ተናግረዋል።

በዘመቻው ወቅት ጣይቱ ብጡል ከምኒልክ በላይ ጎልተው ታይተዋል። የተመረጡ አጃቢዎቻቸው ድባብ ጥላ በመያዝ በበርካታ ሠራዊት አጅበዋቸው ነበር የሚጓዙት። ጣይቱ ያስከተሉትን ጦር ይመሩ የነበሩት ባልቻ፣ ከጦር መሪነታቸው በተጨማሪም የምኒልክ ግምጃ ቤት ኃላፊ እና የዘውድ ጠባቂም ነበሩ።

ጣይቱ በሺህ የሚቆጠሩ ታጣቂዎችን ብቻ አልነበረም ያስከተሉት። ከመቶ በላይ አባላት የነበሩት የሙዚቀኞች ቡድንም ጭምር እንጂ። በሰላሙ ቀን ጣይቱ ለበገና ልዩ ፍቅር የነበራቸው ሲሆን በአድዋው ዘመቻም በርካታ አዝማሪያን እና በገና ደርዳሪዎችን አስከትለዋል። የጣይቱ ፈረስ በመከተል የተለያዩ የዘመቻ ዘፈኖችን፣ ቀረርቶዎችንና ሽለላዎችን በማሰማት ነበር የሙዚቀኞች ቡድን ያጀባቸው።







*ምስል፡- ጣይቱ በዘመቻ ጉዞ ላይ (የካቲት 14 ቀን 1896)*

የየዕለቱን ጉዞ የሚጀምሩትም ሆነ የሚያጠናቅቁት የንጉሡን እና የንግሥቲቱን ማረፊያ ድንኳን የሚሸከሙት የሠራዊት አባላት ነበሩ። በልዩ መጠሪያው «ደስታ» በመባል የሚታወቀው ባለቀይ መጋረጃ የንጉሡ ልዩ ድንኳን «እልፍኝ» የሚባለውን የጣይቱ ማረፊያ እንዲሁም «አዳራሽ» በመባል የሚታወቀው የነገሥታቱ አገልጋዮች ማረፊያ ድንኳኖች በመስመር እንዲጣሉ ሲደረግ ሠራዊቱ የዕለቱን ጉዞ ማጠናቀቁን ያሳውቃሉ። ወደ ሚቀጥለው ቀን የጉዞ መስመር በሩን በማዞር ነበር «ደስታ» የሚከተለው። ሌሎቹ ድንኳኖች በሙሉ ከንጉሡ ማደሪያ ኋላ ነበር የሚጣሉት።

የንጉሡ ቀይ ድንኳን ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ከተተከለ በኋላ ወዲያውኑ የንጉሡ አገልጋዮች ሥራቸውን ይጀምራሉ። በዐሥራ አምስት በቅሎ ተጭኖ የሚጓዘው የንጉሡ እግር መርገጫ በአግባቡ ይነጠፋል። መንበራቸውም ቦታውን ሲይዝ



Taytu on campaign. From *L'Illustration*, 14 March 1896.

ምስል፡- ጣይቱ በዘመቻ ጉዞ ላይ (የካቲት 14 ቀን 1896)

በዙሪያው አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ ቀለማት ያሏቸው በርካታ የሸማ ጨርቆች በመንበሩ ዙሪያ ይሰቀላሉ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የንጉሡ የጉዞ ቤተ-መንግሥት ባማረ ሁኔታ ተገንብቶ ለእራት እና የምሽት መዝናኛ ዝግጁ ይሆናል።

የድንኳኖቹ አቀማመጥ እና ቦታ አያያዝ የባለድንኳኑን መዓርግ ደረጃ እና ማዕረግ ያሳያል። ከንጉሡ ድንኳን በቅርበት የተጣለ ድንኳን ያለው ሰው የቅርበት ደረጃው ከፍተኛ ነው። ከምኒልክ ድንኳን አጠገብ የነበረው የግምጃ ቤቱ ድንኳን ሲሆን ከእርሱ ቀጥሎ ደግሞ የንጉሡ እና የንግሥቷ አልባሳት የሚቀመጥበት ድንኳን ቦታውን ይይዛል። በተለምዶ «የልብስ ድንኳን» ከሚባለው ቀጥሎ የክቡር ዘበኛ እና የካህናት ድንኳን ይተከላል። ከካህናቱ ጀርባ የንጉሡን ጨምሮ የበርካታ ፈረሶች መቆሚያ ሥፍራ ሲሆን ከፈረስ ጋጣው ቀጥሎ የምግብ ማብሰያ ድንኳኖች ይተከላሉ። የንጉሡ ቤተ-መንግሥት አገልግሎት በጉዞ የማይጓደል ሲሆን ለእንጀራ፣ ለወጥ፣ ለጠጅ እና ለጠላ ብቻ የየራሳቸው ድንኳኖች ይጣሉ ነበር።

የምግብ ማብሰያ ድንኳኖች የንጉሡ ማረፊያ የመጨረሻውን መስመር ይይዛሉ። ከማብሰያዎቹ ቀጥሎ የራስ መንገሻ፣ የራስ መኮንን እንዲሁም የምኒልክ አፈ-ንጉሥ ድንኳኖች ይተከላሉ። ከሦስቱ ድንኳኖች ቀጥሎ የበርካታ ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዥ ድንኳኖች ይታያሉ። ከአዛዦቻቸው ጀርባ እጅግ በርካታ ድንኳኖች የሚጥሉት ተራ ወታደሮቻቸው ነበሩ። በአጠቃላይ የምኒልክ ሠራዊት ጊዜያዊ ማረፊያ ታላቅ የድንኳን ከተማ ይመስላል።

ሠራዊቱ በቀን ከአምስት ሰዓታት በላይ እንዳይጓዝ ንጉሡ አዘው ነበር። ከአዲስ አበባ እስከ አሸንጌ ሐይቅ ድረስ የተደረገው ጉዞ ዝግተኛ የነበረ ሲሆን ጣይቱ እና ምኒልክ አጋጣሚውን በመጠቀም በሕዝቡ ዘንድ ያገኙትን ተቀባይነት ለመገምገም ችለዋል። በየመንገዳቸው የሚደረግላቸውን አቀባበል እና አሸኛኘት በመመልከትም የሕዝቡን ይሁንታ ማግኘታቸውን አረጋገጡ።





የምኒልክ ድንኳን አሸንጌ ሐይቅ ዳርቻ በተጣለበት ታኅሳስ ወር አጋማሽ ላይ የሠራዊቱ ቁጥር ከመቶ ሺህ ይልቅ ነበር። ሠራዊቱ ጠንካራ የውጊያ ሞራል የነበረው ሲሆን በዘመኑ ማሰፈያ የነበረ ጠመንጃም ታጥቋል። የጦሩ አሰላለፍ በቁጥር ሲሰላ ለአንድ የጣሊያን ወታደር አራት የኢትዮጵያ ወታደሮችን የማሰለፍ ያህል ነበር።

የወራሪው ጣሊያን ጦር ስለ ኢትዮጵያ ሠራዊት ብዛት እና ጥራት የተዛባ መረጃ ነበር ያለው። ሠራዊቱን ዝቅ አድርጎ ከመገመቱም በላይ ከምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሆን ተብሎ የተነገሩ የማደናገሪያ ወሬዎችንም የጣሊያን ሠራዊት እንደ እውነተኛ መረጃ ተቀብሏቸው ነበር። አፈትልከው ከወጡት የማደናገሪያ ወሬዎች መካከል የራስ መኮንን መከዳት፣ የንጉሥ ተክለሃይማኖት ልብ መሸፈት እና የምኒልክ በመብረቅ ተመትቶ መሞት ይገኙበት ነበር። እያንዳንዱ የስሙት ወሬ ጣሊያኖች የሚገጥሙት የኢትዮጵያ ጦር የተሰነጣጠቀ እና አነስተኛ የውጊያ ሞራል ያለው መኾኑን አሳምኗቸው ነበር።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## አምባ'ላጌ

ፒየትሮ ቶሴሊ የ17 ዓመት ወጣት ሳለ ነበር ቱሪን ከሚገኘው ‹‹ሪያሌ›› የጦር አካዳሚ የተመረቀው። አካዳሚው ከ16 ዓመት በታች ያሉ ልጆችን የማይቀበል ቢሆንም የቶሴሊ ክህሎት ግን የተለየ ስለነበር ተቀበሉት። ከሦስት ዓመት ተከታታይ ሥልጠና በኋላ 1878 መድፈኛ በመሆን ተመረቀ።

በጣሊያን ቆይታው ለስምንት ዓመታት ያህል ምንም የወታደራዊ ማዕረግ ዕድገት ያላገኘው ቶሴሊ ከጣሊያን ውጪ በሚገኙ ቅኝ ግዛቶች የመሥራት ፍላጎት አደረበት። አገሩ ጣሊያን በ1885 ምፅዋን ስትቆጣጠር ጀምሮ ወደ ቀይ ባሕር አካባቢ ለመሄድ አለቆቹን ይወተውት ነበር። በመጨረሻም በ1888 እግሩ ምፅዋን ረገጠ።

በኤርትራ ቆይታው ከፍተኛ ስኬት መጎናጸፍ ቻለ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ የደረጃ እና የደሞዝ ዕድገትም አገኘ። በኤርትራ ይሳካለት እንጂ በአገሩ ጣሊያን ከፍተኛ የፀረ-ቅኝ ግዛት ተቃውሞ ተፈርሞ ነበር። በ1890ዎቹ ወደ ጣሊያን በማምራት ስለ ምሥራቅ አፍሪካ የቅኝ ግዛት ዕድል ለማብራራት ሞክሯል። የሮምን ቀደምት ገናናነት ለመመለስ መራራ ትግል፣ የተግባር ውሳኔ እና ፈጣን እርምጃ እንደሚያስፈልግም ‹‹ፕሮ አፍሪካ ኢታሊካ›› በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፉ ለጣሊያናውያን መልዕክት ለማስተላለፍ ሞክሯል።







*ምስል፦ ፒየትሮ ቶሴሊ እና ጓደኞቹ (ጥር 5 ቀን 1895)*

ኮአቲት እና ሰንአፈ ላይ መንገሻን በ1895 ድል መንሳት የቻለው ቶሴሊ ጦሩን ወደ መሃል ትግራይ ለመግፋት ወሰነ። በወቅቱ በአውሮፓውያን ዘንድ የነበረው ዕምነት ትግራይ በምኒልክ ላይ በቀላሉ ለማመፅ የተዘጋጀ እንደሆነ ነበር። በዚህ የተገፋፋው ቶሴሊ በትግራይ ይኖራሉ በማለት የገመታቸውን አማፅያን በማስተባበር ቀጠናውን ለማተራመስ አቀደ። በመጀመሪያ እርምጃውም ሼህ ታላ የተባሉ የጎሳ መሪን መልምሎ ሥራውን ጀመረ።



Pietro Toselli and friends. From *L'Illustrazione italiana*, 5 January 1896

ምስል፡- ፒየትሮ ቶሴሊ እና ጓደኞቹ (ጥር 5 ቀን 1895)

ቶሴሊም ሆነ ሌሎች አውሮፓውያን የተሳሳተ ግምት እንደነበራቸው የተረዱት የጣሊያን እና የሺህ ታላ ጥምር ኃይል አምባ አላጌ ላይ ብርቱ የመከላከል ውጊያ ሲገጥመው ነበር። የሕዝቡን ተቃውሞ ችላ በማለት ኹለት ሺህ አባላት የነበሩትን ሠራዊት አምባላጌ ላይ በማስፈር ነበር ቶሴሊ የምኒልክን ሠራዊት ለመጠበቅ የወሰነው።

ከዐሥር ሺህ ሜትር የሚበልጥ የባሕር ጠለል ከፍታ ያለው አምባላጌ ተፈጥሮአዊ ምሽግ ነበር። ከወታደራዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ በሸዋ እና ትግራይ መገናኛ መንገድ ላይ መገኘቱ ልዩ ጠቀሜታም ነበረው። አምባአላጌ ላይ የመሸገው ቶሴሊ ተልዕኮው ምን እንደሆነ ግልጽ አልነበረም። ለመኾኑ የምኒልክ ጦር አምባ አላጌ ሲደርስ ይገጥመዋል ወይስ በዝምታ ያልፈዋል? ያልተመለሰ ጥያቄ ነበር።

ከአምባላጌ በስተሰሜን ሠላሳ አምስት ማይል ርቆ ከነበረው አለቃው አሪሞንዲ ጋር መልዕክት በመለዋወጥ ቶሴሊ በአምባ አላጌ መሽጎ ቆየ። ከወራት በኋላ ግን የኹለቱ የጣሊያን መኮንኖች ግንኙነት ሻከረ። ቶሴሊ በሚያዝያ ወር በሮም በጻፈው ደብዳቤ ከአሪሞንዲ ጋር መግባባት አለመቻሉን አሳውቆ ሰኔ ላይ ሙሉ በሙሉ ግንኙነቱን አቋረጠ።

የቶሴሊ ኹለት ሺህ ሠራዊት ከግዙፉ የምኒልክ ጦር ጋር ሲነፃፀር ዐይን ውስጥ ቢገባ የማይቆረቁር ጉድፍ ያህል ነበር። ቶሴሊ የመሸገበትን የአምባላጌ አካባቢ ለማስለቀቅ ምኒልክ አይዋጉም። ግዙፍ ጦራቸው ቶሴሊን አምባላጌ ላይ አልፎ በመሄድ የግንኙነት መስመሩን ቢዘጋበት ከቀናት በኋላ ሠራዊቱ በቀላሉ እንደሚያልቅ ግልጽ ነበር።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ምኒልክ አምባ አላጌን ለሌላ ዓላማ ሊጠቀሙበት ወሥነው ነበር። በበርካታ አውሮፓውያን ምኒልክን እንደሚከዳ የተነገረበት ራስ መኮንን የሚፈተኑበት ቦታ ነበር - አምባ ላጌ። ይህንን ጥርጣሬ ለማረጋገጥም ምኒልክ





ጦሩን ከፊት እንዲያስቀድም መኮንንን አዘዙት። መኮንን የጣሊያን ወዳጅ ሆኖ ምኒልክን የሚከዳ ከሆነ ብቸኛው መፈተኛ ሊሆን የሚችለው ሠራዊቱን ከጣሊያን ሠራዊት ጋር ማፋጠጥ እንደሆነ ነበር አፄ ምኒልክ የወሰኑት።

### የጣሊያን ከቅዠቷ መባነን

የመኮንን ሠራዊት አምባ ላጌ ደርሶ ሲመለከት ነበር ቶሴሊ አገሩ ከማትችለው ባላጋራ ጋር መጋጨቷ የተገለጠለት። ስለ ምኒልክ ዘመቻ አዲስ አበባ ከሚገኘው የጣሊያን ስለላ ቡድን የደረሰው መረጃ ጦሩ በኹለት ቡድን የዘመተ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን ዐሥራ ኹለት ሺህ ሠራዊት ብቻ እንደነበረው ይገልፃል። ንጉሥ ተክለኃይማኖት በማመፁ ምኒልክ ወደ ጎጃም እንደዘመተ እና የራስ መኮንን ጦር ብቻውን ወደ ሰሜን መንቀሳቀሱን በተመለከተ የተሳሳተ መረጃ ነበር ቶሴሊ የደረሰው።

መንገሻ፣ አሉላ፣ ተክለኃይማኖት እና መኮንን የከዷቸው አፄ ምኒልክ ከመንደራደር ይልቅ ሠራዊታቸውን ለማንቀሳቀስ እንደማይሞክሩ ነበር የጣሊያን ግምት። ግምቷን ያጠናከረላት ደግሞ በተደጋጋሚ ጦሯ ወደ ትግራይ ሲገባ የምኒልክ ምላሽ አለመስጠት ነበር።

ጣሊያን የተሳሳተ ግምት በመያዝ ምኒልክን እንደ ፈሪ ብትመለከትም የምኒልክ ዝምታ ግን ምክንያታዊ ነበር። በ1890 ትግራይን በመቆጣጠር በሥርዓተ ንግሥናቸው ወደ አክሱም እንዲመጡ ጣሊያን ስትጋብዛቸው አፄ ምኒልክ አልተቀበሉም። በ1894 ጣሊያን አድዋን በመቆጣጠር መንገሻን ለምኒልክ ለማስረከብ ያደረገችውንም እንቅስቃሴ ምኒልክ በጥሞና ነበር የተመለከቱት።

የጣሊያን የተሳሳተ ግምት እንዳለ ሆኖ በ1895 ነገሮች በሙሉ የተለየ መልክ ያዙ። መንገሻ እና አሉላ እንዲሁም የቀሩት የትግራይ መሳፍንት እና ኀበዛዝት ከምኒልክ ጎን በመሰለፍ አገራቸውን ከጣሊያን ለመከላከል ወሰኑ።

ቶሴሊ የጠበቀው መካከለኛ መጠን ያለው ሠራዊት ነበር። በመንገሻ ወይም በራስ ወሌ የሚመራ 4500 ጦር ሲጠብቁ የነበሩት የቶሴሊ ወታደሮች አምባላጌ ላይ ሆነው ቀልቀል የተመለከቱት ሠራዊት ከቅዠታቸው አባነናቸው። ቁጥሩ ከአርባ ሺህ የሚልቀውን የራስ መኮንን ጠንካራ ሠራዊት ተመልክቶ ነበር ቶሴሊ ለፀበኛ አለቃው አስቸኳይ ደብዳቤ የጻፈው። ‹‹እጅግ በጣም ብዙ ናቸው›› በማለት ቢፅፍም የተመለከተው የአፄ ምኒልክን የፊት ተሰላፊ ሠራዊት ብቻ መኾኑን ግን አላወቀም ነበር።

ታኅሳስ 5 ቀን ራስ መኮንን አምባላጌ ደርሰው ለቶሴሊ በጻፉት ደብዳቤ ይዞታውን በፍጥነት ለቅቆ ካልወጣ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደዱ ገለፁ። የራስ መኮንን ደብዳቤ እጅግ የተለሳለሰ እና በምኒልክ አስገዳጅነት የዘመቱ መሆናቸውን የሚገልፅ ዓይነት ነበር። ‹‹የንጉሡ ጦር ከኋላዬ እየተከተለኝ ሲሆን አሸንጌ ሐይቅን አልፈዋል። እዚህ የምቆም ከሆነ ከኋላዬ ይደርሱብኛል›› በማለት ነበር ራስ መኮንን ለቶሴሊ የፃፉት።

ቶሴሊ የመኮንን ጦር በመግጠም ራሱን ለሞት አሳልፎ መስጠት እንደሌለበት ገብቶታል። ከመኮንን ደብዳቤ መንፈስ የተረዳው ራስ መኮንን በምኒልክ ግፊት መዝመታቸውን ነበር። በተጨማሪም በ1889 ጣሊያንን በመጎብኘት ብርቱ ወዳጅነት መመስረታቸውንም ሲጠቀምበት ወሰነ። ለራስ መኮንን በጻፈው ምላሽ ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት አፄ ቴዎድሮስ እና መንገሻ ከአውሮፓውያን ጋር በመፋለም የተሸነፉባቸውን የመቅደላ እና ሰዓቲ ውጊያዎች በመጥቀስ በዚህኛው ጦርነት ምኒልክ ቢሸነፉ በጣሊያን ወዳጅነት መንበረ-ሥልጣኑን እንደሚይዙ በመግለፅ ሊያማልላቸው ሞከረ።

ራስ መኮንንን ለማግባባት ቢሞክርም በውስጡ ግን ከፍተኛ ፍርሃት እንደነገሰበት ነበር። አምባላጌ ከቶሴሊ ጋር የነበረው ሌላ የጣሊያን ወታደር ሉጂ ካኖቬቲ ለእህቱ ማርያ በጻፈው ደብዳቤ የመኮንንን ሠራዊት ግዙፍነት ጠቅሷል። ‹‹እኛ





*አንድ ሺህ ስንሆን እነርሱ 20 ሺህ ናቸው። ስማችን በታሪክ መዛግብት እንደሚፃፍ ተሰፋ አለኝ። ከዚህ የበለጠ ሽልማት የምናገኝ ግን አይመስለኝም።››*

ቶሴሊ ከፊቱ በነበረው የመኮንን ሠራዊት መበለጡን ቢረዳም አምባ ላጌን ለቆ ለመውጣት ግን የጀነራል አሪሞንዲን ትዕዛዝ መጠበቅ ነበረበት። ቶሴሊ እጅ ባይደርስም ጀነራሉ እንዲወጣ የሚያዝ ደብዳቤ የጻፈለት ቀድሞ ነበር። ቶሴሊ በመጨረሻው ምሽት አምባ ላጌ ከሚገኘው የማደሪያ ድንኳን ለጀነራል አሪሞንዲ የጻፈው ደብዳቤ በከፊል እንዲህ ይነበባል፡-

> *በዚህ ምሽት ከስሬ የመሸገው የጠላት ጦር ያቀጣጠለው እሳት ይታየኛል። የጠሩ ካምፕ መንገሻ ከአቲት ሳይ ከገነባው እጅግ ይበልጣል። በጊዜ ወደ ኋላ በመመለስ ሃይላችንን ማሰባሰብ ይኖርብናል። ካልሆነ ግን መላው ኤርትራን ለመከላከል አንችልም።*

ይህ ደብዳቤ ለቶሴሌ የመጨረሻው ነበር።

ታኅሳስ 6 ቀን የኢትዮጵያ ጦር ለውጊያ ተዘጋጀ። በዕለቱ ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት አካባቢ የጀነራሉን ምላሽ ቶሴሊ ጋር ደረሰ። ስድስት የእግረኛ ሠራዊት ባታሊዮን እና ኹለት መድፈኛ ቡድን እንዲላከለት እና ታኅሳስ ሰባት በማለዳ እንደሚደርሱ አሳወቀው። ቶሴሊም አጠራጣሪውን ደብዳቤ ተመልክቶ ከማፈግፈጉ በፊት ሀሳቡን ቀየረ።

ታኅሳስ 7 ቀን ከጠዋቱ 12:30 የመኮንን ሠራዊት ማጥቃት ጀመረ። ራስ መኮንን ቀድሞ ባደረጉት ጥናት አንድ ሺህ ሦስት መቶ ቅጥረኛ አስካሪ(የባንዳ) ወታደሮችን የያዘው አራተኛ የጣሊያን ባታሊዮን ጠንካራ እንደሆነ አውቀዋል።

ከቅጥረኞቹ በተጨማሪ ቁጥሩ ከ350 የሚልቅ የራስ ስብሃት እና ሺህ ታላ ወታደርም ከጣሊያን ጎን ተሰልፏል። ራስ መኮንንም የኹለቱ ባንዳዎች ጦር ላይ አተኮሩ።

ቶሴሊ በዙሪያው የተወሰኑ ታማኝ አስካሪዎችን በማቆም ለራሱ ልዩ መከላከያ አደረገ። የራስ ስብሃትን ጦር ቀድሞ በማዝመትም ሞቱን ለማራዘም ተጣጣረ። የስብሃት ጦር በግራ የሺህ ታላ ደግሞ በቀኙ ሆነው ከአምባላጌ ወደ ቶጎራ የሚወስደውን መንገድ ዘጉት። ከኹለቱ ጀርባ ደግሞ በሌተናንት ጀነራል ቦልፒቼሊ የሚመራ የኤርትራ ምልምል ሠራዊት ተሰለፈ። በቶሴሊ የሚመራው አራት መድፍ ደግሞ በመሃል ሆኖ አምባውን ያዘ።

ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ መኮንን ጥቂት ወታደሮችን በቀኝ መስመር ወደነበረው የሺህ ታላ ሠራዊት በመላክ በቀላሉ ደመሰሱት። በግራ የተሻለ ይዞታ የነበረውን የራስ ስብሃት ጦር እንዲደመሰስ ራስ ወሌ ሰባት ሺህ ወታደሮቹን እንዲያንቀሳቅስ አዘዙት። ኹለት ሰዓታት የፈጀው የወሌ እና ስብሃት ጦርነት ሲጠናቀቅ የባንዳው ሠራዊት ሙሉ በሙሉ ተደምስሶ ነበር።

ሦስት ሰዓት አካባቢ ራስ መኮንን የሚመሩት 15 ሺህ ሠራዊት በቀጥታ ወደ ቶሴሊ የመድፍ አጥር ገሰገሰ። የቶሴሊ መድፈኞች የሚተኩሱት ጥይት በአየር ላይ በመፈንዳት ከሥር የነበሩትን የመኮንን ሠራዊት በፍንጥርጣሪው ጎዳቸው። መሬት ደርሰው የፈነዱትም ከፍተኛ ጉዳት አስከተሉ።

አራት ሰዓት ከመኾኑ በፊት በመንገሻ እና አሉላ የተመራው ዐሥራ ሦስት ሺህ ጦር አምባላጌ ደርሶ የጣሊያንን ሠራዊት በቀኝ በኩል ማጥቃት ጀመረ። በውጊያ ውሎው ግራ እና ቀኝ የነበሩትን መንቀሳቀሻ ሙሉ በሙሉ በመዝጋት የቶሴሊን ጦር መሃል ላይ በመክበብ ራስ መኮንን የውጊያ ስልታቸውን ውጤታማነት አስመሰከሩ።





ቶሴሊ ወደ መቀሌ ሊሸሽ የሚችልበትንም ሰሜናዊ አቅጣጫ በመያዝ መፈናፈኛ አሳጡት።

በኢትዮጵያ ጦር ብዛት እጅግ የተበሳጠው ቶሴሊ ጀነራል አሪሞንዲ የላከለት ደጀን እስኪደርስ ድረስ ለመዋጋት ወሰነ። በፍጥነት ወደ አምባው በመውጣትም ገዢ መሬት ያዘ። ከዓምባው ላይ ቁልቁል በመተኮስም በርካታ ኢትዮጵያውያን ሙት እና ቁስለኛ አደረገ።

ስድስት ተኩል ሲሆን የተባለው ድጋፍ እንደማይደርስ የተረዳው ቶሴሊ ለማፈግፈግ ወሰነ። የአምባውን ጫፍ በመልቀቅ መሸሽ የጀመረው የቶሴሊ ቀሪ ሠራዊት በኢትዮጵያ ተበለጠ። በርካታ የጣሊያን ወታደሮች እና የጋማ ከብቶቻቸው ራሳ አምባውን ሞላው። የተወሰኑ ወታደሮችም ከአምባው ላይ እየወደቁ ወደ ገደል ሲገቡ ታዩ። የሌተናንት ማርዚዮ ማንፍሬዲኒ በቅሎ በጥይት ተመትቶ ተንገዳገደ እና ጌታውን እንደጫነ ወደ ገደል ወረደ።

ሰባት ሰዓት ላይ ጦርነቱ ሙሉ በሙሉ ተጠናቀቀ። ከአምባው ውጊያ የተረፉት ወታደሮችም ሽሽታቸውን ቀጠሉ። የተረፈው የጠላት ጦር አምባውን ለቅቆ ወደ መንደር ሲጠጋ የአገሬው ገበሬ በጥይት ተቀበለው።

### ታሪክ የቀየረው የአምባላጌ ውሎ

ለጣሊያን እና ወዳጆቿ የአምባ ላጌ ውሎ ጀግንነት የፈፀሙበት እንደሆነ ነበር የተገለጸው። ቶሴሊ በጀግንነት ከበርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር መዋደቁን መላው አውሮፓ አወራለት። የጀርመን፣ አስትሪያ እና ፈረንሳይ ጋዜጦችም የጣሊያን ሠራዊት በአምባላጌ የፈፀመውን ጀግንነት አናፈሱ።

በጣሊያን በተለይ የተደበላለቀ ስሜት ነበር የተፈጠረው። የቅኝ ግዛት ዘመቻውን በመቃወም ይታወቅ የነበረው የጣሊያን ምክር ቤት በበቀል ስሜት

ተገፋፍቶ ለቀጣይ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ እንዲመድብ ጠየቀ። መንግሥትን በመቃወም የሚታወቀው ‹‹ኮሪየሬ ዴላ ሼራ›› ጋዜጣ በበኩሉ ወረራውን ‹‹እብደት›› በማለት አውግዞታል። የሮም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመንግሥታቸው ላይ ተቃውሞ በመውጣት ‹‹ቪቫ ምኒልክ!›› በማለት የኢትዮጵያውያን ንጉሥ ሲያወድሱ ተደምጠዋል። የተማሪዎቹ ተቃውሞ ምናልባትም በአውሮፓ ታሪክ በዓይነቱ የመጀመሪያ ሳይሆን አይቀርም።



*ምስል፦ የአምባ ላጊ ጀግና ራስ መኮንን (ከሌ ፔቲት ጋዜጣ ታኅሣስ 29 ቀን 1896)*






የአምባላጌው ድል ለኢትዮጵያ ከፍተኛ መነሣሣትን በመፍጠር ለአድዋ ድል አስተዋፅኦ አድርጓል። በራስ መንገሻ ፈጣን ሽንፈት ኢትዮጵያን ዝቅ አድርገው የገመቱ አውሮፓውያንም ከአምባላጌ በኋላ ግምታቸውን ለማስተካከል ተገድደዋል።

የአምባላጌውን ድል ምኒልክ የሰሙት ዓላማጣ ሳሉ ነበር። የድሉን ዜና ለማብሰር ሌሊቱን ሙሉ ሲጋልብ ዓላማጣ የደረሰው መልዕክተኛ መንገድ ላይ ላገኛቸው የምኒልክ ሠራዊት አባላት ዜናውን አበሰረ። ወታደሮቹም ዜናውን ሰምተው በማዘን ‹‹ይሄንን ኹሉ መንገድ ተጉዘን የመጣነው ሳንዋጋ ለመመለስ ነበር?›› በማለት እርስ በእርስ ተያዩ።

በምኒልክ ላይ አምፀው የነበሩ በርካታ የአገር ውስጥ ኀበዛዝት እና መሳፍንትም የአምባላጌውን ድል ከሰሙ በኋላ ከምኒልክ ጎን ቆሙ። ዋፍላ ላይ በጊዜያዊነት ያረፉት አፄ ምኒልክ በርካታ አማፅያንን ተቀብለው ከጦሯቸው ጋር ቀላቀሉ። የጎጃሙ ንጉሥ ተክለኃይማኖትም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር ለምኒልክ የላኩት የአምባ ላጌውን ዜና ከሰሙ በኋላ ነበር።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አምባ ላጌ የተለየ ስፍራ ይዟል። የደቡብ እና ሰሜን ኢትዮጵያ ሠራዊት በመተባበር የጋራ ጠላታቸውን ለመደምሰስ የተዋጉበት ግንባር ነው፤ አምባ ላጌ። ከኹሉም በላይ ግን የፖለቲካ ልዩነት የከፋፈላቸው የአገሪቷ ኀበዛዝት ውስጣዊ ችግራቸውን ለጊዜው በመተው ባጋራ አገራቸውን የተከላከሉበት የተለየ ታሪክ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ከአምባላጌ ወደ አድዋ ያደረገው ጉዞ በወኔ የተሞላ ነበር። ጦር ሠራዊቱ ከውጊያ በፊት ድሉን ያረጋገጠ ይመስል ነበር። ለመኾኑ ማነው? የሞግዚት አስተዳዳሪ? ለማስተዳደር የመጣው ጦር በሚተዳደር ተሸንፎ የለምን?



Makonnen, the hero of Amba Alage. From *Le Petit Journal*, 29 December 1895.

ምስል፡- የአምባ ላጌ ጀግና ራስ መኮንን (ከሌ ፔቲት ጋዜጣ ታኅሳስ 29 ቀን 1896)

## የመቀሌው ምሽግ

ቶሴሊ አምባላጌ ላይ የከፈለው መስዋዕትነት በጣሊያን እንደተሰማ ነበር በርካታ ወጣት ወዶ ዘማቾች ወደ ኢትዮጵያ ለመዝመት የተዘጋጁት። የጣሊያን መንግሥትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ አርባ ሺህ ወታደሮችን መለመለ። ከታኅሳስ 16 እስከ ጥር 5 ባሉት ቀናትም በዐሥራ አንድ መርከቦች ተጭነው ወደ ምፅዋ ጉዞ ጀመሩ። በኹለተኛው ዙር ጉዞ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ወታደሮችን እና በርካታ ቶን ትጥቅ እና ስንቅ የጫኑ የጣሊያን መርከቦች ከጥር 12 እስከ የካቲት 1 ባሉት ቀናት ጉዞአቸውን ወደ ምፅዋ ጀመሩ።

ጀኔራል አሪሞንዲ የአምባላጌውን ዜና እንደሰማ ነበር መቀሌን ለመልቀቅ የወሰነው። ነገር ግን በመቀሌ ቆይቶ የሚሆነውን ለመቀበል መረጠ። ባራቲሪ መቀሌ ላይ ምሽጉን እንዲያጠናክር ሜጄር ጋሊያኖን ላከ። የጋሊያኖ ወታደሮች ስለ አምባ ላጌው ውሎ የሰሙት ታኅሳስ ሰባት እኩለ ሌሊት ላይ ከአምባላጌ ተርፈው መቀሌ ከደረሱት የቶሴሊ ወታደሮች ነበር።

ታኅሳስ ወር ያለፈው የጣሊያን ወታደሮች ከባንዳ ቅጥረኞቻቸው ጋር በመሆን መቀሌ ላይ ምሽግ ሲገነቡ ነበር። በመቀሌ የነበሩ አብያተ-ክርስቲያናት ሳይቀሩ የጥይት እና የምግብ ማስቀመጫ ኾኑ። በአጠቃላይ ርዝመቱ 230 ሜትር፣ ከፍታው 16 ሜትር እንዲሁም እስከ ስድስት ሜትር የሚደርስ ውፍረት የነበረው ምሽግ ተገነባ። ለዋናው ምሽግ መከላከያ እንዲኾኑ በርካታ አነስተኛ ምሽጎች በዙሪያው ተቆፍረው እና ተከበውም ነበር።

በምሽግ የነበረው የጣሊያን ሠራዊት ምግብ ለማፈላለግ ታኅሳስ 9 ቀን ከምሽጉ ወጣ። የአምባላጌውን ዜና የሰማው የአካባቢው ሕብረተሰብ ለጣሊያን ስንቅ የሚሆን ነገር ላለመሸጥ ተስማምቶ ግልጽ ጥላቻውን አሳየ። የሕዝቡ ጠላትነት እየከፋ በመምጣቱ ከመቀሌው ምሽግ ወደ አስመራ ይደረግ የነበረውን ግንኙነትም አቋረጡ። በመኾኑም የጣሊያን መልዕክተኞች ምሽት እየጠበቁ ብቻ ነበር የሚንቀሳቀሱት።





ጋሊያኖ በምሽግ ያለ ሠራዊቱን ሞራል ከፍ ለማድረግ ሲል ወይን፣ ቡና፣ ሲጋራ እና የተለያዩ መጠጦችን በራሽን ያደርስቻው ነበር። በሞቅታ የተበረታቱ የጣሊያን ወታደሮች በልቡሙሉነት የኢትዮጵያን ጦር እንደሚደመስሱ ይናገሩ ነበር። ይሄንን የተመለከተው ጋሊያኖ ለአለቃው ጀኔራል ባራቲሪ በጻፈው ደብዳቤ ‹‹የሠራዊቱ የውጊያ ሞራል ከፍተኛ ነው›› ብሎ ነበር።

ታኅሳስ 19 ቀን ከጠዋቱ 4 ሰዓት አካባቢ የጣሊያንን ሠራዊት ስሜት የቀየረ ክስተት ተፈጠረ። ይኸውም ከመቀሌው ምሽግ በስተደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ከፍተኛ አቧራ ተነስቶ የመቀሌን ሰማይ እንደ ደመና ሸፈነው። አቧራውን ያሥነሳው ከአምባላጌ ወደ መቀሌ በመገስገስ ላይ የነበረው የራስ መኮንን እግረኛ እና ፈረሰኛ ሠራዊት ነበር። ሠራዊቱ የጣሊያንን ምሽግ ለመከበብ አመቺ በሆነው የምሽጉ ሰሜናዊ አቅጣጫ ከፍታ ቦታ ላይ ሰፈረ። ሠራዊቱ የያዘው ቦታ የጣሊያን ሠራዊትን የግንኙነት መስመር እንዲሁም የማምለጫ መንገድ ለመዝጋት አመቺ ነበር።

ራስ መኮንን ጦራቸውን ቦታ ባስያዙ በኹለተኛው ቀን ለጋሊያኖ ደብዳቤ ፃፉለት። ራስ መኮንን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሠራዊት እና ከጋሊያኖ ሠራዊት የተሻለ ገዢ ቦታ ይዘው ሳለ ለጋሊያኖ የፃፉት ደብዳቤ የተለሳለሰ መኾኑ አስገራሚ ነበር። የራስ መኮንን ደብዳቤ እንደሚከተለው ይነበባል፦

> *እንደምን አሉ? ለፈጣሪ ምስጋና ይድረሰውና እኔ ከነመላው ሠራዊቴ በጣም ደህና ነኝ። የእርስዎስ ወታደሮች እንዴት ናቸው?*
>
> *ከሰላምታዬ በመቀጠል የምገልፅልዎ ነገር ቢኖር ጦርዎ የመሸገበትን ቦታ ለቅቆ እንዲወጣ በንጉሡ ነገሥቱ ስም አጠይቅዎታለሁ። የክርስቲያን ደም እንዲፈስ ፈፅሞ አልሻም እና ሠራዊትዎን ይዘው ይውጡ ዘንድ አጠይቃለሁ።*
>
> *ወዳጅዎ መኮንን*

ጋሊያኖ የራስ መኮንንን ደብዳቤ የተመለከተው በጥርጣሬ ነበር። የመኮንን ጥያቄ እና መሰሳሰስ የምኒልክ ሠራዊት እስኪደርስላቸው ጊዜ ለመግዛት የታለመ ነበር የመሰለው። ጋሊያኖ የጻፈው ምላሽም የሚከተለው ነበር።

> *ተጻፈ ለራስ መኮንን፣ የሸዋ ጦር የፊት አዝማች፣ ከመቀሌ ምሽግ ለዛሬ። እንደምን አሉ? እኔ ከነመላ ሠራዊቴ ደህና ነኝ። ወታደሮችም ደህና እንደሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። ለጥያቄዎ ምላሽ ይሆን ዘንድ በንጉሴ ስለታዘዝኩ በታውን ለቅቄ እንደማልወጣ ላሳውቅዎት ይገባል። ማድረግ ያለብዎን ያድርጉ። ሠራዊቴ ዘመናዊ ጠመንጃ እና በንብዎ መታጠቁን ላስታውስዎት።*
>
> *ወዳጅዎ ጋሊያኖ*

ራስ መኮንን ታኅሣስ 25 ቀን ኹለተኛ ዙር ደብዳቤ ቢፅፉም ከጋሊያኖ የተለየ መልስ አላገኙም። ታኅሳስ ሠላሳ ቀን ሦስተኛ ደብዳቤአቸው ከነጭ መሃረብ ጋር በወታደር አስይዘው ወደ ጋሊያኖ ምሽግ ላኩ።

በሦስተኛው ደብዳቤ ጋሊያኖን የጠየቁት ቁስለኛ ወታደሮቻችን የሚያክምላቸው ሃኪም እንዲልክላቸው ነበር። ጋሊያኖም የካምፑ ሐኪም የነበረው ሞዜቲን ወደ ራስ መኮንን በመላክ ለአንድ ቀን የሕክምና አገልግሎት ሰጥቶ ወደ ካምፑ ጊዮርጊስ ከተባለ የራስ መኮንን ወታደር ጋር ተመለሰ።

ሞዜቲ ምሽጉ እንደደረሰ ለጋሊያኖ ስለ ራስ መኮንን ሠራዊት ብዛት አብራራለት። ሞዜቲን አጅቦ የመጣው ጊዮርጊስ በምሽጉ ግብዣ ተደርጎለት የነበረ ሲሆን ብዙ ብራንዲ ከጠጣ በኋላ መለፍለፍ ጀመረ። 100 ሺህ ሠራዊት ያለው





የምኒልክ ጦር በመምጣት ላይ መኾኑን፣ ጦሩ መድፍ መታጠቁን እና ምኒልክ ምፅዋ ቤተ-መንግሥት ተቀምጦ ጠጅ እንደሚጠጣ መዛቱን ጊዮርጊስ ለጋሊያኖ ዘከዘከ። ጋሊያኖም የምኒልክ ፍላጎት ትግራይን ማስለቀቅ ብቻ ሳይሆን ጣሊያንን ከመላው አፍሪካ ነቅሎ ማስወጣት እንደሆነ ተገለጠለት።

የራስ መኮንን ጦር የማጥቃት እርምጃ ሳይወስድ ለቀናት በዝምታ መቀመጡ ጋሊያኖን አጠራጠረው። ጥር 1 ቀን የመኮንን ሠራዊት የጋሊያኒን ምሽግ ከብቦ ጨረሰ። ጥር 3 ቀን ለጋሊያኒ በጻፉት የመጨረሻ ደብዳቤ ራስ መኮንን «በአምባላጌ የቶሴሊን መጨረሻ አስታውስ። ምሽጉን አስረክበኝ፣ ተጨማሪ ደምም አታፍስስ። ይህንን ብታደርግ ከነሙሉ ንዝህ እስከ ምጽዋ ድረስ ልሸኝልህ ቃል እገባልሃለሁ።» በማለት ከረር ያለ መልዕክት አስተላለፉ።

### የበዓለ-ጥምቀት ስልፍ

ጥር 6 ቀን ከጻፈው የግል ማስታወሻ ጋር በማያያዝ ጋሊያኖ ስለ በዓለ-ጥምቀት ፅፎ ነበር። በዕለቱ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ወታደር ከምሽጉ በተቃራኒ አቅጣጫ ሲተምም መመልከቱን እና ወታደሮቹም የምኒልክ መሆናቸውን ከራሱ ሠራዊት ማረጋገጡን ጋሊያኖ ፅፎ ነበር። «የምኒልክ ቀይ ድንኳን ከፊት በመሆን ወታደሩን አስከትሎ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ አለፈ።»

በጥምቀት ማግስት የምኒልክ ሠራዊት ማረፊያ በታውን ያዘ። ጣይቱ ብጡል ከአንዱ ሰሜናዊ ርስታቸው ያስመጡትን ከፍተኛ መጠን ያለው ቅቤ፣ በርካታ የቀንድ ከብት እና ከአምስት መቶ በላይ በጎች ለሠራዊቱ ስንቅ አከፋፈሉ። የስንቅ እደላው ወታደሩ ለቀጣይ ትዕዛዝ ዝግጁ እንዲሆን ያመላከተ ነበር። የመቀሌው ጥቃት ሊጀመር ተቃርቧል።

የኢትዮጵያ ጦር ጥር 7 ቀን ከዋናው የጣሊያን ምሽግ ራቅ ያሉ ኹለት የቅኝት ማማዎችን በማጥቃት ነበር የጀመረው። ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ሠራዊት ፈጣን እና የተቀላጠፈ የጥቃት እርምጃ ተገረሙ። በመጀመሪያው የውጊያ ውሎ ቀድሞ ቦታ የያዘው የጣሊያን ሠራዊት በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮችን ገደለ። ለዕለቱ ከፍተኛ ኪሳራ ጣይቱ፣ አሉላ፣ መንገሻ እና ምኒልክ ተጠያቂ ያደረጉት ራስ መኮንን

ነበር። ለቀናት በመደራደር ባባከኑት ጊዜ ጣሊያን ምሽጉን እንዲያጠናክር በቸልታ መመልከታቸው ተገቢ እንዳልነበረም ወቀሱ። በሁኔታው የተበሳጩት አፄ ምኒልክም ለቸልታቸው መቀጫ ይሆን ዘንድ ራስ መኮንን የራሳቸውን ወታደሮች በማስቀደም ምሽጉን እንዲሰብሩ አዘዙ።

ጥር 8 ቀን የኢትዮጵያ መድፍ የጣሊያንን ምሽግ ሲደበድብ ቢውልም ምሽጉን ለመስበር ግን አልቻለም። የኢትዮጵያ ሠራዊት በአጠቃላይ ዐሥራ ኹለት መድፍ ያሰለፈ ሲሆን ኹለቱ ከአምባላጌው ውጊያ በምርኮ የተገኙ ነበሩ። የመድፈኞቹን የተስተካከለ ዒላማ የተመለከተው ጋሊያኖ «የኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይሆን አውሮፓውያን መሆን አለባቸው» በማለት ተደንቆ ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት የታጠቀው ሆች ኪስ መድፍ ከጣሊያን መድፍ የተሻለ ጥራት የነበረው ሲሆን የተሻለ ርቀት ይሸፍናል።



Makonnen's forces attack Mekele. From L'Illustrazione italiana, 2 February 1896.

*ምስል፦ የመኮንን ሠራዊት የመቀሌን ምሽግ ሲያጠቃ (ከ ላ ኢሉስትራዚዮኔ ኢታሊያና፣ ጥር 2 ቀን 1896 የተወሰደ)*






ጥር 9 ቀን የራስ መኮንን ጦር በምሽጉ ላይ መጠነ-ሰፊ የማጥቃት ዘመቻ ከፈተ። ነገር ግን ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢትዮጵያ ወታደር አለቀ። በዕለቱ በተከሰተውም እልቂት ጣይቱ እና ምኒልክን ጨምሮ ንጉሥ ተክለኃይማኖት እና አቡነ ማቴዎስ ራስ መኮንንን በአገር ክህደት ተግባር ወቀሱት። በእልቂቱ ልባቸው የተሰበረው ራስ መኮንን «ታማኝነቴን እንዴት ላረጋግጥ እችላለሁ?» በማለት አምርረው ጠየቁ። በወቅቱ የተሰጣቸው ምላሽ «ምሽጉን እንዲገነቡ ጊዜ የሰጠሃቸው አንተ ነህ። ስለዚህ ምሽጉን ማፍረስም ያንተ ኃላፊነት ነው» የሚል ነበር።

ጥር 10 ከእኩለ ሌሊት በኋላ በእልህ የተሞሉት ራስ መኮንን ሦስት ተከታታይ ጥቃት ሰነዘሩ። በስድስት፣ ስምንት እና ዐሥር ሰዓት ያደረጓቸው የማጥቃት ሙከራዎች ስኬታማ አልነበሩም። የጣሊያን ጦር በአብሪ ጥይት ታግዞ የራስ መኮንን ጥቃት መከተ። ራስ መኮንን ጥር 11 ቀን ሠራዊታቸው ለምሽጉ መውጣጫ የሚሆን መሳላል እንዲያዘጋጅ አዘዙ። ከሌሊቱ 9 ሰዓት ጭለማውን አስታከው ሠራዊታቸውን ወደ ግምቡ አስጠጉ።

መጀመሪያ ላይ በቀላሉ ግንቡን መወጣጣት የጀመሩት የራስ መኮንን ወታደሮች የጣሊያንን ምላሽ ማስተናገድ የጀመሩት በአስገራሚ ሁኔታ ነበር። ንጋት ሲቃረብ ከስድስት መቶ በላይ የመኮንን ወታደሮች የምሽጉ ግድግዳ ሥር ተዘርረው ነበር። የወታደራቸውን ከፍተኛ ሞት የሰሙት ራስ መኮንን በቀጥታ የገሰገሱት ወደ ምሽጉ ነበር። ራሳቸውን ለጣሊያን ጥይት አጋልጠው ለሞት የተዘጋጁትን ራስ መኮንን የታደጋቸው ራስ አሉላ ነበር። በተደጋጋሚ ሲወቅሳቸው የነበረው ራስ አሉላ በመጨረሻም ነፍሳቸውን መታደጉ ጨዋነቱን ነበር ያሳየው።

ጥር 11 ቀን በምኒልክ ዘመቻ ጥቁር ቀን ነበር። በአምባላጌው ድል ወኔው ተነሳስቶ የነበረው ሠራዊታቸው በመቀሌው ውጊያ ከፍተኛ እልቂት አጋጠመው። ይህንን ተከትሎም በጦራቸው ላይ ከፍተኛ የውጊያ ሞራል ውድቀት ተመለከቱ።



Makonnen's forces attack Mekele. From *L'Illustrazione Italiana*, 2 February 1896.

ምስል፡- የመኮንን ሠራዊት የመቀሌን ምሽግ ሲያጠቃ (ከ ላ ኢሉስትራዚዮኔ ኢታሊያና፣ ጥር 2 ቀን 1896 የተወሰደ)

ምኒልክ እና ራስ መኮንን በንጉሡ ድንኳን ውስጥ ፊት ለፊት ተቀምጠው ተሳቀሱ። ከድንኳኑ ውጪም የሴቶች የለቅሶ ድምፅ ይሰማ ነበር።

‹‹ይህ ቀን ለኢትዮጵያ ጥቁር ነው።›› በማለት ለቅሶአቸውን አቁመው ነበር አፄ ምኒልክ ራስ መኮንንን እሥነስተው ያቀፉት። ‹‹ይህ ታማኝ ታዛገር ነው›› በማለትም ለከፍተኛ ሹማምንቶቻቸው የራስ መኮንንን ታማኝነት መሰከሩላቸው። የአፄ ምኒልክ ምስክርነት የራስ መኮንንን ተደጋጋሚ ወቀሳ እና ውንጀላ በመጨረሻም አስቆመ።

በመጨረሻም አፄ ምኒልክ የማጥቃት እርምጃው እንዲቆም አዘዙ። መቀሌ ያለ ምንም መስዋዕትነት ከጣሊያን እጅ የምትወጣበት አንድ አማራጭ ነበር።

የጣሊያን ምሽግ በኹሉም ረገድ እንከን የለሽ አልነበረም። ቋሚ የውሃ አቅርቦት አልነበረውም። የሠራዊቱ ብቸኛ የውሃ አቅርቦት የነበሩት ኹለት ምንጮች ከምሽጉ ውጪ ግራና ቀኝ የሚገኙ ሲኾኑ ከርቀታቸው አንፃር ከምሽጉ ሆኖ ለመከላከል አይቻልም ነበር።

ይህንን ችግር የተረዳው ካፒቴን ቶርኩአቶ ቤኑቺ ምሽግ ውስጥ ኹለት የውሃ ጉድጓድ ያስቆፈረው የምኒልክ ጦር ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት ነበር። እያንዳንዳቸው 13 ሺህ ጋሎን ውሃ መያዝ የሚችሉ ኹለት ጉድጓዶችን ምሽግ ውስጥ በማስቆፈር በውሃ እንዲሞሉ ተደረገ። በመቀጠልም ለወታደሩ ውሃ በራሽን እንደሚከፋፈል ጥብቅ ማስታወቂያ ተነገረ። በራሽኑ መሠረትም ለጋማ ከብቶች በቀን አምስት ሊትር፣ ለከፍተኛ መኮንኖች ኹለት ሊትር እንዲሁም ለተራ ወታደር አንድ ሊትር ውሃ ብቻ መከፋፈል ተጀመረ።

ጥር 8 ቀን በንግሥት ጣይቱ ሃሳብ አመንጪነት የኢትዮጵያ ሠራዊት ኹለቱን ምንጮች ተቆጣጠረ። ምንጮቹ ከዋናው የምሽግ ክልል ራቅ ብለው





በመገኘታቸው የተነሣ ጣሊያኖቹ ምንጮቹን መጠበቅ አልቻሉም ነበር። በምሽግ ውስጥ የተጠራቀመው ውሃ ሲያልቅ ሲቃረብ የዕለት ራሽኑን በመቀነስ የቀረው ውሃ ለዳቦ መጋገሪያ ብቻ እንዲውል ተወሰነ። ከፍተኛ መኮንኖች በውሃ ምትክ ወይን መጠጣት ጀመሩ።

የውሃውን ምንጭ ከተቆጣጠረ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከዋናው መከላከያ አጥር ተጠግቶ ምሽግ መቆፈር ጀመረ። የመድፈኛው ብርጌድ የጣሊያን ወታደሮች በምንም ዓይነት ምሽጉን ለቀው እንዳይወጡ በጥይቱ አስቆማቸው። በጭለማ ብቻ እየተንቀሳቀሱ እስከ ዋናው አጥር የሸበ መከላከያ መጠጋት የቻሉት የኢትዮጵያ ወታደሮች በጣሊያን ምሽግ ውስጥ የነበሩትን ባንዳ ወታደሮች ማስጠንቀቅ ጀመሩ። ባንዳዎቹ ከቻሉ ራሳቸውን እንዲያተርፉ ነገር ግን ከጣሊያን ጎን ሆነው መዋጋት ከቀጠሉ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ነበር ያስጠነቀቋቸው።

በመከላከያው አጥር ውስጥ የነበሩት የጣሊያን ባንዳ ወታደሮች በውኃ ጥም መሰቃየት የጀመሩት ዕለታዊ የውኃ ራሽናቸው ወደ ኹለት ኩባያ ዝቅ እንዲል ከተወሰነበት ጥር 13 ጀምሮ ነበር። በጉድጓድ የነበረው ውኃ በርካታ ነፍሳት እና ትላትል ስለረባበት ከጥር 17 ጀምሮ ለወታደሩ ይታደል የነበረው የተበከለ ውኃ ነበር።

በኢትዮጵያ ሠራዊት ተከብቦ በምሽጉ አጥር ውስጥ የነበረው ጀነራል ጋሊያኖ ብቸኛ ተስፋው ባራቴሪ ደጋፊ ኃይል በመላክ ሊያተርፈው እ ሚችል ነበር። የባራቴሪ ኹለት ባታሊዮን ጦር ጥር 9 ቀን አዲግራት ቢደርስም ወደ መቀሌ በመዝመት የጋሊያኖን ጦር የማትረፍ ዕቅድ አልነበረውም። ባራቴሪ የአምባላጌውን ሽንፈት ደግሞ መቀሌ ላይ ማየት ካልፈለገ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ከምኒልክ ጋር መደራደር ነበር።

አፄ ምኒልክ በበኩላቸው ከጊዜ ጋር ትግል ላይ ነበሩ። የያዙትን ግዙፍ ሠራዊት ለብዙ ቀናት መመገብ አይችሉም። በመኾኑም በፍጥነት መንቀሳቀስ ካልቻሉ በርካታ ወታደሮቻቸውን በርሃብ እና ጥማት ሊያጡ ይችላሉ።

## የተራብ የይሁዳ አንበሳ ሲሳይ

ጣሊያን ለሽምግልና የመረጠችው ፒየትሮ ፌልተርን ነበር። ፌልተር ለመጀመሪያ ጊዜ በ1881 ወር ኢትዮጵያ የመጣ ሲሆን ለዓመታት በንግድ ሥራ በመቆየቱ ከጣይቱ፣ ምኒልክ እና ራስ መኮንን ጋር መቀራረብ ችሏል። ለድርድሩ አመቺ እንዲሆን ፒየትሮ ወደ ምኒልክ የጦር ሰፈር ያመራው ጀነራል ጋሊያኖን ይዞ ነበር።

ፒየትሮ በድንኳናቸው ያገኛቸው አፄ ምኒልክ በጣም ተቀይረው ነበር። በጠይም ፊታቸው ወትሮም አስፈሪ ሞገስን ይሰጣቸው የፈንጣጣ ምልክት የባሰ አፍጥጦ ይታይ ነበር። በጦርነቱ አስጨናቂነት «የበሰጠ ጠቁረው እና አስፈሪ ሆነው» እንዳገኛቸው ተናግሯል። በይሁዳ አንበሳው ፊት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው ጋሊያኒ የተቆጡት የአንበሳ ሲሳይ ሊያደርጉት እንደሚችሉ በማሳብ በፍርሃት ተብረከረከ።

ጋሊያኖ ለመብረክረኩ ምክንያት ነበረው። በመቀሌ ላለቀው በርካታ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኃላፊነቱን የሚወስደው እርሱ ነበር። «ለመኾኑ ይሄን ሰው ፊቴ ያመጣኸው ለምንድን ነው?» በማለት ነበር በቁጣ የነደዱት አፄ ምኒልክ ፌልተርን የጠየቁት። ፌልተርም በከፍተኛ ትሕትና የእርሳቸው አንድ ጀነራል በጣሊያኑ ንጉሥ ፊት ቢቀርብ በከፍተኛ አክብሮት እንደሚቀበሉት በማስታወስ ንጉሥ የንጉሥን መልዕክተኛ የሚያከብረው እንደ ንጉሥ መኾኑን በተማፅኖ ገለጸላቸው።

አፄ ምኒልክ ለአንዱ አጃቢያቸው በጆሮው የኾነ ነገር ተናገሩ። አጃቢው ድንኳኑን ለቅቆ ወጣና በፍጥነት አንድ ኮርቻ የተጫነ በቅሎ ይዞ ተመለሰ። ስለ በቅሎው ሲናገር ፌልተር «በሕይወቴ እንደዚያ ያማረ በቅሎ ተመልክቼ አላውቅም። የንጉሡ የራሳቸው መሆን አለበት» ብሎ ነበር።





«ውድ ፌልተር፤ እንደምታውቀው እኛ ድሀ ሕዝቦች ነን። ይህ ስጦታ ወዳጅህ ጋሊያኖን እንደሚያስደስተው አልጠራጠርም» በማለት ምኒልክ በቅሎውን ለጋሊያኖ ሰጡት። ንጉሡ አፋቸውን በጋቢያቸው ሲሸፍኑ ንግግራቸው የመጨረሻ መኾኑን አመላከተ። ጋሊያኖ ምንም ቃል ሳይተነፍስ የቀረበለት በቅሎ ላይ ወጥቶ ወደ መቀሌ ሽምጥ ጋለበ።

አፄ ምኒልክ እና ፌልተር ስምምነት ላይ የደረሱት ጥር 19 ቀን ነበር። አፄ ምኒልክም ጋሊያኖ እና ሠራዊቱ ምሽጉን ለመልቀቅ ከተስማሙ ከነመሳ ጓዛቸው፣ ትጥቃቸው፣ ሴቶቻቸው እና ልጆቻቸው እንደሚለቋቸው ተስማሙ። ጥር 20 ቀን ጋሊያኖ በመቀሌው መከላከያ ግንብ አናት ላይ ነጭ ሰንደቅ እንዲውለበለብ አዘዘ።

የጋሊያኖ ወታደሮች በኢትዮጵያ ሠራዊት ጥበቃ ሥር ሆነው እንደሚጓዙ ምኒልክ አስገነዘቡ። የጋሊያኖ ወታደሮች ጓዛቸውን ለመጫን በቂ የጋማ ከብት ስላልነበራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ በቅሎዎችን ከምኒልክ ጦር ለመዋስ ተገደዱ። ለኪራይ ክፍያም ሐያ አምስት ሺህ ሊሬ ለመክፈል ሀሳብ አቀረቡ።

ጥር 21 ቀን የጋሊያኖ ሠራዊት ምሽጉን ለቅቆ መውጣት ሲጀምር ለወራት የዘለቀው ፍጥጫ ፍፃሜ አገኘ። ምሽጉ ሙሉ በሙሉ እንደተለቀቀ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሰዓታት ውስጥ አፈራረሰው። ዋናው የምሽጉ ማማ ላይም የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቀለ።

የጋሊያኖ ሠራዊት በሰላም መውጣት ዜና በጣሊያን ሲሰማ ከፍተኛ ደስታ ተፈጠረ። በርካታ የጣሊያን ጋዜጦች ዜናውን እንደ ከፍተኛ ድል ነበር የተገነዘቡት። ጋሊያኖም ከፍተኛ የደረጃ ዕድገት አገኘ። በጣሊያን ከነበረው በተቃራኒ ግን የተለያዩ የአውሮፓ ጋዜጦች ጣሊያንን እንኳሰው ነበር የፃፉት። የፈረንሳዩ «ሌ» ፔቲት ጆርናል ጋዜጣ የጠቅላይ ሚኒስትር ፍራንሴስኮ ክሪስፒን ምስል በካርቱን የፊት ገፁ ላይ ያወጣው ከአፄ ምኒልክ ጋር በማያያዝ ነበር። በምስሉ ላይ ወታደራዊ ልብስ

የለበሰው ክሪስፒ የምኒልክን ጥቁር ዓይን በፍርሃት ሲመለከት ይታያል። በርካታ የዓለም ጋዜጦች ይህንኑ ምስል ተቀባብለውታል።

የንጉሥ ኡምቤርቶ ወዳጅ የነበሩት የጀርመኑ ንጉሥ ካይዘር ዊልሄልም የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክታቸውን በፍጥነት ነበር ለጣሊያኑ አቻቸው የላኩት። ከደስታ መግለጫቸው ጋር አያይዘውም ጋሊያኖን ለመሸለም ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን ጋሊያኖ እና ባራቴሪ የጥንት የሮማውያንን ገድል መድገማቸውን አወድሰዋል።

ጋሊያኖ የተበረከተለት ሽልማት እና ዝና ከሠራው አንፃር ሲታይ ተገቢው አልነበረም። ነገር ግን በጥቂት ሠራዊቶቹ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የአፄ ምኒልክ ሠራዊት መቀሌ ላይ በማቆም ለባራቴሪ ጊዜ መግዛት ችሏል። ባራቴሪም ጊዜውን ተጠቅሞ አዲግራትን ለመያዝ ችሏል።

አፄ ምኒልክ የሰሜኑን ጉዞ የጀመሩት ጥር 22 ሲሆን የጋሊያኖን ሠራዊት በመያዝ ነበር የተንቀሳቀሱት። በሠራዊታቸው አሰላለፍ ከፊት የመንገሻ ሠራዊት ሲቀድም በመቀጠል ደግሞ የጋሊያኖ ሠራዊት ይከተላል። ዋናው የምኒልክ ሠራዊት ደግሞ ከጋሊያኖ ቀጥሎ የሚንቀሳቀስ ሲሆን መቀሌ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት የራስ መኮንን ጦር የኋላ ደጀን በመሆን ምኒልክን ይከተላል።

ከመቀሌ በኋላ ባለው ጉዞ በምኒልክ ጦር እና አዲግራት ላይ በመሸገው የባራቴሪ ጦር መካከል ምንም መከላከያ አልነበረም። ለሠራዊታቸው ደኅንነት ሲሉ ነበር የጋሊያኖን ጦር ከጦራቸው ጋር ቀላቅለው ለመጓዝ የወሰኑት። ከመቀሌ የተማሩት ነገር ቢኖር ከመሸገ ጠላት ጋር መዋጋት ከፍተኛ መስዋዕትነት እንደሚያስከፍል ነበር። የጋሊያኖን ሠራዊት እስከያዙ ድረስ ግን ባራቴሪ ጥቃት እንደማይከፍት ያውቃሉ።

አዲግራት ከመድረሳቸው በፊት ነበር አፄ ምኒልክ ሠራዊታቸውን አጉላ ላይ ለኹለት ቀናት ያሳረፉት። ከእረፍት በኋላ ጉዟቸውን ሲቀጥሉ ግን በአዲግራት የሚያልፉ አስመስለው ወደ ምዕራብ ነበር ያመሩት። ጥር 29 ቀን ሃውዜን ላይ





በማረፍ ወደ አዲግራት የሚወስደውን የሰሜን አቅጣጫ በመተው ወደ አድዋ የሚወስደውን የምዕራብ መንገድ ተያያዙ።

ሠራዊታቸው አዲግራትን ወደ ጎን ትቶ ባለፈበት ወቅት በቦታው የነበረው ባራቴሪ ሊሰነዝር ከሚችለው ጥቃት ለመከላከል እንደ ጥይት እብራጅ ያዘጋጁት የጋሊያኖን ጦር ነበር። ጥር 30 ቀን የጋሊያኖን ሠራዊት በመልቀቅ ከባራቴሪ ጋር እንዲቀላቀሉ አደረጉ። ጋሊያኖን ጨምሮ ዐሥር ከፍተኛ መኮንኖች ግን አብረዋቸው ለጥቂት ቀናት እንዲቆዩ ምኒልክ ወሰኑ።



Menelik, the Lion of Judah. Photograph taken by Alfred Ilg in 1896. From Völkerkundemuseum der Universität Zürich; credit: © Völkerkundemuseum der Universität Zürich, VMZ [illegible]

*ምስል፦ የይሁዳ አንበሳ - ዳግማዊ አፄ ምኒልክ (አልፍሬድ ኢልግ በ1896 ካነሳው ፎቶግራፍ የተወሰደ)*



Menelik, the Lion of Judah. Photograph taken by Alfred Ilg in 1896. From Völkerkundemuseum der Universität Zürich; credit: © Völkerkundemuseum der Universität Zürich, VMZ 805.01.001.

ምስል፦ የይሁዳ አንበሳ - ዳግማዊ አፄ ምኒልክ (አልፍሬድ ኢልግ በ1896 ካነሳው ፎቶግራፍ የተወሰደ)

አፄ ምኒልክ አዲግራት ላይ የነበረውን የጣሊያን ጦር አልፈው በመሄድ ቦታ ያዙ። በዚያ ወቅት ነበር ሰላም ወዳድ መሆናቸውን ለአውሮፓውያን በማሳየት የተወረረው ግዛታቸውን በድርድር የማስመለስ ፍላጎት ያሳዩት።

የካቲት 5 ቀን ባራምባራስ አማኑኤልን ወደ ባራቴሪ የላኩት አፄ ምኒልክ ጦራቸውን ከሃውዜን በማንቀሳቀስ በአድዋ አቅራቢያ ወዳለችው ጉንዳብታ እንደሚያመሩ ገለፁ። በጉንዳብታ ለአምስት ቀናት በመቆየትም ከጣሊያን ልዑካን ጋር ለመደራደር ፈቃደኛ መሆናቸውን ለባራቴሪ አሳወቁ።

በወቅቱ ከመቶ ሺህ በላይ የሆን ሠራዊታቸውን ወደ ኤርትራ ለማዝመት ዝግጁ የነበሩት አፄ ምኒልክ 17ሺ ሠራዊት ብቻ ካሰለፈው ባራቴሪ ያገኙት ምላሽ ያልጠበቁት ነበር። ባራቴሪ በመልዕክተኛው ቶማስ ሳልሳ በኩል ለምኒልክ አቋሙን የገለጸው በኹለት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ እንደሚደራደር ነበር። ይኸውም ኢትዮጵያ የውጫሌ ስምምነትን ሙሉ በሙሉ እንድትቀበል እና ጣሊያን ለያዘቻቸው አዳዲስ የኢትዮጵያ ግዛቶች የባለቤትነት ዕውቅና እንድትሰጥ የሚጠይቅ ነበር።

የባራቴሪ ቅድመ ሁኔታ በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ ቀሰቀሰ። በተለይ ጣይቱ፣ ወሌ፣ አሉላ እና መንገሻ እጅግ በጣም ነበር የተበሳጩት። ምኒልክ ለባራቴሪ በሰጡት ምላሽም ኹለት ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀመጡ። ይኸውም ጣሊያን የያዘችውን የኢትዮጵያ ግዛት እንድትለቅ እንዲሁም የውጫሌው ስምምነት ሙሉ በሙሉ እንዲስተካከል የሚጠይቅ ነበር።

የአምባላጌ እና የመቀሌውን ኹነት ተከትሎ ኢትዮጵያ ሙሉ የመደራደር ብቃቷን ስታስመሰክር ባራቴሪ በአንጻሩ አጣብቂኝ ውስጥ ነበር የገባው። አገሩ ጣሊያን በመደራደር ከአፄ ምኒልክ ጋር የማትስማማ ከሆነ የሚኖረው አማራጭ ጦርነት በመግጠም ምኒልክን ድል መንሳት ወይም ደግሞ ሸሽቶ በማምለጥ ውርደትን መከናነብ ነበር።





# ምዕራፍ አሥር

## ግራ መጋባት በሳውራ

አፄ ምኒልክ ራሳቸውን ለጦርነት ከማዘጋጀት ጎን ለጎን አልፍሬድ ኢልግ የዲፕሎማሲ ዘመቻውን በአውሮፓ እንዲያፋፍምላቸው ላኩት። ኢልግም ለአውሮፓውያን በራሳቸው ቋንቋ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ ሲገልፅ ከረመ። የውጫሌ ስምምነት የጣሊያን የማጭበርበሪያ መንገድ መኾኑንም በተለያዩ ጋዜጦች ሲፅፍ *«ለበርካታ ክፍለዘመናት ነጻነቷን ጠብቃ ከኖረች አገር ላይ እንዴት መሬት ይነጠቃል?»* በማለት ጠይቋል።

ለጣሊያናውያንም እንዲሁ መንግስታቸው የተዛባ መረጃ እየሰጠ እንዳሳሳተቸው ለመግለፅ ሞክሯል። ወጣት ጣሊያናውያን በማይገባ ጦርነት ላይ ሕይወታቸውን ማጣት እንደሌለባቸውም ኢልግ ቀስቅሷል።

የጣሊያን ጦር በአዲግራት ከፍተኛ ምሽግ ገንብቶ መጠበቁን ምኒልክ እንደማያውቁ እና የተሻለ የውጊያ ዕቅድ እንዳላቸውም ለአውሮፓውያኑ ግልጽ አድርጓል። አፄ ምኒልክ በአዲግራት የመቀሌውን ስሕተት አይደግሙትም። በመኾኑም አዲራግትን በመተው በራሱ ሰዓት የራሱን መፍትሔ እንደሚፈጥር ማቀዳቸውን ነበር ኢልግ የገለጸው።

በኢትዮጵያ ውስጥ መከፋፈል እና የሥልጣን ሽኩቻ መኖሩን ያልደበቀው ኢልግ የጣሊያንን ወረራ ተከትሎ ኹሉም ኃይሎች ልዩነታቸውን በማቻቻል አንድ ላይ መሰለፋቸውን ለአውሮፓውያኑ የገለጸው በምሳሌ አስደግፎ ነበር። *«ኹለት ውሾች በአንድ አጥንት ሊጣሉ ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ጅብ ቅርምቱን ሊቀላቀል ቢሞክር ኹለቱ ውሾች ይተባበሩበታል።»* በማለት ነበር ኢልግ ስለ ኢትዮጵያ ውስጣዊ የፖለቲካ ሽኩቻ ያስረዳው።

አውሮፓውያን የኢትዮጵያን ነጻነት ከራሳቸው አንፃር እንዲመለከቱም ኢልግ ጥሪ አቅርቧል። የአገሪቷን ሉዓላዊ እኩልነትም ሲገልፅ *‹‹ማንም አውሮፓዊ ለኢትዮጵያ መዝር እንደማይፈልግ ኹሉ ሉዐላዊት ኢትዮጵያም ለአውሮፓ ኃያላን የምትገብርበት አግባብ የለም››* ብሏል።

በ19ኛው ክፍለዘመን የነበረው የጦርነት ስሌት በሠራዊት ብዛት እና ወታደራዊ ጥራት ላይ የተመሠረተ ነበር። አፍሪካውያን ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች የተሻለ ብዙ ሠራዊት የመመልመል ብልጫ ሲኖራቸው አውሮፓውያኑ ያለባቸውን የሰው ኃይል አናሳነት ለማካካስ ዘመናዊ ሥልጠና እና የጦር መሣሪያ ብልጫቸውን ይጠብቃሉ። ምኒልክ ለጦርነት የተዘጋጁትም ይህንን ስሌት ቀድመው በመረዳት ነበር። የእርሳቸው አፍሪካዊ ሠራዊት በሥልጠናም ሆነ በትጥቅ የአውሮፓውያንን ያህል የላቀ ባይሆንም ምንም የማያውቅ ግን አይደለም። አብዛኛው የሠራዊት አባል ከምኒልክ ጋር ወደ ወላይታ እና ሌላ ግዛቶች በመዝመት ልምድ ያካበተ ነው። ልምድ የሌለው ወታደርም ቢኖር እንኳን ራሱን ለአውሮፓውያን ጥይት መስዋዕት ለማድረግ የተዘጋጀ ነው። ጦሩ በተለይም ከአምባላጌ እና መቀሌ በኋላ በጠላት ላይ ያለው አቋም ጠንካራ እና ከክብር ጋር የተቆራኘ ሆኗል።

የምኒልክ ጦር ዘመናዊ አደረጃጀት እንዳለው ባራቴሪ ሳይቀር መስክሮለታል። ስለ ሠራዊቱ ለጣሊያን መንግሥት በላከው ማብራሪያ ሲጠቅስ ‹‹… የአገሪቷ ጦር በይዘቱም ሆነ በመጠኑ በ1888 ከነበረው ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል።›› በማለት መስክሯል። ከሠራዊቱ ብዛት በተጨማሪ የምኒልክ ወታደሮች ፈረንሳይ ሠራሹን ሆችኪስ መድፍ ጨምሮ በርካታ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁ ሲሆን በዚህም ከጣሊያን ትጥቅ የላቁ ነበሩ።

ከወታደራዊ ቁጥር እና ትጥቅ ብልጫው በተጨማሪ የምኒልክ ጦር በቦታ አያያዝ ከባራቴሪ የተሻለ ሆኖ ታይቷል። አዲግራት ላይ ጣሊያንን በመግጠም





ሠራዊታቸውን ማስፈጀት ያልፈለጉት አፄ ምኒልክ የባራቴሪን የአዲግራትን ምሽግ ወደ ጎን በመተው ነበር ያለፉት። ምኒልክ የባራቴሪን የግንኙነት መስመር መቁረጥ ከመቻላቸው በዘለለ መላው ኤርትራን ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን ቦታ ለመያዝ በመንቀሳቀስ ላይ ነበሩ። የምኒልክን ግስጋሴ ለማስቆም ሲል ነበር ባራቴሪ ከመንገሻ ሽንፈት በኋላ ይዞት የነበረውን ግዛት ለመልቀቅ ያሰበው።

ባራቴሪ አዲግራት ላይ አነስተኛ ኃይል በማስቀመጥ ጦሩን ምኒልክ በሄደበት አቅጣጫ ከአዲግራት ወደ አድዋ በመምራት አለቃን ተቆጣጠረ። ምኒልክም ከባራቴሪ እየራቁ ወደ አድዋ ሲቃረቡ ባራቴሪ መከተሉን ቀጠለ። ከኹለት ቀናት በኋላ የካቲት 3 ቀን ባራቴሪ ከእንጢቾ ከተማ አጠገብ ሳውራ ላይ ጦሩን አሳረፈ። ምኒልክ ደግሞ የካቲት 5 ቀን ጉዳብታ ላይ ጦራቸውን በማደራጀት የሰላም ድርድር ጥሪ በድጋሚ አደረጉ።

በየካቲት ወር 1896 የኢትዮጵያ እና የጣሊያን ጦር በአዲግራት እና አክሱም መሃል ነበር የተፋጠጡት። የምኒልክ ጦር ከነበረበት ጉንዳብታ እስከ ባራቴሪ የጦር ሰፈር ኢንጢቾ ድረስ ያለው ሜዳማ ስፍራ ኹለት በአምስት ማይል ስፋት ነበረው። ሜዳው ዙሪያውን በተፈጥሮ ሰንሰለታማ ተራሮች የታጠረ ነው። ምኒልክ በምዕራብ አቅጣጫ ያለውን ቦታ ሲይዙ ባራቴሪ ደግሞ ሜዳውን በመሸሸ ምሥራቃዊ ኮረብታውን ይዞ ምሽግ ማስቆፈር ጀመረ።

ኹለቱ ኃይሎች ሳውራ እና ጉንዳብታ ላይ ቦታ ከያዙ በኋላ ነበር የሰላም ድርድሩን የቀጠሉት። ነገር ግን ከአንድ ሳምንት በኋላ የሰላሙ አማራጭ ተስፋ አስቆራጭ ሆነ። ኢትዮጵያም ለማይቀረው ጦርነት ተዘጋጀች።

**የከፋፍለህ ግዛ መጨረሻ፤ የራስ ስብሃት እና የሐጎስ ተፈሪ መክዳት**

ከአምባላጌ በኋላ በርካታ ጣሊያናውያን ወታደሮችን የጫኑ መርከቦች ወደ ምፅዋ መጓዝ መጀመራቸው ለባራቴሪ እፎይታን ፈጥሮለታል። በየሳምንቱ በሺህ የሚቆጠሩ ወታደሮች ምፅዋ እየተራገፉ ነበር። በየካቲት ወር መጨረሻ ላይ ብቻ ሲንጋፖር፣ አንድሪያ፣ ጎታርዶ፣ ዋሽንግተን፣ ሩባቲኖ እና ሚንጌቲ የተባሉ ስድስት መርከቦች ምፅዋ ደርሰዋል።

በጣሊያን ሠራዊት በኩል የተወሰኑ ችግሮች ነበሩ። የመጀመሪያው በጦር ግንባር ያለውንም ሆነ ከምፅዋ ወደ አዲግራት የሚመጣውን ሠራዊት መመገብ ነበር። ከአስመራም ሆነ ከሌሎች አካባቢ በቂ ምግብ ማቅረብ ስላልተቻለ ሥጋ ይመጣ የነበረው ከህንድ ሲሆን ሌላ አቅርቦት ደግሞ በቀጥታ ከጣሊያን ነበር የሚመጣው። ከምፅዋ ወደ መሃል አገር የሚደረገው የማጓጓዝ ተግባር የራሱ የሆነ ችግር ነበረበት። ከምፅዋ እስከ አስመራ በአነስተኛ ባቡር የተጓጓዙ አቅርቦት እና ወታደሮች ከአስመራ ወደ አዲግራት ደግሞ ይጓዙ የነበረው በጋማ ከብቶች ነበር።

ወደ አዲግራት የሚደረገው ቀሳቀስ ማጓጓዝ ከጋማ ከብት እጥረት በተጨማሪ በሽፍታ ይስተጓጎል ነበር። ከምፅዋ የሚነሱ ተጓዦች አዲግራት ለመድረስ ኢላልያ፣ ማህዮ፣ አዲ ቀይህ፣ ሰንአፌ፣ ባራኺትን እና አዲ ጉደምን ማለፍ የግድ ይላቸዋል።

የባራቴሪ ጦር እንደ ምኒልክ ኹሉ የማፈንገጥ አደጋ አጋጥሞል። መንገሻ ያስኮረፏቸውን ኹለት የአጋሜ አካባቢ አስተዳዳሪዎች (ራስ ስብሃትን እና ሐጎስ ተፈሪን) መመልመል ችሎ ነበር። ኹለቱም የአጋሜን ግዛት በተለያዩ ጊዜያት ካስተዳደሩ ቤተሰቦች የተገኙ ሲሆን በ1895 ባሥነሱት የእርስ በእርስ ግጭት ኹለቱን በማባረር ከግዛት አስተዳዳሪነታቸው ያነሳቸው መንገሻ ነበር።





የሻከረ ግንኙነታቸውን ለማለዘብ መንገሻ ኹለቱንም አኩራፊዎች ወደ አድዋ ጋበዛቸው። ሐጎስ ተፈሪ ተጠራጥሮ ሲቀር ራስ ስብሃት ግን ሄደ። በግብዣው መሃል ግን ራስ ስብሃት በመንገሻ ወታደሮች ታሰረ።

በኋላም ራስ ስብሃት በግዞት ወደ አምባላጌ ተልኮ ታሰረ። ራስ ስብሃት ከአምባላጌ እሥር ቤት በጥቅምት 1895 የተለቀቀው በጣሊያኖች ምህረት ነበር። ከሳምንት በኋላ ከጣሊያን ጎን ሆኖ መንገሻን መውጋት ጀመረ።

በመንገሻ ጭካኔ የተበሳጨው ሐጎስ ተፈሪም ከጣሊያን ጋር በመወገን መንገሻን ሲወጋ ቆይቷል። በ1895 ሰንአፌ ላይ መንገሻ ሲሸነፍ በርካታ የጦር መሣሪያ፣ የቁም ከብት እና የተለያዩ ንብረቶችን ከሸሸው ጦር ላይ በመዝረፉ ሃይሉን አጎልብቷል። በ1895 የመጨረሻ ወራት ላይ ኹለቱ ኢትዮጵያውያን ከጣሊያን ጎን ተሰልፈው ነበር።

ራስ ስብሃትን እና ተፈሪን ከጎኑ ማሰለፍ የቻለው ባራቴሪ የ‹‹ከፋፍለህ ግዛ›› ዕቅዱን ለማሳካት አንድ እርምጃ መራመድ ችሏል። የመንገሻን ኃይል በማሳሳትም የራሱን የሠራዊት ቁጥር ከፍ ከማድረግ አንፃርም የኹለቱ ተከታዮች ከጦሩ ጋር መቀላቀል አስተዋፅኦ አድርጎለታል።

ራስ ስብሃት እና ሐጎስ አጋጣሚውን ለመጠቀም እንጂ ከባራቴሪ ጋር የወገኑት በእርግጥም ከሃዲዎች ሆነው አልነበረም። ከአምባላጌ እና መቀሌ ዘመቻዎች በኋላ በተለይም በየካቲት ወር ላይ የምኒልክን እንቅስቃሴ ከተመለከቱ በኋላ ነበር ባራቴሪን ለመክዳት የወሰኑት። በመኾኑም የካቲት 13 ቀን ኹለቱም ወታደሮቻቸውን ከነ ሙሉ ትጥቃቸው በማስኮብለል የጣሊያንን ካምፕ ለቀቁ።

የእነ ስብሃት ሠራዊት ምኒልክ ካምፕ ሲደርስ የደግና አቀባበል ነበር የተደረገለት። ስብሃት እና ተፈሪም ከፍተኛ ውዳሴ ተደረገላቸው። ባራቴሪ የገመተው

ኹለቱ የካዱት መንገሻ ዮሐንስን በመኾኑ በምንም መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ሠራዊት እንደማይቀላቀሉ ነበር። የሠራዊቱ ወደ ምኒልክ መመለስ የኢትዮጵያን ውስጣዊ መረጋጋት ያረጋገጠ ሲሆን የባራቴሪን ከፋፍሎ የመግዛት ዕቅድም ጥያቄ ውስጥ ከተተው።

## የጣሊያን ይዞታ መፍረክረክ

የራስ ስብሃትን እና የተፈሪን መክዳት ተከትሎ የአጋሜ አካባቢ ነዋሪዎች በጣሊያን ላይ ማመፅ ጀመሩ። በርካቶችም ኹለቱን በመከተል የከዳውን የሠራዊት ቁጥር በሦስት እጥፍ ከፍ አደረጉት። የባራቴሪን ካምፕ ለቀው በወጡ በአምስተኛው ቀን በምኒልክ አበረታችነት የስብሃት እና ተፈሪ ሠራዊት የባራቴሪ የግንኙነት መስመር ላይ የምትገኘውን ባራኪት ከተማ ለመቆጣጠር ተንቀሳቀሱ።

በአዲግራት ዙሪያ የነበረው የሳውራ ጦር ካምፕ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት። የካቲት 14 ቀን 110 የጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃት የተሰነዘረ ሲሆን ድጋፍ ለመስጠት ባራቴሪ የላካቸው 35 ወታደሮች በሙሉ ተገደሉ። የካቲት 16 ቀን የምኒልክ ታማኞች በአዲግራት አቅራቢያ በመመሸግ ከአስመራ ወደ አዲግራት በመንዝ ላይ የነበረውን የጣሊያን ስንቅ እና ትጥቅ ዘረፉ። በዘረፋ ያገኙትን የጣሊያን ዮኒፎርም በመልበስ ተመሳስለው በመጠበቅም በቀጣዩ ቀን ለቅኝት በወጡ 140 የጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃት ፈፀሙ።

የዘረፋ ጥቃቱን ተከትሎ ባራቴሪ የግንኙነት መስመሩን በመቀየር የማይመራት እና የደብረዳሞን መንገድ ለመጠቀም ወሰነ። የእነ ስብሃትን መክዳት ቀድሞ የሰማው የደብረዳሞ አካባቢ ነዋሪም ባራቴሪ ላይ በማመፅ ለምኒልክ ታማኝነቱን አረጋገጠ።

የምኒልክ ታማኞች በአዲግራት እና ሳውራ መካከል በመመሸግ የጣሊያንን ወታደራዊ ትጥቅ እና ስንቅ አቅርቦት ማጥቃት ጀመሩ። ጣልያናውያኑ በጭለማ





መንቀሳቀስ ቢጀምሩም የሽምቅ ተዋጊዎች ጥቃታቸውን ቀጠሉ። የስንቅ አቅርቦቱ በመስተጓጎሉም የጣሊያን ወታደሮች በየኹለት ቀናት ብቻ በሚሰጥ የዱቄት፣ ሥጋ እና ቡና ራሽን ለመኖር ተገደዱ። ለባንዳ ሠራዊት ቀድሞ ለጋማ ከብት ይቀርብ የነበረው ገብስ መታደል ጀመረ።

ሠራዊቱ በምግብ እጥረት መቸገር የጀመረው በየካቲት ወር የመጨረሻ ሳምንት ነበር። የተወሰኑ ባንዳ ወታደሮች አጋጣሚውን በመጠቀም ለጣሊያን ወታደሮች ምግብ በመሸጥ ገንዘብ ማግኘት ጀመሩ። ሉጂ ጎጂ እና ካርሎ ዲዮቲ እንደተናገሩት ሠራዊቱ የምግብ መጋዘኖችን መስበር ጀምሯል። ከምግብ አቅርቦት ችግር ጋር በተያያዘ በሠራዊቱ መካከል የዲሲፕሊን ችግር ተፈጠረ።

ባራቴሪ ለጣሊያን የጦር ሚኒስቴር ስታኒስላኦ ሞቼኒ የካቲት 18 ቀን በላከው ቴሌግራፍ «የስብሃት እና ሓጎስ ሠራዊት በአዲግራት ዙሪያ መሽጓል» በማለት በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየቀ። ሚኒስትሩ በላኩት ምላሽ «የተሻለ አማራጭ የምትለውን አሳውቅ። አስፈላጊውን ድጋፍ እናደርግልሃለን» በማለት የመንግስታቸውን አቋም አሳወቁ።

የጦር ሚኒስትር ሞቼኒ በርካታ ወታደሮች ለባራቴሪ ሲልኩ ቆይተዋል። በዚያው ዓመት የጦርነቱ ወጪ በመብዛቱም ከገንዘብ ሚኒስትሩ ሲድኒ ሶኒኖ ብርቱ ተቃውሞ ሲሰነዘርባቸው ቆይተዋል። የጦርነቱን ወጪ ለመቀነስ የሚቻለው ውጊያው ከአንድ ወር በላይ እንዳይወስድ በማድረግ መኾኑን ሞቼኒ ለሚኒስትሩ ገልፀውላቸው ነበር። ጦርነቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በድል ማጠናቀቅ የጣሊያን ብርቱ ፍላጎት ነበር።